

እጅ ያጠረው ዕድሜ

ገጽ 16



ሌላው የኮንስትራክሽን ዘርፍ ፈተና

የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች እጥረትና የዋጋ ንረት

ገጽ 14

አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 098 ታኅሣሥ 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



# በኢትዮጵያና በአሜሪካ መሪዎች መካከል የተካሄዱ ግንኙነቶች የዲፕሎማሲ እመርታ ማሳያዎች ናቸው

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከዩኤስ አፍሪካ ጉባኤ ጎን ለጎን ያደረጓቸው ግንኙነቶች የሁለቱ ሃገራት የዲፕሎማሲ እመርታ ማሳያ መሆናቸውን ጋዜጠኛ አሊሰቴር ቶምሰን ተናገረ።

ጋዜጠኛ አሊሰቴር ቶምሰን ከፒስ ቶክ ኢትዮጵያ ጋር ባደረገው ቆይታ እንደገለጸው፤ በሁለቱ መሪዎች መካከል የተደረገው ግንኙነት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ግልፅና በተግባር ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ ተስፋ ሰጪ ጉዞ ላይ ወደፊት መምጣት መቻላቸውን አመላካች ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን የሁለቱ መሪዎች ግንኙነት አሜሪካ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን አመራር መቀበሏንና ለኢትዮጵያ ያላት አመለካከት አወንታዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብሏል።

በዋሽንግተን የተካሄደው ስብሰባ አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲ አንድ ደረጃ ወደፊት ያስፈነጠረ ነውም ብሏል። ለሚቀጥሉት የሁለቱ ሀገራት

በኢትዮጵያና በአሜሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# «በሰሜኑ የነበረው ጦርነት መቋጨቱ ያበሳጫቸው አካላት በኦሮሚያና በአዲስ አበባ ግጭት ለማንገስ እየሠሩ ነው»

\- ዶክተር አረጋዊ በርሄ
የትዴፓ ሊቀመንበር

ሰላማዊት ውቤ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ ባደረጉት ስምምነት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የነበረው ጦርነት መቋጨቱ ያበሳጫቸው አካላት በኦሮሚያና አዲስ አበባ ሁከትና ብጥብጥ ለማንገስ እየሠሩ ነው ሲሉ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ተናገሩ።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ዶክተር አረጋዊ በርሄ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን የተረዱ አካላት ስምምነቱ መሬት እንዳይረግጥ በአዲስ አበባና በወለጋ ሁከትና ብጥብጥ ለማንገስ በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

«በሰሜኑ የነበረው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ኮሚሽኑ በ1 ሺህ 300 ወረዳዎች የምክክር ተሳታፊዎች ልየታ ሊያካሂድ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በ1 ሺህ 300 ወረዳዎች የምክክር ተሳታፊዎች ልየታና ምዝገባ በቅርቡ እንደሚጀምር የኮሚሽኑ አመራሮች ገለጹ።

የኮሚሽኑ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ወይዘሮ ሂሩት ገብረሥላሴና ኮሚሽነር ዘገየ አስፋው፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአሁኑ ወቅት ስለምክክር ሂደቱ፣ ስለተሳታፊዎች ልየታ የሃሳብ ግብዓት የመሰብሰብ ሥራዎችን እያከናወነ ነው ብለዋል።

ኮሚሽኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



በክልሉ በመስኖ ግብርና ከ10 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል

ገጽ 4





ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲን ለመገንባት ጥረት እንዲደረግ ጥሪ ቀረበ

ገጽ 3

# የሠላም ሥምምነቱን ተከትሎ 229 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁስ ወደ ትግራይ ክልል ተልኳል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ወደ ትግራይ ክልል ግምታቸው 229 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁስ መሰራጨቱን የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ገለጸ።

አገልግሎቱ በመቀሌና በሽሬ የሚገኙ ቅርንጫፍ ቢሮዎቹ በከፊል ሥራ መጀመራቸውንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ ለኢዜአ እንዳሉት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በሦስት አቅጣጫዎች መድኃኒቶችን ወደ ትግራይ እየተሰራጩ መሆኑን ገልጸዋል።

በመጀመሪያው ዙር 229 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የሕክምና ግብዓቶች ወደ ትግራይ ክልል መላካቸውን ጠቁመዋል።

በመቀሌ እንዲሁም በሽሬ የሚገኙ የአገልግሎቱ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በከፊል ሥራ መጀመራቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

የመድኃኒቶቹ ዓይነትም የጤና ፕሮግራም መድኃኒቶች (የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የወባ እንዲሁም የእናቶችና ሕጻናት መድኃኒቶች) መሆናቸውን ጨምረው ገልጸዋል።

ለመደበኛ፣ ለሕይወት አድን የሚውሉ መሠረታዊ መድኃኒቶችና ለሕክምና አገልግሎትና ለላቦራቶሪ ግብዓት የሚውሉ ኬሚካሎች መሰራጨታቸውን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

እንደ ስኳርና ደም ግፊት የመሳሰሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለማከም የሚያገለግሉ መድኃኒቶች መካተታቸውንም እንዲሁ። የሁለተኛ ዙር የመድኃኒት ሥርጭት በቀጣዮቹ ቀናት እንደሚጀመርም ጠቁመዋል።

እንዲሁም የመቀሌና የሽሬ ቅርንጫፎች ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ እንዲገቡ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። መድኃኒቶቹን ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲጓጓዙ መደረጉንም ጠቁመዋል።

# ተቋማቱ ራስ ገዝ መሆናቸው የአስተዳደር ነፃነትን በመስጠት ተልዕኳቸውን እንዲፈጽሙ ያስችላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው የአስተዳደር ነፃነትን በማጎናፀፍ ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲፈጽሙ ያስችላል ሲሉ የትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሠረት ልማት ጉዳዮች ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሰለሞን አብርሀ (ዶክተር) ገለጹ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታቸውን ያደረጉት ዶክተር ሰለሞን አብርሃ እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው አስተዳደራዊ ነፃነትን በመስጠት የራሳቸውን መዋቅራዊ ቅርጽ የመወሰን ስልጣን እንዲኖራቸው ያደርጋል።



ሰለሞን አብርሀ (ዶ/ር)

ይህ ማለት ተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮችን የመሾም፣ የመሻር፣ የውስጥ አሠራር መመሪያ ሥርዓቶችን የማጽደቅ፣ የተለያዩ ገቢ ሊያመነጩ የሚችሉ አደረጃጀቶችን የመፍጠር፣ የሠራተኞቻቸውን ክፍያ የመወሰን እንዲሁም ተማሪዎች ለመማር መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ ለመተመን እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፤ ይህን ሲያደርጉ ዋና ዓላማው ገንዘብ እንዲሰበስቡ ሳይሆን የሚጠበቅባቸውን መሠረታዊ ተልዕኮ የሚፈጽሙበትን ሀብት ማመንጨት እንዲችሉ ነው ብለዋል።

ዩኒቨርቲዎቹ የተመሠረቱበት ዋነኛ ተልዕኮም የመማር ማስተማር ሥራ ማከናወን፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማካሄድ እና የማኅበረሰብ አቀፍ ሥራዎችን በተገቢው መንገድ መሥራት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ዶክተር ሰለሞን አክለውም ተቋማቱን ራስ ገዝ ማድረግ አስፈላጊ የሆነበት አንዱ ምክንያት የትምህርት ጥራቱን በይበልጥ ማረጋገጥ እንዲቻል ነው። ይህን ለማረጋገጥ የምንችለው አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶች እና የሰው ኃይል ሲሟላ ነው። ከነዚህም መካከል ቤተ መጽሐፍት፣ ላብራቶሪ፣ የተማሪዎች አገልግሎት መስጫ ስፍራ፣ ብቁ መምህራንና መሰል ግብዓቶችን ተቋማቱ በራሳቸው ሲያሟሉ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክተርና የአዲሱ ዩኒቨርሲቲ መዋቅር አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተክሉ ታፈሰ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርስቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው ለተቋማቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል።

በተለይ የአካዳሚክ ነፃነትን ለማስጠበቅ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን ከመንግሥት ከመጠበቅ ባሻገር ተቋማት ለራሳቸው ምቹ በሆነ መልኩ እንዲያደራጁ እና ተጨማሪ ሀብትን እንዲያመነጩ በማገዝ፤ የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ ከሀገርና ከአህጉሩ አልፎ ለዓለም አቀፍ ገበያ ብቁ የሆነ የሰው ኃይል ለማዘጋጀት ያግዛል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ተክሉ ገለፃ፤ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ራሱን ራስ ገዝ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል በምጣኔ ሀብት ረገድ እራሱን ለማብቃት ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ተቋማትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ ሌሎች አቻ ዩኒቨርሲቲዎችና አጋር ተቋማት ጋር በጤና፣ በግብርናና በመሳሰሉ ዘርፎች እየሠራ ይገኛል።

ሌሎች ጥናት ላይ የተመሠረቱ ገቢ ማመንጫ ሐሳቦችን በማፍለቅ ከምሥራቅ አፍሪካ አልፎ በአፍሪካ ደረጃ ተፈላጊ የሆኑ የትምህርት መስኮችን በመቅረጽ ገቢ ለማግኘት በትኩረት እየተሠራበት እንደሆም ገልጸዋል።

አዲስ ነገር ሲጀመር መንገራገጭ እንደሚፈጠር ታሳቢ በማድረግ ካሁኑ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን እያዘጋጁ እንደሆነም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽን ስትራቴጂና ኮሙኒኬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ዘውዱ እምሩ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ እንዲሆን የሚያስችሉ ዝግጅቶችን የምሑራን ኮሚቴ በማዋቀር እየሠራበት ይገኛል።

ዶክተር ዘውዱ እንደተናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው። ከእነዚህ ውስጥ የራሱን የቅጥር ጉዳዮች ይሠራል፣ የሚሠሩትን ሠራተኞችና ተመራማሪዎች በውጤታቸው መሠረት የሚያበረታታበት ሥርዓት ይኖረዋል። ከደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችንም ለመፍታት ያስችላል።

ዶክተር ዘውዱ አክለውም ራስ ገዝ የመሆኑ ጉዳይ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ከመንግሥት ውጭ ይሆናሉ ማለት ሳይሆን ራሳችንን እንድንገመግም እና ያለንበትን ደረጃ እንድናውቅ ነው። እኛም ይህንኑ ሀሳብ በመቀበል ወደ ሥራ በመግባት አቅማችን ምን ያክል እንደሆነ በመለየት መሥራት ያለብንን ሥራዎች በመሥራት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሰለሞን ገለፃ፤ ተቋማቱ ጋር ራስ ገዝ እንደሚሆኑ ተስማምተናል፤ በዚህ ዓመት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ራስ ገዝ እናደርጋለን፣ በሁለተኛ ዙር ከሁለት ዓመት በኋላ ራስ ገዝ የምናደርጋቸውን ስምንት ዩኒቨርሲቲዎች ለይተናል። አሁን ላይ ያለው ነገር ተቋማቱ ራሳቸው ያሉበትን ደረጃ እየገመገሙ ማድረግ ነው፤ ምክንያቱም ተቋማዊ ነፃነት ዝም ብሎ የሚሰጥ አይደለም፤ በአካዳሚክ፣ በፋይናንስ እንዲሁም በሰው ኃይል ስምሪት የሚታዩ ነገሮች አሉ፤ ይህንን በተመለከተ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

# በጤናው ዘርፍ የሚስተዋለውን የተደራሽነት ችግር ለመፍታት የዲጂታል ቴክኖሎጂው ትልቅ አቅም ይሆናል

**አጸገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ ፡- በጤናው ዘርፍ የሚስተዋለውን የተደራሽነት ችግር ለመፍታት የቴክኖሎጂ አማራጮችን መጠቀም ትልቅ አቅም እንደሚሆን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

የአፍሪካ ቴሌ ሜዲስን ኔትዎርክ በአዲስ አበባ የመጀመሪያው ጉባኤውን ሲያደርግ የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ እንዳሉት በጤናው ዘርፍ የሚስተዋለውን የተደራሽነት ችግር ለመፍታት ብሎም ታካሚዎች ከሕክምና ባለሙያዎች እንዲሁም የሕክምን ተቋማት እርስ በእርሳቸው ተሳስረው እንዲሠሩ ለማስቻል ቴክኖሎጂዎች ሚናቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም።



ፎቶ - አዮብ ተፈራ

ዶክተር ሊያ ታደሰ

በኮቪድ 19 ወቅት ቴሌ ሄልዝ የሚል ቴክኖሎጂ በሥራ ላይ መዋሉን የጠቀሱት ዶክተር ሊያ በዚህም ኅብረተሰቡ በተለያየ መንገድ አገልግሎት ሲያገኝ ነበር፤ብዙ ተቋማት ተጠቅመውበታል፤አሁንም የአፍሪካ ቴሌ ሜዲስን ኔትዎርክ እያስተዋወቀ ያለው ዘመናዊ መተግበሪያ የጤናውን ዘርፍ ተደራሽነት ከፍ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

እንደ ሀገርም እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ዲጂታል ስትራቴጂ ተከትሎ ዲጂታል ጤና ስትራቴጂ አዘጋጅተን ወደ ትግበራ ገብተናል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከዚህም መካከል የቴሌ ሜዲስን አንዱ ነው ብለዋል።

ይህ ቴክኖሎጂ ብዙ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ከመሆኑም በላይ ታካሚዎች በስልክ ብቻ ባለሙያዎችን አግኝተው ምክር ከመጠየቅ ጀምሮ የተለያዩ ሕክምናዎችን ማግኘት ያስችላቸዋል፤ ይህ ደግሞ በጤና ተቋማት ላይ የሚፈጠረውን ጫና ያቃልላል ሲሉም ጠቁመዋል።

ራጅ፣ አልትራሳውንድና ሌሎች ነገሮች ከተወሰዱ በኋላ እነሱን ለመተንተን የሚችሉ ስፔሻሊስቶች በሌሉባቸው አካባቢዎች ላይ ባለሙያዎቹ ካሉባቸው አካባቢዎች ጋር የማገናኘት ሥራ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በቴሌ ራዲዮሎጂ ተጀምሯል። በዚህም 19 ሆስፒታሎች ተሳስረው ይሰራሉ፤ ይህንን ማድረጋችን ደግሞ ተጠቃሚው አገልግሎቱን ሳይቸገር እንዲያገኝ፤ ተቋማትም ተረዳድተው መሥራትን እንዲለምዱ በማድረግ የጤና ዘርፉን ተደራሽነትንና ጥራትን ማሻሻል አስችሏል ብለዋል። አሁን ደግሞ አፍሪካ ቴሌ ሜዲስን ኔትዎርክ ይፋ ያደረገው የቴክኖሎጂ ውጤት የጤናውን ዘርፍ አንድ እርምጃ የሚያራምድ መሆኑንም አክለዋል።

ይህ ኔትዎርክ ከኢትዮጵያ አልፎ በተለያዩ የዓለም አገራት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶችን የሚያቀናጅ ከመሆኑም በላይ፤ አገልግሎቱን የሚያደርስ ማበልጸጊያም ይፋ ሆኗል፤ በመሆኑም ከጤና ተደራሽነት አኳይ በጣም የሚጠቅም ነው ብለዋል።

“በኢትዮጵያ በርካታ ሕዝብ የተንቀሳቃሽ ስልክ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ነው፤ በመሆኑም ሕመም ሲሰማው ሆስፒታል መሄድ ሳያስፈልገው ባለበት ሆኖ “ሃበሪ ዶክን” በመጠቀም የቴሌ ሜዲስን አገልግሎት ማግኘት ይችላል። ይህ አሠራር ወደፊትም እንደ ሀገር አጠናክረን የምንቀጥልበት አገልግሎት አሰጣጥ ነው” ብለዋል።

በመሠረተ ልማት ዙሪያ ጥያቄ የቀረበላቸው ሚኒስትሯ ሲመልሱም የመሠረተ ልማት ጉዳይ መሠረታዊ ቢሆንም ለጊዜው ባለን እየተጠቀምን ወደፊት ግን አገልግሎቱን እያሻሻልን ጎን ለጎን የምንሠራው ይሆናል በማለት መልሰዋል።

“ቴሌ ሜዲስን ማለት አንድ ሰው ሕመም ቢሰማውም ወደሆስፒታል መሄድ ሳያስፈልገው በስልክ ግንኙነት የሚፈልገውን የሕክምና ባለሙያ አግኝቶ ሕክምና ማግኘት የሚችልበት ሂደት ነው፤ በዚህ መንገድ ሐኪሙ ታካሚውን በቀጥታ በማግኘት በበሽታው ዙሪያ በመነጋገር ላብራቶሪ ካስፈለገው እዛው ያዛል፤ መድኃኒቱንም እንደዚያው፤ በተለየ ሁኔታ ሰውየው ወጥቼ መድኃኒት አልገዛም ቢል ቤቱ ድረስ የሚሄድለትን አገልግሎት እስከማግኘት የሚያደርስ ነው” የሚሉት ደግሞ የአፍሪካ ቴሌ ሜዲስን ኔትዎርክ መሥራች ዶክተር አከዘ ጣዕመ ናቸው።

በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ የሕክምና ማዕከላት በተቀናጀ መልኩ ለኅብረተሰቡ ቀልጣፋ ዘመናዊና ተደራሽ የሆነ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡበትና በዘርፉ የተሠማሩ ባለሙያዎችም ለሙያቸው የኅብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ የአገልግሎት ክፍያን ጠይቀው የሚሠሩበት በአገራችን የመጀመሪያ የሆነ ቴክኖሎጂ መሆኑን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ ትልልቅ የሕክምና ተቋማትና ባለሙያዎችን የሚያሳትፍ ነው ያሉት ዶክተር አከዘ ተጠቃሚ ለመሆን መተግበሪያውን “ሃባሪ ዶክ “ በእጅ ስልካችን ላይ ብቻ መጫን ነው የሚጠበቀው ብለዋል። በሌላ በኩልም የዲያግኖስቲክስ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በሙሉ አባል ናቸው። በመሆኑ ይህ መተግበሪያ ሁሉንም አገልግሎት በአንድ ላይ ተደራሽ የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል።

እስከ አሁን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው አገልግሎቱን እንዲሰጥ የሆነው። ነገር ግን የሕክምና ባለሙያዎች ሲቀላቀሉ የሕይወት ታሪካቸው አብሮ ስለሚያያዝ ምን ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪም እንደሆኑ በዛው ላይ ማየት ስለሚቻል ኅብረተሰቡ ይግባባኛል የሚለውን ባለሙያ መርጦ መገልገል ይችላል ሲሉም ተናግረዋል።

አሁን ላይ ከሀገር ሀገር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሕዝብን ከሕዝብ የሚያባሉ ብዙ ናቸው። እኛ ደግሞ ቴክኖሎጂውን ተጠቅመን የጤናውን ዘርፍ እናዘምን፤ አገልግሎቱን ተደራሽ እናድርግ እያልን ነው፤ ስለዚህ ሀገሪቱ ውስጥ ያለው የቴሌ መሠረተ ልማት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ሊያስቸግር ቢችልም በመሠረታዊ ችግርነት የሚነሳበት ቁመና ላይ ግን አይደለም ብለዋል።

ታካሚው የትም ቦታ ቢሆን ስፔሻሊስቱ በተባለው ሰዓት መስመር ላይ ከሆነ ያለምንም ችግር አገልግሎቱን ያገኛል፤ ከምንም በላይ ከክልል እየመጡ የሚጉላሉ ወገኖቻችን እዛው ባሉበት ቦታ ሆነው ሕክምና እንዲያገኙ ያስችላል ሲሉም ጠቁመዋል።

የዲጂታል ጤና አገልግሎት በደንብ እንዲለመድ ብዙ ማበረታቻዎች እንዳሉ በመንግሥት በኩልም ሲገለጽ ነበር። ይህ መሆኑ ደግሞ የሚሰጠውንም አገልግሎት ደረጃ ለማውጣት ይመቻል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለት ሺ ሐኪም በቴክኖሎጂው ላይ አገልግሎት ሲሰጥ አንዱ የአንዱን ሥራ የማየት ዕድሉ ይኖራል፤ በመሆኑም ሥራውን ተናቦ ለመሥራትም ሚናው የጎላ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር አከዘ ገለጻ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ከ2 ሺ በላይ ባለሙያዎች ወደ ቴክኖሎጂው ይቀላቀላሉ ተብሎ ይጠበቃል። ሥራውን ሊያሠራ የሚችል መደላደል በማስፈለጉም ሀባሪ ዶክ (Habaridoc) የተሰኘ መተግበሪያ በልጽጓል። ለመላው አፍሪካም ይፋ ይደረጋል። በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታትም ሩዋንዳ፣ ኬንያ፣ ሱዳንና ሌሎች አገሮች ይህንን መተግበሪያ መጠቀም ይጀምራሉ። ኢትዮጵያውያን ደግሞ በተለየ ሁኔታ ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት በነጻ እንዲገለገሉበት ከአገልግሎቱ ጋርም እንዲተዋወቁ ይደረጋል።

# ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲን ለመገንባት ጥረት እንዲደረግ ጥሪ ቀረበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲን ለመገንባት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ሊያደርጉ እንደሚገባ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሳሰበ። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዩኒቨርሲቲው የመስክ ምልከታ አካሂዷል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ የትምህርት ዩኒቨርሲቲው "እያስተማርኩ እገነባለሁ፤ እየገነባሁ አስተምራለሁ" ብሎ ያስቀመጠውን ራዕይ እውን እንዲያደርግ የገጠሙትን የመሠረተ ልማቶች፣ የማስፋፊያ ግንባታዎች እና የበጀት ችግሮች ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረባረብ እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የሀገር ባለውለታ የሆነውን ዩኒቨርሲቲ በማስፋፊያ ግንባታ ችግር ምክንያት ሕንፃ ተከራይቶ እያስተማረ ይገኛል ያሉት ዶክተር ነገሪ፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የዩኒቨርሲቲውን ቦርድ አመራሮች ጨምሮ ባለድርሻ አካላት ዩኒቨርሲቲው ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት ድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ዩኒቨርሲቲው ከገጠሙት ችግሮች በፍጥነት እንዲወጣ የቋሚ ኮሚቴው ክትትል እንደማይለየው ሰብሳቢው ተናግረው፤ ችግሩን ለመፍታት ክልሎችም ተባባሪ ሊሆኑ እንደሚገባ ዶክተር ነገሪ ተናግረዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባላት በግቢው ውስጥ እየተገነቡ የሚገኙ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ፣ ክሊኒክ እና መማሪያ ክፍሎችን ተዘዋውረው የተመለከቱ ሲሆን፣ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ መርሐ-



ዶክተር ነገሪ ሌንጮ



ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና

ግብር ተጠናቅቀው ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆኑ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ክትትላቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ብርሃነ-መስቀል ጠና (ዶክተር) በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው ባለቤትና ተመልካች አጥቶ በመቆየቱ አሁን ላይ ውስብስብ ችግሮች ሊገጥሙት ችለዋል፤ ከችግሮቹ ስፋት አኳያ ከዩኒቨርሲቲው አመራሮች ባለፈ ባለቤት ሊኖረው ይገባል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲውን የሚመራው አካል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተገነቡ ፕሮጀክቶችን መቆጣጠር የሚያስችል አሠራር ባለመኖሩ ምክንያት ግንባታዎች የጥራት ችግር ገጥሟቸዋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተገነባ ሦስት ዓመት የሆነው ባለ ስምንት ወለል ሕንፃ በጥራት መጓደል ምክንያት እያፈሰሰ እንደሆነ ገልፀዋል።

ፕሬዚዳንቱ አክለውም፤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲው ይዞታ 16 ሄክታር የነበረ ቢሆንም፤ በመንገድ ማስፋፊያ ምክንያት አሁን ላይ ይዞታው ወደ 14 ሄክታር ዝቅ እንዳለ ገልፀዋል።

ይህም ዩኒቨርሲቲው በግቢው ውስጥ የማስፋፊያ ግንባታዎችን ለመገንባት ማነቆ እንደሆነባቸው ተናግረው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከሚመለከተው አካል ጋር እንደተነጋገሩና በጎ ምላሽ እንደተሰጣቸው ጠቅሰዋል።

ዶክተር ብርሃነመስቀል እንዳስታወቁት፤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲው አንጋፋ መምህራንን በማፍራት ረገድ የሀገር ባለውለታነቱን ቢወጣም፤ ዩኒቨርሲቲውን የሚመጥን መሠረተ ልማቶችና ማስፋፊያዎች ባለመገንባታቸው ወደ ኋላ ቀርቷል። ከግንባታ ባሻገርም በጀቱ ዝቅተኛ በመሆኑ በተለይም ትምህርት ሚኒስቴር እና ገንዘብ ሚኒስቴር ለዩኒቨርሲቲው ልዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

# በክልሉ ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ተሰበሰበ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴን በመኸር ወቅት መሰብሰብ እንደተቻለ ተገለጸ። በክልሉ በምርት ዘመኑ በመኸር ወቅት ከ177 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆነው መሬት በስንዴ ሰብል ተሸፍኗል።

እስካሁን በተደረገው የምርት አሰባሰብ ሂደትም ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት መሰብሰቡን በደቡብ ክልል በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዑስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልፀዋል።

እንደ አቶ ዑስማን ገለጻ፤ በአብዛኛው በክልሉ ቆላማ አካባቢዎች ሰብልን ከማሳ ወደ ጎተራ የማስገባት ሥራ ለብክነት በማያጋልጥ ሁኔታ እየተካሄደ ሲሆን፤ ከ70 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ከ40 በመቶ በላይ የስንዴ ሰብል መሰብሰብ ተችሏል።

የዘንድሮው የመኸር አዝመራ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈና በሜካናይዜሽን ስልት መከናወኑን የጠቀሱት አቶ ዑስማን በተለይም ምርትን በኮምባይነር የመሰብሰብ ሥራው የምርት ብክነትን በሚቀንስ መልኩ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

እስከ አሁን በመኸር ወቅት በሰብል ከተሸፈነው 177 ሺህ ሄክታር መሬት የስንዴ ምርት ውስጥ ከ3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰብ መቻሉን አመላክተዋል።

በአሁኑ ወቅት በክልሉ እንደ ጉራጌ፣ስልጤ፣ሃላባ፣ከምባታ፣ሃዲያ፣ወላይታ ባሉ የስምጥ ሸለቋማ አካባቢዎች እንዲሁም በከፊል የስንዴ ምርት በስፋት በደረሰባቸው ዞኖች የመኸር የስንዴ ምርት መሰብሰብ እንደተቻለ አቶ ዑስማን ገልጸዋል። ሰብሎች



አቶ ዑስማን ሱሩር

ገና እየደረሱ በመሆናቸው የመሰብሰብ ሥራው በቀጣይም በስፋት ይሠራል ብለዋል።

የምርት አሰባሰቡ ሂደቱ የምርት መሰብሰብ ብክነትን በመቀነስ፣የገበያ ተወዳዳሪነትን በመጨመር፣ የምርትና ምርታማነት ጥራትን በማሳደግ እንደሆነም አቶ ዑስማን ተናግረዋል።

በምርት አሰባሰብ ሥራው ከክልል እስከ ወረዳ ያሉት መዋቅሮች የተሳተፉ ሲሆን ለዚሁ አገልግሎት የተደራጀውን የባለሙያዎች ቡድን በክላስተር በመከፋፈል የክትትል ሥራ መሠራቱንም አስረድተዋል።

በምርት ዘመኑ በዘርፉ ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ መሠራቱን የጠቀሱት ኃላፊው፤ "በክልሉ በሚሰበሰበው የስንዴ ምርት ከራሳችን ፍጆታ አልፈን ወደ ውጪ ለመላክ እንደ ሀገር የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ክልሉ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት እየሠራ ይገኛል" ሲሉ ገልጸዋል።

# ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በከተማዋ እንዲያፈሱ ጥሪ አቀረበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አልሚ ባለሀብቶች በከተማዋ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ የወረኢሉ ከተማ አስተዳደር ጥሪ አቀረበ። ከተማ አስተዳደሩ ከአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአዲስ አበባ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር ከወረኢሉና አካባቢው ተወላጅ ባለሀብቶችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር በከተማዋ ስላሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችና መልካም እድሎች ምክክር አድርጓል።

የወረኢሉ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ እሸቱ ታረቀኝ በምክክር መድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ ወረኢሉና አካባቢው ታሪካዊና በርካታ ሀብት የታደለ ቢሆንም አካባቢው ማደግ በሚገባው ልክ ሳያድግ ቆይቷል። ከተማ አስተዳደሩ ይህን ሁኔታ ለመቀየርና ከባለሃብቶች ጋር ተባብሮ አካባቢውን ለማልማት ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም በማኑፋክቸሪንግ፣ በከተማ ግብርና፣ በአገልግሎት፣ በማዕድንና በሌሎችም ዘርፎች ለሚሠማሩ ባለሃብቶች 175 ሄክታር መሬት መዘጋጀቱን በመጠቆም፤ ባለሀብቶች ወደ ከተማዋ ሄደው መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል።

የአካባቢውን እድገት ለማፋጠንና ሕዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የግድ ሀብታም መሆን አያስፈልግም ያሉት ከንቲባው፤ እውቀት ያለው በእውቀቱ፣ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ሀብት ያለውም ሀብቱን አስተባብሮ በጋራ መሥራት ብቻ እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

የአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአዲስ አበባ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ምትኩ በየነ በበኩላቸው፤ በከተማ አስተዳደሩ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በየደረጃው መሠራት ያለባቸው የቤት ሥራዎች እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

እንደ ክልል ውጤት የሚመዘገበው በየአካባቢው የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ተደምረው መሆኑን በማስታወስም፤ አቅም ያላቸው በየግላቸው ሌሎችም በጋራ በመሆን በታሪካዊቷ ወረኢሉ ከተማ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች ቢሮው አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

አማራ ክልል በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ሀብት አለው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ያለውን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የሕዝቡን ሕይወት ለመለወጥ መሥራት ይገባል። በተለይም በትብብር መሥራት የሚፈጥረውን ጠንካራ ሀብት ተገንዝበን በትብብር ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

በምክክር መድረኩ ላይ ተሳታፊዎች ቢስተካከሉ፣ መልስ ቢሰጥባቸው ያሏቸውን ሀሳቦች አቅርበው በከተማ አስተዳደሩና በማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

# ኢትዮጵያ የቪዛ ሥርዓቷን ለአፍሪካውያን ምቹ ማድረጓን የአፍሪካ ልማት ባንክ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የቪዛ ሥርዓቷን ለአፍሪካውያን ምቹና ቀላል በማድረግ የተሻለ ሥራ ማከናወኗን የአፍሪካ ልማት ባንክ አስታወቀ።

ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት ማለትም ከፈረንጆቹ 2016 እስከ 2022 ለአፍሪካውያን የቪዛ ሥርዓቷን በማቅለል በሯን ይበልጥ ክፍት በማድረግ እመርታ ማሳየቷን የአፍሪካ ልማት ባንክ በሪፖርቱ አመላክቷል። በአፍሪካ ጥቂት አገሮች በ2016 እና 2022 መካከል የቪዛ ሥርዓታቸውን በማቅለል ጎልተው መታየታቸውንም ባንኩ በሪፖርቱ ጠቅሷል።

እንደ ሪፖርቱ፥ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት የሌላ የአፍሪካ ሀገር ዜጋ ቪዛን መዳረሻ ላይ እንዲያገኝ በማድረግ አሊያም የኤሌክትሮኒክስ ቪዛ አማራጮችን ማቅረብ መጀመራቸውን ሪፖርቱ አያይዞ ገልጿል።

ከምሥራቅ አፍሪካ አገራት በተሻለ ደረጃ የቪዛ ሥርዓትን በማቅለል ረገድ ሪፖርቱ ኢትዮጵያን ተጠቃሽ አድርጎ አቅርቧል።

በዚህም እ.አ.አ. ከ2016 ጀምሮ በምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛ እመርታን ያስመዘገበችው ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ ለአፍሪካውያን ጎብኚዎች በራቸውን በተሻለ ክፍት ካደረጉ 20 ሀገራት መካከል 17ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ አመላክቷል።

ይህም የኮሮና ወረርሽኝን ተከትሎ በፈረንጆቹ 2021 ያጣችውን ደረጃ መልሳ እንድታገኝ እንዳስቻላት ነው የአፍሪካ ልማት ባንክ የገለጸው።

ከ2016 እስከ 2022 ከአህጉሪቱ የተሻለ የቪዛ ሥርዓታቸውን ለጎብኚዎች በማቅለል ቀዳሚ የሆኑ አራት ሀገራት የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ማለትም ቤኒን፣ ጋና፣ ናይጄሪያ እና ጋምቢያ መሆናቸው ተጠቁሟል።

የሀገራቱ የቪዛ ሥርዓትን ማሻሻል እና ማቅለል በአህጉሪቱ የንግድ ግንኙነትን እና የጉብኝት እንቅስቃሴ እንዲያድግ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ተገልጿል።

# በክልሉ በመስኖ ግብርና ከ10 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባሕር ዳር:- የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ በዘንድሮው የበጋ መስኖ ግብርና ከ10 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ለማግኘት አቅዶ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ። ክልሉ የዘንድሮውን የበጋ መስኖ ስንዴ ሥራ በደቡብ ወሎ ዞን አስጀምሯል።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ትናንት የበጋ መስኖ ሥራን በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ባስጀመረበት ወቅት የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኃይለማሪያም ከፍያለው እንደገለጹት፤ በክልሉ ከ250 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ ስንዴ በመሸፈን ከ10 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በቀጣይም አርሶ አደሩን የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን የቻለች ሀገር እንድትሆን የክልሉ ግብርና ቢሮ የድርሻውን ይወጣል ሲሉ ተናግረዋል።

የደቡብ ወሎ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አብዱ ሁሴን በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ ዞኑ በጦርነቱ ሳቢያ የተጎዳ በመሆኑ ምርትን በማሳደግ ኢኮኖሚውን ማነቃቃት ይገባል።

የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ ቢሮ ኃላፊ አሕመድ ጋሎ በበኩላቸው እንደገለጹት በዞኑ 42 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ ይሸፈናል። ከዚህም ከ1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዷል። ከዚህም ውስጥ 200 ሺህ ኩንታል ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው።

የለጋምቦ ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ መሐመድ ጋሻው በበኩላቸው በወረዳው 37 ቀበሌዎች 5 ሺህ 735 ሄክታር መሬት ላይ በመስኖ የስንዴ ልማት ሥራ እየተካሄደ ነው ብለዋል።

ስንዴ የማምረት ሥራን ከጀመሩ አራት ዓመት እንደሆናቸው የሚናገሩት የ 021 ቀበሌ አርሶ አደር ይማም እንድሬ የተሻለ ገቢ እያገኙ እንደሆነ ተናግረዋል።

ያም ሆኖ ግን የምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እጥረት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ አርሶ አደሮች የተሻለ ምርት እንዲያገኙ መንግሥት አስፈላጊውን እገዛ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል ሲል የዘገበው አሚኮ ነው።

# በኢትዮጵያና በአሜሪካ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ወሳኝ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች የአሜሪካ ኃላፊነት የጎላ እንደሆነም ተናግሯል።

የሁለቱ መሪዎች ግንኙነት ምዕራባውያን የኢትዮጵያን ሐቅ እንዲያውቁ ዕድል የፈጠረ ነው ያለው ጋዜጠኛው፤ ይህ ሲሆን ደግሞ እንደ አውሮፓ ኅብረት እና አሜሪካን የመሳሰሉ የምዕራባውያን ለጋሽ ድርጅቶች እጃቸውን መዘርጋት እንደሚጀምሩ ተናግሯል።

አሜሪካ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ጎራ ተሰላፊ ከሆኑት ሀገራት አንዷ እንደነበረች የተናገረው አሊሰቴር ቶምሰን፤ በአሁኑ ወቅት ግን ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ላይ እምነት እያሳደሩ ነው ብሏል።

በኢትዮጵያ ላይ የምዕራባውያን ግንዛቤ በእጅጉ የተዛባ እንደነበር ገልፆ፤ ባሁኑ ጊዜ አሜሪካም ሆነች ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት የያዙት ግንዛቤ የተሳሳተ እንደነበር ተረድተዋል ብሏል።


የተካሄደው የአሜሪካ አፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ አዳዲስ ለውጦች የታዩበት እና ለውጦች የተመዘገቡበት ስብሰባ ነው ሲልም አክሏል።

በያዝነው ሳምንት በተካሄደው ስብሰባ አሜሪካ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በግጭት ውስጥ በነበሩ የሀገሪቱ ሰሜናዊ አካባቢዎች የሰብዓዊ አቅርቦትን በማሻሻል እና መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማደስ ሰላም እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያደርገውን የማያወላውል ቁርጠኝነት አድንቃለች።

በተመሳሳይ የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ጆን ብሊንከን የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ በትግራይ ክልል ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሰብዓዊ አቅርቦትን ለማሻሻል እና አስፈላጊ አገልግሎቶችን ወደ ነበሩበት ለመመለስ የወሰደውን እርምጃ ማድነቃቸው የሚታወስ ነው።



ወይዘሮ ሂሩት ገብረሥላሴ



ኮሚሽነር ዘገየ አስፋው

# ኮሚሽኑ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት እንዳሉት፥ ኮሚሽኑ አካታችና አሳታፊ ምክክር የማካሄድ ኃላፊነት ስላለበት በየክልሎቹና በከተማ አስተዳደሮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ግብዓት የመሰብሰብ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ነው።

በዚህም ከፊል አዲስ አበባና ከፊል ኦሮሚያ ክልል ላይ ብቻ ባለድርሻ አካላትን አወያይቶ ግብዓት የመሰብሰብ ሥራዎች እንደቀሩ ጠቁመው፤ እነዚህም በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደሚጠናቀቁ አስረድተዋል።

ኮሚሽነር ዘገየ አስፋው በበኩላቸው፥ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያላት ሀገር እንደመሆኗ ሁሉም ማኅበረሰብ በተወካዮቹ በኩል እንደሚሳተፍም ነው የተናገሩት።

የባለድርሻ አካላትን አስተያየት በመሰብሰብና መተማመን ላይ በመድረስ ምክክር ከተካሄደ ቅቡልነት እንደሚኖረውም ጠቁመዋል።

የኮሚሽኑ አመራሮች አክለውም፥ ሙሉውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በምክክሩ ለማሳተፍ ስለሚያስቸግር ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተወከሉባቸው ተሳታፊዎች መረጣ ይካሄዳልም ነው ያሉት።

የተሳታፊዎች ውክልና እንደየክልሎቹና ማኅበረሰቡ ሁኔታ ዝርዝር መስፈርት እንዳለውና ሁሉም ማኅበረሰብ እንዲወከል የሚደረግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ምክክሩ በሁሉም ወረዳዎች ስለሚደረግ በልየታው ውስጥ ምንም ዓይነት ችኮላ ሳይኖር በጥንቃቄ ሁሉም ማኅበረሰብ እንዲወከል ይደረጋል ብለዋል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ ሁሉም ክልልና ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች እንዲሳተፉ ለማድረግ የተጠናከረ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

# «በሰሜኑ የነበረው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዶክተር አረጋዊ በርሄ እንደተናገሩት ስምምነቱ በጦርነቱ ምክንያት እጅግ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩት ለትግራይ፣ ለአማራና ለአፋር ሕዝቦች እጅግ ጠቃሚ ነው። ከስምምነቱም በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል በጦርነት ውስጥ ለነበሩት ሕዝቦች ትልቅ እፎይታም አስገኝቷል። የሰብዓዊ ርዳታ በስፋት መግባት ጀምሯል፤ የተቋረጡ መሠረተ ልማቶች ተጀምረዋል።በዚህም ሕዝቡ የሰላም አየር መተንፈስ ጀምሯል።

ሆኖም የኢትዮጵያ በሰላም ማደር የማይዋጥላቸው እና ከግጭት ማትረፍ የለመዱ አካላት ስምምነቱ መሬት እንዳይረግጥ ያደረጉት ሙከራ እየከሸፈ መሄዱን ሲረዱ ከሰሜኑ ክፍል ራቅ ብለው በአዲስ አበባና በወለጋ ሌላ የጦርነት ግንባር ለመክፈት ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ዶክተር አረጋዊ ጠቁመዋል።

በተለይ ወለጋ ላይ በሽብርተኝነት የተፈረጀው የሸኔ ቡድን በሕዝብ ላይ ግጭት እየፈጠረ እንደሚገኝና በአብዛኛው በአማራ ሕዝብ ላይ በማተኮርና ሃሳቡን የማይቀበሉ የኦሮሞ ልጆችን ጭምር በመጨፍጨፍ ጸረ ሕዝብነቱን እያሳየ መሆኑን ዶክተር አረጋዊ ተናግረው የሰሜኑ ጦርነት በሰላም መጠናቀቁ መንግሥት በቀጣይ ፊቱን ወደ ሸኔ በማዞር የቡድኑን ሕልውና እንደሚያከስመው ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ሸኔም ሆነ ሌሎች ጸረ ሰላም ኃይሎች ሕልውና የሚኖራቸው ሁከትና ብጥብጥ ሲነግስ መሆኑን የተናገሩት ዶክተር አረጋዊ የሰሜኑ ጦርነት በሰላም መጠናቀቁ ስጋት እንደፈጠረባቸውም አስረድተዋል።

ሰሞኑን ከሰንደቅ ዓላማ ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የተነሳው ግርግርም የዚሁ ቅጥያ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር አረጋዊ በርሄ፤ የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ የሚያጣላ እንዳልሆነና የሕዝቡም አጀንዳ አለመሆኑን አብራርተዋል።

ዶክተር አረጋዊ አክለውም በየቦታው የሚነሱት ሁከቶችና ብጥብጦች የኢትዮጵያን ሰላም መሆን የማይፈልጉና ከግጭትና ሁከት ለማትረፍ የሚጥሩ ፀረ-ሠላም ኃይሎች የሚያካሂዱት ሥራ መሆኑን ሕዝቡ ተረድቶ የሀገሩን ሰላም ነቅቶ ሊጠብቅ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አሁን በየቦታው የሚታዩ ችግሮችም ዘመናትን የተሻገሩና በአንድ ጀንበርም ሊፈቱ የማይችሉ መሆኑን የተናገሩት ዶክተር አረጋዊ ችግሮቹ በዘላቂነት ሊፈቱ የሚችሉትም በውይይት መሆኑን አስረድተዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# የፕላንና ልማት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር


ዶክተር ዳዲ ወዳጆ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 መሠረት ከተቋቋሙት ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ፕላንና ልማት ኮሚሽን አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶክተር ዳዲ ወዳጆ እንደሚገልፁት፤ በአዋጁ ክፍል አራት በተደነገገው መሠረት ኮሚሽኑ እንደሌሎች ተቋማት ስልጣንና ተግባራት ያሉት ሲሆን፤ የወል እና የተናጠል ሥልጣኖችም አሉት። በዛሬው ዕትማችን በአዋጁ ላይ በተቀመጠው አግባብ የተናጠል ሥልጣን እና ተግባራቱን የምንመለከት ይሆናል። ከተቋሙ ተግባራት መካከል የከተማውን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት፤አፈፃፀሙን መከታተል፤ ግብረ መልስ መስጠት፤ መገምገም ፤ መመዘን ፣ ደረጃ ማውጣት ፣ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ማዘጋጀት፤ ሲፀድቅ ደግሞ ተግባራዊ ማድረግ ይገኙበታል።

እንደ ዶክተር ዳዲ ገለፃ፤ ከተቋሙ ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ የአካባቢ ልማት ፕላን ማዘጋጀት፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል። እንዲሁም የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ፕላን ማዘጋጀት፤ ማጽደቅ እና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግን ያካትታል። ሌላው ተግባሩ ደግሞ የፕላን ዝግጅትና አተገባበር የጥናትና ምርምር ሥራዎች ማከናወን፣ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማቀነባበር እና ማሰራጨት ነው። እንዲሁም በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅትም የሕዝብ ተግባቦትና ስርፀት ሥራዎችን ያከናውናል፤ ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ስነዳና ስርጭት ቋት ያደራጃል፣ ጥቅም ላይም ያውላል።

ከተቋሙ ሥልጣንና ተግባራት መካከል የከተማው አስተዳደር ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ድጋፍና ምክር ይሰጣል ያሉት ዶክተር ዳዲ፤ በሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ከተማ ፕላኖች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፤ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የሴቶችንና የወጣቶች ጉዳዮች እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል በማለት ያስረዳሉ። የከተማ ፕላን በሚጥስ ማናቸውም አካል ላይ በሕግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድም ያደርጋል።

ከተቋሙ ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ የከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረታዊ የከተማ ካርታ ከሀገሪቱ ጂኦዴቲክ ካርታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤ የፀደቀ ፕላን በሕግ መሠረት እንደ የአግባቡ ያሻሽላል፤ ያጣጥማል። የፕላን፣ የዲዛይንና የግንባታ ፈቃድ ደረጃዎችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት እንዲያቀርቡና የመስክ ምልከታ እና ጥናት በማድረግ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የሚገልጹት ኮሚሽነሩ ፤ የከተማውን ዝርዝር የሥነ ሕዝብ ጥናትና ትንበያ ያካሄዳል፣ ውጤቱንም ለከተማው አስተዳደር አካላትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በከተማው ውስጥ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል ሲሉም ያብራራሉ።

ዶክተር ዳዲ እንደሚያስረዱት ተቋሙ በዝርዝር ከተሰጡት ሥልጣን እና ተግባራት መካከል የከተማውን ዓመታዊ አጠቃላይ የምርት ዕድገት ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት ዕድገት መነሻዎችን ይገምታል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል። የከተማውን የምርት ዕድገት ግቦች የፖሊሲና የሕግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንትና የወጪና የገቢ ንግድ ከተማ አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል። እንዲሁም ከአጠቃላይ ከተማ አቀፍ ምርት የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎት ዘርፎችና የከተማ ግብርና የተናጠል ድርሻን ይለያል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል። ከተማውን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል።

በተጨማሪም ተቋሙ ለሬዚለንስ ስትራቴጂ ትግበራ ከተለያዩ የሀገር ውስጥ፣ የክልል እና የውጭ ሀገር የግል ዘርፍ አካላት ጋር አጋርነትን ይመሠርታል፤ ለሁሉም ዘርፎች የሬዚሊየንስ ስትራቴጂ ለማስፈፀም አዋጭ ፕሮጀክቶችን ያሰናዳል፣ ለተፈፃሚነታቸውም ተዛማጅ የሆነ የገንዘብ ምንጭ መገኘቱንና ለታለመለት ዓላማ መሰራጨቱን ያረጋግጣል። በሬዚሊየንስ አግባብ ፍላጎት መርና ችግር ፈቺ የሆነ ጥናት የተፅዕኖ ዳሰሳ ከዩኒቨርሲቲ፣ ከምርምር ማዕከላትና ከሌሎች ትምህርታዊ አካላት ጋር በመተባበርም ያከናውናል። ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የሕግ ሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል። በአጠቃላይ ተዋረዳዊ አደረጃጀት ያላቸው የከተማው አስተዳደር አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ በየበኩላቸው የሚፈፅሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን አፈፃፀም መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን መከታተልም የተቋሙ ሥልጣን እና ተግባር መሆኑን ዶክተር ዳዲ ያመለክታሉ።


ዘመን ባንክ
Zemen BANK



የአድራሻ ለውጥ ማስታወቂያ

ዘመን ባንክ አ.ማ አዲስ ያስገነባውን ባለ 32 ፎቅ ዘመናዊ ህንፃ ማጠናቀቁን ለክቡራን ደንበኞች ፣ ለባለአክሲዮኖችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በታላቅ አክብሮት ያስታውቃል፡፡

የህንፃውን መጠናቀቅ ተከትሎ እስካሁን ሲጠቀምበት የነበረውን የዋና መስሪያ ቤት ህንፃ በመልቀቅ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ስራ ትምህርት ቤት ፊትለፊት ወደሚገኘው አዲሱ የዋና መስሪያቤት ህንፃ በቅርቡ የሚዘዋወር መሆኑን በደስታ ያበስራል፡፡

ክቡራን ደንበኞቻችንም አብራችሁን በመጓዝ ለዚህ ስኬት ላደረጋችሁት አስተዋጽኦ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

ዘመን ባንክ የላቀ አገልግሎት ማዕከል!

Follow Us on

## የዘመን እንግዳ

# ‹‹በመፅሐፍ ቅዱስ የሙስና መጥፎነት እና ሃጥያትነት በስፋት ተገልጿል››

*- ወንጌላዊ አዳነ ደቻሳ*
*በኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የሰላም ግንባታ መምሪያ ምክትል ኃላፊ*

ማህሌት አብዱል

**የዛሬው ‹‹የዘመን እንግዳችን›› ወንጌላዊ አዳነ ደቻሳ ይባላሉ። ትውልዳቸውም ሆነ እድገታቸው አርባምንጭ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዛው አርባምንጭ በሚገኘው ኃይሌ ደጋጋ እና አርባምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው የተማሩት። አዲስ አበባ ይገኝ በነበረው መሰረተ ክርስቶስ መፅሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በስነ መለኮትና በሰላም ግንባታ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ሰርተዋል። ሁለተኛ ዲግሪያቸውንም ኢቫንጀሊካል ሳይሆን ሲገስት ከተባለ የኢትዮጵያ ስነ-መለኮት ትምህርት ቤት አግኝተዋል። በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፒስ ኤንድ ሴኩሪቱ ዘርፍ ተጨማሪ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ተምረዋል። እንዲሁም በናይጄሪያ፣ በአውስትሪያ፣ ኒጀር፣ በሴኔጋልና ኬኒያ በመዟዟር የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስደዋል። የተለያዩ መንፈሳዊና ጥናታዊ ፅሁፎችንም በመፃፍ እና ተማሪዎችን በማማከር የበኩላቸውን ሚና ሲወጡ ቆይተዋል።**

**አርባ ምንጭ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጂንካና ወላይታ በሚገኙ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት መንፈሳዊ ትምህርቶችን በመስጠትና ወጣቶችን በማሰልጠን ለረጅም ዓመታት አገልግለዋል። አዲስ አበባ በሚገኘው የመሰረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፅሕፈት ቤት የወንጌል ትምህርት ክፍልን በማስተባበር ሰርተዋል። በተጨማሪ በመሰረተ ክርስቶስ መፅሐፍ ቅዱስ ኮሌጅና በተለያዩ መንፈሳዊ ተቋማት አስተምረዋል። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በመዟዟር በሰላም ግንባታ ስራ በስፋት ተሳትፈዋል። የአዲስ አበባ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ጸሃፊ ሆነው ለሶስት ዓመታት ያገለገሉት እንግዳችን ካለፉት ስምንት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የሰላም ግንባታ መምሪያ ምክትል ኃላፊ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ። በተጨማሪም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ተቋማት እየተጋበዙ የወንጌል ትምህርት ይሰጣሉ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከወንጌላዊ አዳነ ደቻሳ ጋር በፀረ ሙስና ትግሉ የሃይማኖት ተቋማት ሚና ዙሪያ ቃለምልልስ አድርጎ እንደሚከተለው ቀርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ሙስና ወይም ሌብነት ከመፅሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አኳያ ምን ይመስላል ?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** ሙስና እኛ ከምናስተምረው መንፈሳዊ ትርጉም አኳያ ስንመለከት የተበላሸና የተዋረደ ስነምግባር የጎደለው ተግባር ማለት ነው። ይህም ማለት ሌብነትን የሚፈፅም፤ ፍርድን የሚያጣምም፤ ህዝብን የሚጎዱ ነገሮች የመፈፀም ተግባርንም ይጨምራል። ከዚህ አንፃር ይህ ተግባር ተቀባይነት እንደሌለው ነው ቤተክርስቲያን የምታስተምረው። በነገራችን ላይ ‹‹ሙስና›› ስንል ብዙ ጊዜ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ጉቦ መቀበልና መስጠትን ብቻ ነው። ነገር ግን ሰው በአዕምሮ፣ በአስተሳሰቡ፣ በድርጊቱ ሙስና ሊፈፅም ይችላል። በጣም በብዙ መንገድ ልናየው እንችላለን። ነገር ግን የተዋረደ፣ የወረደ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው፤ ህዝብና አገርን እንዲሁም ራስንም ጭምር የሚጎዳ እንደሆነ ነው የምናስተምረው። ቅዱስ መፅሐፉም ይህንኑ ነው የሚናገረው።

በመፅሐፍ ቅዱስ የሙስና መጥፎነት እና ሃጥያትነት በስፋት ተገልጿል። ለምሳሌ በመፅሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 29 ቁጥር 4 ላይ ‹‹ንጉስ በፍርድ አገሩን ያፀናል፤ መማለጃ የሚወድ ግን ያፈርሰዋል›› ይላል። ከዚህ እንደምንረዳው ጉቦ የሚቀበሉ ባለስልጣናት በበዙበት አገር እንደሚፈርስ ነው። መሪ ጉቦ የሚቀበልና ፍርድ የሚያጣምም ከሆነ አገር አትቀጥልም። እንዲሁም ዘዳግም ምዕራፍ 16 ቁጥር 19 ላይ ‹‹ ፍርድን አታጣምም ፤ ፊት አይተህም አታዳላ፤ ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን ያሳውራልና የፃድቃንም ቃል ያጣምማልና ጉቦ አትቀበል›› በሚል መፅሐፍ ቅዱስ ለሁሉ ሰው ትዕዛዝ ያስተላልፋል። ይሄ ብቻ አይደለም፤ ዘዳግም ምዕራፍ 27 ቁጥር 25 ላይ ‹‹የንፁሑን ሰው ነፍስ ለመግደል ጉቦ የሚቀበል እርጉም ይሁን፤ ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይላሉ›› በማለት ያስቀምጣል። በነገራችን ላይ እዚህ ቃል ላይ ለማለት የተፈለገው ሰው መግደል ብቻ ሳይሆን ሰውን መጉዳትና ፍርድን ማጣመም፤ ፍትሕን ማዛባትንም የሚያካትት ነው።

በመሰረቱ ጉቦ ወይም ሙስና ስንል አንደኛ ያለአግባብ ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው። ይህም ግለሰብን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ህዝብ እና አገርን ይጎዳል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ሰው በእምነታችን ፊፅሞ የተወገዘና የተረገመ ነው ። በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንደተገለፀው በፅድቅ የማይመራ ንጉስ ባለበት አገር ቀውስ ይፈጠራል። ለምሳሌ መፅሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 15 ላይ የጉቦ ተቀባዮችን ድንኳን እሳት ትበላዋለች›› ይላል። ይህም የፈጣሪን ፍርድ ነው የሚያሳየው። አሁንም ብዙዎች ያልተገባ ሃብት ሰብስበው ሲያበቁ የሰበሰቡት ሃብት ሳይጠቀሙበት እንደጉም ሲበን እናያለን ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሰማይ ያያልና ይፈርዳል። በአጠቃላይ ጉቦ ዋና የሰውነት ክፍል የሆኑት አይንና ልብን ያጠፋል። አዕምሮን ያደነዝዛል። በመሰረቱ የአመለካከትና ስነ-ምግባር መበላሸትን ራሱ እግዚአብሔር የሚፀየፈው ተግባር ነው። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስም ወደ ምድር የመጣው ሰዎች ከገቡበት የተወረደ ማንነት ነፃ ለማውጣት እንደሆነ ግልፅ ነው። በአጠቃላይ መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉ ሃጥያትን ሰርቷል፤ ስለዚህ ሰዎች ከዚህ ለመውጣት የፈጣሪን ትዕዛዝ ማክበር እና እንደቃሉ መኖር ይጠበቅባቸዋል እያልን ነው የምናስተምረው። ንፁሃን በግፍ በሚበደሉበት እና በሚገደሉበት ምድር አማኞች ለፅድቅና ለእውነት እንዲቆሙ እንዲኖሩ ነው ግንዛቤ የምናስጨብጠው። ከመፅሐፍ ቅዱስ አንድ ጥቅስ ልጨምርልሽ፤ የሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 24 ላይ አንድ ፍሌክስ የተባለ ባለስልጣን ከእስር ቤት ሐዋርያው ጳውሎስን እያስጠራ ያመላልሰዋል። ግን አይፈታውም ነበር። ከብዙ መንከራተት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ ባለስልጣን በየጊዜው እያስጠራ ያመላልሰው የነበረው ገንዘብ መቀበል ፈልጎ እንደነበር ተረዳ፤ ሆኖም በአምላክም በሰውም ዘንድ አፀያፊ ተግባር በመሆኑ ጉቦውን ሳይሰጥ እንደቀረ ከዚህ ክፍል እንማራለን። ጉቦ ቢሰጥ ኖሮ ቶሎ ይፈታ ነበር፤ ግን ባለመስጠቱ በእስር ተንከራተተ።

ዛሬምበዚህባለንበትዘመንከሙስናየተነሳብዙየሚሰቃዩ ወገኖቻችን አሉ። በሃሰት የሚመሰክርባቸውም በርካታ ንጹሃን ናቸው። በአጠቃላይ በምድራችን እርኩሰትና ክፋቱ እጅግ እየጨመረ የመጣበት ጊዜ ነው። በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን ይህንን ችግር በመከላከል ረገድ ምሳሌ ሆና መታየት አለበት ብዬ አምናለሁ። ትውልዱን ከዚህ ችግር ለመታደግ ከሁሉ በፊት መታገል አለባት። መፅሐፍ ቅዱሳዊውን አስተምህሮ በግልፅ ማስተማር አለበት ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ሙስንና የመከላከሉ ኃላፊነት የማን ነው ብለው ያምናሉ?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** ሙስናን የመከላከሉም ሆነ ሙሰኞችን የማጋለጡ ኃላፊነት የሁላችንም ነው ብዬ ነው የማምነው። በተለይም ቤተ-እምነቶች ቅዱስ መፅሐፍት የሚያወግዙት ተግባር በመሆኑ ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው፤ መንግስትም መዋቅሩን ከሙስና ከማፅዳትና በዚህ ተግባር ላይ የተገኙትን በህግ ተጠያቂ የማድረግ ኃላፊነቱን መወጣት ይገባዋል።



ፎቶ፡ በአሸናፊ ጉደታ

> **በመፅሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 29 ቁጥር 4 ላይ ‹‹ንጉስ በፍርድ አገሩን ያፀናል፤ መማለጃ የሚወድ ግን ያፈርሰዋል››**

ይህ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የቤተሰብ መሪ በቤተሰቡ ውስጥ ለሚፈጠር ነገር ኃላፊነት መውሰድ አለበት። እኔ ልጆቼን ሳሳድግ ከፅድቅ እና ከእውነት ውጭ እንዳይሆኑ አድርጌ የማሳደግና የማስተማር ኃላፊነት አለብኝ። ከቤተሰቤ በአንዱ ላይ በሚፈፀም ማንኛውም መጥፎ ተግባር በዋናነት ተጠያቂ የምሆነው እኔ ነኝ። በአጠቃላይ ትውልዱ በስነምግባር የታነፀና ከሌብነት የፀዳ እንዲሆን ማስተማር ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ ነው የሚጀምረው።

ከዚህ አኳያ በየደረጃው ኃላፊነታችንን ተወጥተናል ወይ? ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። ‹‹አትስረቅ›› ብሎ የሚያስተምር የሃይማኖት መምህር ሰርቆ የሚገኝ ከሆነ የእሱ ተከታዮች ላይሰርቁ የሚችሉበት አግባብ የለም። በተለይም የእምነት አባቶች እንደሚያስተምሩት መኖር ካልቻሉ ለውጥ ሊመጣ አይችልም የሚል እምነት ነው ያለኝ። አሁን ላይ የምናውቃቸውና በማስረጃ ልንናገርባቸው የምንችላቸው ሙሰኞች ሳይቀሩ በየመገናኛ ብዙሀን ላይ የተለያዩ የሃይማኖት ሰዎች እና የመንግስት ባለስልጣናት ቀርበው ሲፎከሩ ይታያሉ። ሙስና አገር ያጠፋል ይላሉ፤ ነገር ግን እነሱ ራሳቸው በሙስና የተዘፈቁ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምሳሌነት የጎደላቸው ናቸው። እንደእኔ እምነት እንደዚህ አይነት ሰዎችን ማጋለጥ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ኃላፊነቱ የእያንዳንዱ ግለሰብ ነው። ልጆቼን በአግባቡ ማስተማር፤ ማሳደግና ለእነሱ ምሳሌ የመሆን ኃላፊነት የእኔ ነው። ፓስተሮች፤ ቄሶች እና ካህናት ለምዕመናቱ አርዓያ መሆን መቻል አለባቸው። ምሳሌ መሆን ከቻልን ኃላፊነታችንን ተወጥተናል ማለት ነው። ምክንያቱም ደግሞ የምንመራው ህዝብ ከፈጣሪ አደራ የተሰጠን በመሆኑ በንፅህና እና በእውነት ልንመራው

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ይገባል። በአደራ የተሰጠንን በአግባቡ የማናስተዳድር ከሆነ ግን ኃላፊነታችንን ባለመወጣታችን ከተጠያቂነት አናመልጥም። በምድርም ሆነ በሰማይ እንጠየቃለን። በመሆኑም ጤና ጥበቃ ባለሙያዎች ‹‹እያንዳንዱ ሰው ጊቢውን ካፀዳ አገር ንፁህ ትሆናለች›› እንደሚሉት እኛም ራሳችንን ከሙስና ብናፀዳ እና ለቤተሰብ አብነት መሆን ከቻልን አገርን ከሌቦች ፅዱ ማድረግ እንችላለን የሚል እምነት ነው ያለኝ። በአጠቃላይ ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ኃላፊነት ማፍራት የሁላችንም ነው። በይበልጥ የሃይማኖት መሪዎችና የመንግስት ባለስልጣናት ኃላፊነታቸውን ተገንዝበው አርዓያ መሆን መቻል አለባቸው ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ሙስናን ወይም ሌብነትን የሚያወግዙ የቀደሙ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ መምጣታቸው ይነገራል። በእርሶ እምነት ምንድን ነው ምክንያቱ? እነዚህን እሴቶች በመመለስ ረገድ የሃይማኖት ተቋማት ድርሻ ምን ሊሆን ይገባል?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** እንደእኔ እምነት እሴቶቻችን የተሸረሸሩት ግለኝነት እና ስግብግብነት እያደገ በመምጣቱ፤ ለሌሎች ማካፈል፤ ሌሎችን ማገልገል የሚለው አስተሳሰብ እየወረደ በመምጣቱ ነው። አሁን ላይ እኔነት እየጎላ ለአገርና ለህዝብ ማሰብ እየጠፋ የመጣበት ጊዜ ነው። በተለይም ምሳሌነት የጎደላቸው የሃይማኖት ሰዎች እየተበራከቱ መጥተዋል። እርግጥ ነው፤ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔርን የሚፈሩ እና በቅድስና የሚያገለግሉ አሉ፤ ይህ ጉዳይ እነሱን እንደማይመለከት እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። ይሁንና ከሚገባው በላይ ስግብግብ የሆኑ እኔነት የተጸናወታቸው፤ ራሳቸውን ብቻ የሚያጎሉ የእምነት መሪዎች እና ባለስልጣናት ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። እንደእውነቱ ከሆነ ወንጌላችን የሚያስተምረው እኛ ዝቅ ብለን እግዚአብሄርን ከፍ እንድናደርግ፤ ሌሎችን እንድናገለግል ነው። አሁን ግን የተገላቢጦሽ ነው የሆነው። ራሳቸውን የሚያገኑ ብዙ የቤተክርስቲያን ባለቤቶች አሉ።

እርግጥ ነው፤ መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሄር ናት፤ ግን በዚህ ዘመን ያሉ ብዙ ቤተክርስቲያናት ‹‹የእግዚአብሄር ናቸው›› ለማለት አልደፍርም። ብዙ የቤተክርስቲያን ባላባቶች እና ባለንብረቶች ሆነው ከህዝብ የሚገባውን ብር የሚቦጠብጡ፤ በዚያም ለራሳቸው አጃቢ የሚቀጥሩ የማይገባ ኑሮ የሚኖሩ በርካቶች ናቸው። አሁን ላይ ልቅነት ከመብዛቱ የተነሳ በምዕመኑ የሚደመጥ፤

> **አሁን ላይ እኔነት እየጎላ ለአገርና ለህዝብ ማሰብ እየጠፋ የመጣበት ጊዜ ነው።**

የሚገለፅ፣ ምሳሌ የሚሆን የሃይማኖት አባት ማግኘት አስቸጋሪ ነው። እዚህ ላይ ግን ጥቂትም ቢሆኑ በንፅህና የሚያገለግሉ የሉም እያልኩ እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። ግን ደግሞ ወንበዴዎቹ አገሪቱን በመቆጣጠራቸው ከዚህ ቀደም ተከባብረን የኖርንባቸው እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ መጥተዋል።

እንደእኔ እምነት በአሁኑ ወቅት ብዙ ቤተክርስቲያናት ላይ ያለው ሙስና ከሌላው አለማዊ ተቋም ያነሰ አይደለም። ምክንያቱም እነዚህ የእምነት ተቋማት ግብር የማይከፍሉ፤ ኦዲት የማይደረጉና ጠያቂ የሌላቸው በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ምሳሌነት የጎደለው ስራ በዝቷል። እርግጥ ድህነቱ እና የፖለቲካው አለመረጋጋት የየራሳቸው አሉታዊ ሚና ሊኖራቸው ይችላል። ስለሆነም ቤተክርስቲያን ለፅድቅ ለእውነት ጨክና የሙስና አፀያፊነት ማስተማርና ህዝቡን የሚበዘብዙ ሰዎችን ማጋለጥ እና ፅድቅ በሌለው መንገድ የተጓዙትን አይወክሉኝም ብላ በድፍረት ልትናገር ይገባል።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ህብረት ከዚህ ቀደም በሙስና ጥፋትና መንፈሳዊ እሴቶች ዙሪያ ሲያስተምርና ግንዛቤ ሲያስጨብጥ ቆይቷል፤ ግን ደግሞ ይሄ በቂ ነው ብዬ አላምንም። አሁንም ከችግሩ ስፋትና የእምነት ተቋማቱን እየፈተነ ያለ ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ በላይ በስፋት ሊሰራበት ይገባል የሚል እምነት ነው ያለኝ። በነገራችን ላይ ሙሰኝነትና ሙሰኞችን ባጋለጡ መሪዎቻችን ላይ ብዙ ነቀፋ እንደደረሰ አውቃለሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ምሳሌ ላንሳ፤ የቀድሞ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አሁን ደግሞ ሰላም ሚኒስቴር የሚባለው ተቋም የነበሩ አመራሮች አንድ ወቅት ላይ ጠርተውኝ ‹‹እናንተ የእምነት አባቶች ፅድቅን እና እውነተኝነት ታስተምራላችሁ ብለን ስንጠብቅ የእናንተ ፓስተሮች ሰራተኞቻችንን ጉቦ አስተማሩብን›› የሚል ቅሬታ አቀረቡ። እንዴት ብዬ ስጠይቅ ፍቃድ ለማግኘት ብለው ጉቦ እንደሚሰጡ፤ በዚህ የተነሳ ለእነዚህ ቤተክርስቲያናት ፈቃድ የሚሰጠው ክፍል ላይ ሁሉም ሰራተኛ ለመመደብ እንደሚሯሯጡ ነው የነገሩኝ። ይሄ ነገር እንደአንድ የእምነት አባት ክፉኛ አስደንግጦኛል፤ አሳፍሮኛልም።

ስለዚህ አሁንም ችግሩ ያለው በአጠቃላይ የእምነት ተቋም ውስጥ በመሆኑ መንፈሳዊ ድርጅት ነው በሚል ብቻ ልቅ ከመልቀቅ ይልቅ አሰራሩን የሚፈትሽ ስርዓት መኖር አለበት ብዬ አምናለሁ። ይህም ደግሞ ምዕመኑን ከጉዳት የሚያድን ብቻ ሳይሆን አገርን ከስጋት የሚታደግ በመሆኑ የሚመለከተው አካል ሊያስብበት ይገባል። በአጠቃላይ አሁን ለወደቅንበትና እሴታችንን ለተሸረሸረበት ምክንያት ከቤተሰብ ጀምሮ የእምነት ተቋማቱ እና መንግስት የየራሳቸውን ኃላፊነት መወጣት ባለመቻላቸው እንደሆነ ነው የማምነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሃብት እያፈሩ ያሉትን የእምነት ሰዎች በመመለስ እና ምዕመናኑን በማስተማር ረገድ የእምነት ተቋማት ሚናቸውን ምን ያህል ተወጥተዋል? በተለይ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ስር ያሉ ተቋማት ላይ ያለውን አሰራር ያብራሩልን?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ህብረት ውስጥ በርካታ ቤተክርስቲያናት ናቸው ያሉት፤ በዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ ጥረት የምናደርገው በተለይ የእምነት መሪዎቹ በእውነትና በፅድቅ እንዲኖሩ ነው። አለማወቅ ጥፋት ውስጥ እንደሚከት የምንረዳ በመሆኑ ህብረቱ ግንዛቤ ማስጨበጡ ላይ ነው ትኩረት የሚያደርገው። በመሆኑም አገልጋዮች መፅሐፍ ቅዱስ ተሸክመው የሚሄዱ ብቻ ሳይሆኑ የሚያነቡ፤ እንደቃሉ የሚኖሩ እንዲሆኑ በማስተማር የራሳችንን ጥረት እናደርጋለን። ግን ፈታኙ ጉዳይ ደግሞ ሌላው የእምነት አባት ተቃራኒ የሆነ እና ሁሉም በነፃነት ያለአንዳች ኃላፊነት እንዳይኖር የሚያደርግ አስተምህሮ ለምዕመኑ የሚሰጥ መሆኑ ነው።

ያም ቢሆን ግን ህብረቱ ጉዳዮን በጥንቃቄ ስለሚያየው በስፋት ነው እየሰራንበት ያለው። ሙስና ላይ የተዘጋጁ ትምህርቶች ይሰጣሉ፤ አንዳንድ ጊዜ በሙስና ላይ ተዘፍቀው የሚገኙ ሰዎች ወደ ኃላፊነት እንዳይመጡ ይደረጋል። ምክንያቱ ደግሞ ለሌሎች ምሳሌ ስለማይሆኑ ነው። አልፎ አልፎ ተመክረው፤ ተገስፀው ሊመለሱ ያልቻሉትን አገልጋዮች በይፋ ለህዝቡ የማጋለጥ ስራ ይሰራል። ይሁንና የተሰራው ሥራ በቂ ነው ብዬ አላምንም። በጣም የሚያሳዝነው አንዳንዱ ሰው ገንዘብ መጠቀሚያ ከማድረግ ባለፈ የገንዘብ ባሪያ ሲሆን ይታያል። በዚህ አስተሳሰቡ ምክንያት ቤተክርስቲያንና ምዕመናን ይጎዳል። በአጠቃላይ ከጥያቄው አንፃር ጥረት እያደረግን ነው፤ ግን ደግሞ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ብዬ ለመግለፅ እወዳለሁ። ሆኖም ግን ከዚህ ጥረታችን በተቃራኒ የቆሙ ዝም የተባሉ አሉ፤ የየራሳቸውን ቤተ-እምነት ከፍተው ሁነኛ የገቢ ምንጭ አድርገው የቀጠሉ አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የእምነት ተቋማት ከሙስና የፀዱ እንዲሆኑ ማስተማሩ ብቻ ውጤት ያመጣል ብለው ያምናሉ?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** በመሰረቱ ይህ ጉዳይ በወንጌላውያን በኩል ይታወቃል፤ መንግስት ስላለው ሳይሆን የማስተማሩ ነገር የእምነት ተቋማቱም ኃላፊነት ስለሆነ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጥረት ይደረጋል። ግን ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል ብዬ አስባለሁ። አሁንም ግን ሁሉንም በደምሳሳው እንዳልጨፈልቅ ስጋት አለኝ። አሁን ላይ በታሪክ ሰምተን በማናውቀው ሁኔታ ሁሉንም መንፈሳዊ አገልግሎት ለጥቅማቸው የሚያውሉ በመኖራቸው ነባራዊ ሁኔታው ችግር ያለበት መሆኑ አሳሳቢ ነው ባይ ነኝ። ከተሰራው ስራ ይልቅ በአብዛኛው ችግሩ ጎልቶ ይታያል። አስቀድሜ እንዳልኩት በዚህ ውስጥ ነፍሳቸውን የሚያስጨንቁ በርካቶች ናቸው።

በአጠቃላይ ስርዓቱ በሌብነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ከችግሩ ለመውጣት አደጋች ሆኗል። ለምሳሌ አንድ የቤተክርስቲያን መጋቢ የሆነ ሰው የጊቢውን አጥር ለማጠር ፈልጎ ፈቃድ ሲጠይቅ ጉቦ ይጠየቃል፤ አሻፈረኝ ቢልም ከላይ እስከታች ያለው አመራር በዚህ ስርዓት ውስጥ የተዘፈቀ በመሆኑ እና ሰሚ ባለማግኘቱ ባያምንበትም ጉቦ ለመስጠት መገደዱን አጫውቶኛል። ከዚያ ሰው ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ተጋጭተናል። እኔ ብሆን እድሜ ልክ ሳይታጠር ይቅር እንጂ የእምነት አባት ሆኜ እንዲህ አይነት ነገር ውስጥ አልገባም ነበር ብዬ ብዙ ተሟግቼዋለሁ። ስለዚህ ይህ የሚያሳይሽ አንዳንድ ሰዎች ተጎትተው ወደዚህ ስርዓት የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩን ነው። ይህም ቢሆን ግን ችግሩን መናገርና ማስተማር ብቻ ሳይሆን እኛ ራሳችን ምሳሌ መሆን መቻል አለብን። ሁላችንም ከቤታችን ጀምሮ አገር ከሙስና እንዲፀዳ ኃላፊነታችንን መወጣት አለብን። በአጠቃላይ ካሉት ችግሮች የተነሳ ጥሩ ነገር ላይ ነን ብዬ በድፍረት መናገር አልችልም።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** በእኔ በኩል መናገር ወይም ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ሙስና ከሃይማኖት ያፈነገጠ፤ እግዚአብሄር የሚያዝንበት፤ ሌሎች ሰዎች የሚጎዱበት ስለሆነ ከዚህ ተግባር ሁሉም ራሱን እንዲጠብቅ ነው። ሙስና ብዙ መልክ አለው፤ በአዕምሯችን በልቦናችን ሰርቀን እንዳንገኝ መጠንቀቅ ይገባናል። ምክንያቱም ድርጊታችንን ብቻ ነው ሰው ሊያይ የሚችለው፤ ፈጣሪ ግን የልባችንን ሃሳብ ይመረምራልና ከእሱ ፍርድ ልናመልጥ ስለማንችል እንጠንቀቅ የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ሁሉን በሚያይ በእግዚአብሔር ፊት ኑሯችን የሚያሳዝን እንዳይሆን እንጠንቀቅ። በሌላ በኩል ለእውነት ብቻ ለመኖር መዘጋጀት አለብን የሚል እምነት አለኝ። ብዙ ጊዜ እውነት ዋጋ ያስከፍላል፤ ሰው ሁሉ ከሃሰት ጋር ስለወገነ ብለን መፍራት የለብንም። ከዚህ ይልቅም ብቻችንም ብንቀርም እውነት ከመናገር ልንታቀብ አይገባም። የውሳኔ ሰዎች እንሁን። የምንናገረውን እንኑር። በተለይ በሌብነትና በጉቦ የተዘፈቁ ሰዎችን ልንታገል ይገባል። መፅሓፍ ቅዱስም እውነትን በፍቅር ግለፁ ነው የሚለው። ሁላችንንም ይህንን የማድረግ ኃላፊነት አለብን፤ ከመጥፎ ህይወት እንውጣ። እንደዚያ ከሆንን አገራችን እናድናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ወንጌላዊ አዳነ፡-** እኔም እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## "ስነ ምግብ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አገርን መገንባት ነው"

*- ዶክተር አረጋሽ ሳሙኤል*
*የምግብ ሳይንስና የስነ ምግብ ከፍተኛ ተመራማሪ*

አፀገነት አክሊሉ

ሳይንስ እንደሚለው የተስተካከለ አመጋገብ ስርዓት ያለው ህብረተሰብ አምራች ይሆናል። ስርዓተ ምግብ ደግሞ የተመገብነውን ምግብ በስነህይወታዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ሂደቶች በማለፍ በአጠቃላይ ሰውነታችን፤ በአሰራርና በሰውነት ግንባታ ዙሪያ እድገት ማምጣት ነው። እነዚህ ንጥረ ምግቦች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን፤ ዋና እና ንዑስ ይባላሉ። ዋና ንጥረምግቦች የሚባሉት ማንኛውንም ፍጥረት በብዛት ኃይል የሚሰጡትና የሰውነታችንን ስርዓተ ኡደት በትክክል እንዲሰራ የሚረዱ ናቸው። ንዑስ ንጥረ ምግቦች ደግሞ ስርዓተ ዑደቱ እንዲካሄድ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት ናቸው። ሁለቱም ዓይነት ንጥረ ምግቦች ከአካባቢያችን ይገኛሉ።

የሰውነታችን ሙቀት በመጠበቅ፤ በመገንባትና የተጎዱ አካላት በመጠገን ኃይል የሚሰጡ ናቸው። ለመሆኑ ስርዓተ ምግብ ማለት ምን ማለት ነው? በአገራችን ያለው ሁኔታስ ምን መልክ አለው? ከተባለ መልሱን በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና የስነ ምግብ ከፍተኛ ተመራማሪ እንዲሁም ብሔራዊ የስነ ምግብ መረጃ ማዕከል የኢትዮጵያ አስተባባሪ ከሆኑት ዶክተር አረጋሽ ሳሙኤል ጋር ቃለ ምልልስ አድርገናልና እንደሚከተለው እንመልከተው።

**አዲስ ዘመን ፦ ስርዓተ ምግብ ማለት ምን ማለት ነው?**

**ዶክተር አረጋሽ ፦** ስርዓተ ምግብ ጥሩና መጥፎ በሚል በሁለት ይከፈላል። ጥሩ ስርዓተ ምግብ ማለት ተመጣጣኝና በቂ የሆነ ምግብ መመገብ ማለት ነው። በቂ ሲባል ግን ሁልጊዜ አንድ አይነት ምግብ እየተመገብን የሚበቃኝን አገኛለሁ ማለት አይደለም። ከሁሉም አይነት ተመጣጣኝ ምግቦችን ማግኘት የግድ ነው። የምግቡን ተመጣኝነት ለመጠበቅ ደግሞ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም እንቅስቃሴ አንዱ የስርዓተ ምግብ አካል ነው። በጠቅላላው ጥሩ ስርዓተ ምግብ የሚባለው በመጠኑ በቂ፣ በይዘቱ ደግሞ የተመጣጠነ ምግብ መውሰድ ማለት ነው።

በሌላ በኩል ጥሩ ያልሆነ ስርዓተ ምግብ ደግሞ ሶስት ዓይነት ነገሮች አሉት። እነዚህም ከላይ ጥሩ ስርዓተ ምግብ ብለን ያነሳነውን በቂና ለሰውነት ግንባታ ኃይል መስጠት ብሎም ሌሎች ተጨማሪ አቅሞችን የሚፈጥሩ ምግቦችን ያልያዘ ዝም ብሎ ለረሃብ ማስታገሻ ብቻ የሚበላ ማለት ነው። እዚህ ጥሩ ያልሆነ ስርዓተ ምግብ ውስጥ የበዛ ከሚፈለገው መጠን እልፍ ያለ አመጋገብ ማለት ነው።

ሌላው እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነገር ደግሞ ሰዎች ምግብ ይመገባሉ በገጽታቸውም ላይ እጥረትም ሆነ ሌላ ነገር አይታይም። ነገር ግን ውስጣቸው ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ሲያጡ ማለት ነው። ይህ በራሱ ጤናማ ያልሆነ የስርዓተ ምግብ አካሄድ ነው። **ለምሳሌ፡-** ደም ማነስ ያለበት ሰው አልጋ ይዞ አይተኛም፤ ስራ ይሰራል፣ ይማራል ነገር ግን ውስጡ ያለው የደም ዝውውር በቂና በተገቢው ልክ አይደለም። እንደዚህ ዓይነቶቹ ችግሮችም ጤናማ ካልሆነ የአመጋገብ ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ናቸው።

**አዲስ ዘመን ፦ ስርዓተ ምግብ ለእከሌ ያስፈልጋል የሚባል ነው ?**

**ዶክተር አረጋሽ ፦** ስርዓተ ምግብ ለሁሉም ሰው የሚያስፈልግ ነው። ነገር ግን ማነው የበለጠ ተጠቂ ሊሆን የሚችለው ብለን ከተነሳን ከሁለት ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ተጋላጭ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። ስለዚህም ለእነሱ በተለየ ሁኔታ ያስፈልጋል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ፡- አንድ ህጻን ከጽንሱ ጀምሮ ተወልዶ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ጊዜ ድረስ ያሉት 1ሺህ ቀናት በርከት ያለ ተመጣጣኝ ምግብ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። እናም ለአንድ ሰው የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ተዘጋጅተው፣ አድገው የሚያስፈልጋቸውን ይዘት አሟልተው የሚገኙበት በመሆኑ በእነዚህ ጊዜያት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል። ስለዚህም የተለየ ለእከሌ ያስፈልጋል ወይ ላልሽው መልሱ የተመጣጠነ ምግብ ለሁሉም የሚያስፈልግ ቢሆንም በተለይ ከጽንስ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያልሞላቸው ልጆች በጣም ያስፈልጋቸዋል።

በሌላ በኩልም ነፍሰ ጡርና የሚያጠቡ እናቶች ከማንም በላይ የተመጣጠነ ምግብ ተመጋቢ ሊሆኑ ይገባል። ምክንያቱ ደግሞ እነሱ የሚመገቡት ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን በሆዳቸው ላለው እንዲሁም ወልደው እያጠቡት ላለው ልጅ ነው።

ሌላው ወጣት ሴቶች ናቸው። ከሌላው በተለየ ሁኔታ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ያለባቸው። ዋናው ምክንያት ደግሞ እነዚህ ሴቶች በወር አበባ ጊዜ የሚያጡት ንጥረ ነገር አለ። ይህ ንጥረ ነገር ሊተካ የሚችለው ጥሩ የሆነ የስርዓተ ምግብ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ከሆነ ብቻ ነው። ጥሩ የሆነ የስርዓተ ምግብ ሂደት ከሌላቸው በተለይም አርግዘው ለመውለድ ሲያስቡ ራሳቸው ብቻ ሳይሆን የሚያረግዙትና የሚወልዱት ልጅም የተጎዳ ይሆናል። በመሆኑም በመውለድ እድሜ ላይ ያሉ ሴቶች ተገቢነት ያለው ስርዓተ ምግብ ሊከተሉ ይገባል። ነገር ግን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተሟላ የስርዓተ ምግብ ሊኖረው ይገባል።



ሳይንስ እንደሚለው የተስተካከለ አመጋገብ ስርዓት ያለው ህብረተሰብ አምራች ይሆናል

**አዲስ ዘመን፦ ሁሉም ሰው የተስተካከለ ስርዓተ ምግብ አካሄድን ይከተል ዘንድ ምን አይነት ምግቦች ምንጮቹ ሊሆኑ ይገባል?**

**ዶክተር አረጋሽ፦** በባህላችን ሁልጊዜ ስጋ የሚመገብ ሰው ሰውነቱ ሞላ ያለ ሰው ነው። ከጤነኛ ብሎም የተመጣጠነ ምግብ ካገኘ በጠቅላላው ከተመቸ ኑሮ ጋር የምናያይዘው። ይህ ግን ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው። በአጭሩ ለተሟላ የስነ ምግብ ሂደት የሚረዱ የምግብ አይነቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዳጉሳ፣ ገብስ እና ሌሎችም የእህል ዘሮች ሲሆኑ፤ በጥራጥሬው ምድብ ደግሞ ሽምብራ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ማሾ፣ ምስርና ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ወተትና የወተት ተዋጽዖ የአሳ ስጋ፣ የበሬ ስጋ፣ የዶሮ ስጋና ሌሎችም እንዲሁ ወሳኝ ምግብ ናቸው። እንቁላልና በአትክልት ዘርፍ ቢጫና ብርቱካናማ ቀለም ያላቸው የምግብ አይነቶችን መመገብ የተሟላ ስነምግብ እንደተከተልን ማሳያዎች ናቸው።

ቀለል ባለ መልኩ ስንገልጸው ግን አንድ ሰው እዚህ ከተዘረዘሩት መካከል በቀን የተወሰኑትን እንኳን ቢያገኝ መልካምና ተገቢ ነው። ቀላል ምሳሌ ብነግርሽ የተለመደው የምንበላው በየዓይነቱ እንኳን ከሞላ ጎደል እህሉንም ጥራጥሬውንም ይይዛል። ስለዚህም እዛ ላይ አንድ ሙዝ ወይም ሌላ የፍራፍሬ አይነት ብንጨምርበት የሚያስፈልገንን የተመጣጠነ ምግብ አገኘን ማለት ነው።

ሌላውና ትልቁ ነገር ውሃ ሲሆን፤ ብዙ ሰው የሚቸገርበትም ነው። ነገር ግን የተሟላ የስነምግብ ስርዓትን ተከተልን ማለት ውሃ የመጠጣት ልምዳችንን ማዳበር ስንችል ነው። በህክምናውም በሳይንሱም የሚመከረው በቀን ቢያንስ ከስምንት እስከ 10 ብርጭቆ ውሃ መጠጣት ያስፈልጋል። ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ በሰውነታችን ውስጥ የሚፈጠር ድርቀትን ይከላከላል። የምግብ ዝውውርን ያፋጥናል፤ ሰውነት በስራም ሆነ በተለያዩ ነገሮች እንዳይደክም ይልቁንም እየታደሰ እንዲሄድ ያግዛል። ነገር ግን ሁልጊዜ ስጋ ቅባት የበዛበት እንዲሁም አቅም የሚጠይቁ ምግቦችን መመገብ ወሳኝ አይደለም። እንደውም እነዚህ ምግቦች ሲዘወተሩ የተለያዩ ችግሮችን ይዘው ይመጣሉ። ስለሆነም የተመጣጠነ የሚለውን መለየት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፦ የስነ ምግብ ስርዓታችን መዛባቱ ወይም ደግሞ በሚመከረው መጠን አለመጠቀማችን የሚያስከትለው ጉዳትስ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር አረጋሽ፦** ብዙ የስነ ምግብ ተመራማሪዎች እንደሚሉት አገራችን ላይ መቀንጨር በጣም የሚታይ ችግር ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉና እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ መቶ ህጻናት መካከል 37ቱ ለእድሜያቸው የሚገባቸውን ቁመት የያዙ አይደሉም። ወይም ደግሞ የሚቀነጭሩ ናቸው። ልጆች ሁለት ዓመት እስከሚሆናቸው ድረስ የጭንቅላታቸው፣ የሰውነታቸው እንዲሁም የሴሎቻቸው እድገት የሚፈጠረው በወቅቱ በሚገባቸው መልኩ የስርዓተ ምግብ ስርዓትን ባለመከተላቸው ነው። ይህ ደግሞ ምርታማነታቸው ይቀንሳል፤ በትምህርት ደካማ ይሆናሉ፤ በማህበራዊ ግንኙነታቸውም የተጎዱ ነው የሚሆኑት። ስለዚህ የስርዓተ ምግብ መጎዳት ችግሩ ዘርፈ ብዙ ነው። እናም ከጅምሩ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

ችግሩ ዘርፈ ብዙ መሆኑን የሚያሳየው አንድ ጽሁፍ አለ። እሱም "ለስነ ምግብ አንድ ዶላር ማዋል 16 ዶላር ያተርፋል" የሚል ነው። እኛም ለመንግስት አካላትና ለውሳኔ ሰጪዎች ማሳሰብ የምንፈልገው ስነ ምግብ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አገርን መገንባት ነው። በመሆኑም ስርዓተ ምግብ ላይ መንግስታት ኢንቨስት ሊያደርጉ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፦ እንደ አገር በስነ ምግብ ስርዓት ዙሪያ ያለንበት ደረጃ ምን ይመስላል? ችግሩንስ ለማስተካከል ምን መሰራት አለበት?**

**ዶክተር አረጋሽ ፦** አገራችን ጥሩ ያልሆነ አመጋገብ ስርዓት ተጠቂ ናት። ይህም ማለት በአላስፈላጊ ሁኔታ የሚበዛ የስርዓተ ምግብ ስርዓት ዝቅተኛ የምግብ ስርዓት እንዲሁም ድምጽ አልባ (ሂድን ) የስነ ምግብ ስርዓት አለባት ማለት ነው። ይህንንም ለመከላከል ሁላችንም የራሳችን አስተዋጽኦ ሊኖረን ይገባል።

እንደአገር ያለንበት ሁኔታ ከባድ ነው። ከመቶ ህጻናት 37ቱ ለሰውነታቸው የሚገባቸውን ቁመት የያዙ አይደሉም። በሌላ በኩል ደግሞ ከኪሎ በታች ያሉት 24 በመቶ ናቸው። መቀንጨር በስፋት የሚታየውም ለዚህ ነው። መቀጨጭ ደግሞ ለሰውነታቸው የሚገባቸውን ክብደት አለመያዝና ደማነስ ጎልተው በአገር ደረጃ የሚታዩ የስርዓተ ምግብ ውስንነታችን ያመጣብናል። እናም ይህንን አስቦ መንቀሳቀስ ይገባል። ሁኔታውን ለመቀየር ደግሞ ሁሉም ኃላፊነት አለበት።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ በስርዓተ ምግብ ችግር የተጠቁ ህጻናት ድምጽ አልባ ናቸው። በመሆኑም መገናኛ ብዙኃኑም ባለሙያውም የሚያውቀውን ሁሉ ለህብረተሰቡ ማስተላለፍ ይገባዋል። ውሳኔ ሰጪዎች ደግሞ ኢንቨስትመንትን ሲታቀዱ፣ በጀት ሲመደብ ይህንን ያካተተ ማድረግ ይገባቸዋል። ከዚያም አለፍ ብለው ትኩረት የሰጠ እንዲሆን መገፋፋት አለባቸው። ምክንያቱም ትርፉ ቀላል ስላልሆነ። በጠቅላላው ጤናማ ዜጋ እንዲኖረን ከፈለግን ሁሉም የድርሻውን ይወጣ እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፦ ለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር አረጋሽ ፦** እኔም አመሰግናለሁ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “ወርቃማዎቹ እሴቶቻችን ስለምን ደበሱብን?”

**በቅድሚያ፤-**

ጥንታውያኑ ግሪካውያን ፈላስፎች የአደባባይ እሰጥ አገባ ሙግታቸውን ከመጀመራቸው አስቀድሞ “በመጀመሪያ በቃሉ ትርጉም እንስማማ” ይሉ እንደ ነበር በብዙ ድርሳናት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ይህንን መልካም መርህ ለጽሑፋችን ግብዓትነት ብንጠቀምበት መልካም መስሎ ስለታየን የብዕረ መንገዳችንን ጉዞ የምንጀምረው በርዕሳችን ውስጥ ለተጠቀሱት “**ወርቅ**” **እና** “**ደበሰ**” ለሚሉት ሁለት ጽንሰ ሃሳቦች ተገቢውን የማብራሪያ መደላድል በማኖር ይሆናል።

**የወርቅ ወግ፤-**

“ወርቅ” የተሸከመው እሴትና ምሥጢረ ሃሳብ ከዕለት ተዕለቱ ምልከታችንና ከአዘቦት ቀን የተለምዶ ወጋችንና ከጌጥነቱ በእጅጉ የላቀና የመጠቀ ነው። ወርቅ ማጌጫና መዋቢያ ብቻም አይደለም። ወርቅ የሀብት፣ የስኬት፣ የክብር፣ የገዢነት፣ የቅንጦት፣ የዝና፣ የመልካም ባህርይ፣ የጉብዝናና የብርታት ወዘተ. ወካይም ጭምር ነው።

በወርቅ ዙሪያ የተንዠረገጉት እነዚህን መሰል ሽሽግ ትርጉሞች በተለምዶ በምናውቃቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ሃይማኖታዊ የማሕበረሰብ ተቋም ውስጥ ተሰግስገው ያሉና እንደ አእማድ የሚቆጠሩ እሴቶች ጭምር ናቸው። ወርቅ የገዢነትን ክብር ይወክላል ስንል የፖለቲካዊውን ባህርይ ማጣቀሳችን ነው። የነገሥታት በትረ ሥልጣን የሚወከለው፣ ዘውዳቸውም የሚንቆጠቆጠው በወርቅ ነው።

ሰብአ ሰገል ለሕጻኑ ክርስቶስ ካመጡለት ስጦታዎች መካከል አንዱ የስጦታ ዓይነት ወርቅ መሆኑ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ የታወቀ ነው። “ስለምን ወርቅ አመጡለት?” ተብሎ ሲጠየቅ “የክርስቶስን የሉዓላዊነት ሥልጣነ መንግሥት ስለሚወክል ነው” በማለት የሃይማኖቱ መምህራን ማብራሪያውን ይሰጣሉ።

የአንድ አገር ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጡንቻ መፈርጠሙ የሚረጋገጠው አገረ መንግሥቱ ባለው የወርቅ ሀብት ክምችት መጠን መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ምስክርነት ይሰጣሉ። ይህ እውነታ የወርቅን፣ የኢኮኖሚውንና የፖለቲካውን ጠንካራ ትሥሥር በሚገባ የሚያመለክት ነው። የመሠረታዊ ሸቀጦች ውድነት የሚገለጸውስ “ልክ እንደ ወርቅ ዋጋው ሰማይ ደርሷል” እየተባለም አይደለም።

በዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮች ላይ ለአሸናፊዎች የሚበረከተው የወርቅ ዋንጫ ወይንም ሜዳሊያ መሆኑስ እርግጥ አይደል። ለጦር ሜዳ ጀግኖችና በተለያዩ ዘርፎች አገራዊ ስኬት ባስመዘገቡ አርአያ ግለሰቦች ደረት ላይ በክብር የሚቀመጠው ሽልማትና ማድነቂያው ኒሻንስ “የወርቅ” የሚል ቅጽል ታክሎበትም አይደል። እነዚህና ሌሎች በርካታ መሰል ሽልማቶች ከማሕበራዊው ዘርፍ ጋር በሚገባ የሚጠቆሙ ናቸው። በባህርይው ሸጋ የሆነ ሰው ሲሞካሽስ “አመሉ ወርቅ ነው” እየተባለ መሆኑስ መች ይጠፋናል።

የወርቅ መገለጫ ቀለማት ብዙዎቻችን እንደምናስበው ቢጫው ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉ ናቸው። ነጭ፣ ቀይ፣ ሮዝ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ ወዘተ. እየተባሉ ልክ እንደ ቀስተ ደመና በበርካታ ሕብረ ቀለማት እንዲሚታወቁ የዘርፉ ተመራማሪዎች በየጥናታቸው ማረጋገጫውን ሰጥተዋል። የወርቅ ደረጃ የሚመደበውም ካራት በተባለ መስፈርት እየተለካ 10፣ 14፣ 18፣ 24 ወዘተ. በሚሉ ቁጥሮች ውቅልና መሆኑም ይታወቃል። በአጭሩ ወርቅ ከይዘቱ በተጨማሪ የያዘው ምሥጢራዊ ፍች ልክ እንደ ማዕድን ሥፍራዎች እጅግ የጠለቀና የረቀቀ እንደሆነ አስታውሶ ማለፍ ይቻላል።

ወደ አገራዊ ሥነ ቃሎቻችንና ትውፊቶቻችን መለስ ስንልም በብሂሎቻችን፣ በተረታ ተረቶችም ሆነ በፈሊጣዊ አጠቃቀሞቻችን ውስጥ ወርቅ ተደጋግሞ መነሳቱ የተለመደ ነው። ለማሳያነትም፡- “ወርቁ ቢጠፋ ሚዛኑ አይጥፋ፣ ወርቅን በሚዛን እህልን በላዳን፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር፣ የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም፣ ወርቅ በእሳት ይፈተናል፣ ወርቅና ጨዋ አስታራቂ ነው፣ ወርቅ የያዘ ሳጥን በወርቅ አይለበጥም ወዘተ.” በሚሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚተላለፉት መልእክቶች ምን ያህል የገዘፉ እንደሆኑ መመርመር ይቻላል። ወርቄ፣ ወርቅነሽ፣ ወርቅአየሁ፣ ወርቁ ወዘተ. የሚሉት የተለመዱት የግለሰቦች ስያሜዎችም ምን ለማለት ተፈልጎ ስሙ እንደተሰጣቸው አንባቢያን ሊገምቱ ይችላሉ።

ሌላው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከወርቅ ጋር ተዳብሎ የተጠቀሰው እንግዳ መሰል ቃል —**ደበሰ**“ የሚለው ነው። ወርቅ ይደብሳል ሲባል፣ ይወይባል፣ ይጠቁራል፣ ይቆሽሻል፣ ተፈጥሯዊ ውበቱንና ቀለሙን ያጣል፣ ያድፋል፣ ይነብዛል ማለት ነው። ስለዚህ በሁሉም የአዳምና የሔዋን (የአደምና የሐዋ) ዝርያዎች መካከል የማሕበራዊውን መስተጋብር ዋጋ ከፍ የሚያደርገው ይኼው የወርቅ ሀብት መጠን ነው።

በአገራት መካከል ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውንና ማሕበራዊ ሱታፌውን የሚያደምቀው፣ የሚያስከብረውና የሚያቆነጀው “ወርቅ” ይሉት ትንግርተኛ መሆኑም ልብ ሊባል ይገባል። የወርቅ ሀብት በአግባቡ ካልተያዘ በስተቀር መወየቡ፣ መበላሸቱ፣ መልክና ውበቱ መጠየሙ፣ በእድፍ መቆሸሹና በመጨረሻም ተገቢውን ዋጋ ማጣቱ አይቀሬና የግድ ነው። ወርቅ በእሳት ሲፈተን ያምር ካልሆነ በስተቀር ቀልጦ ያለመጥፋቱም የዚህ የከበረ ማዕድን ሌላው መገለጫ ነው።

**በወርቅ ተምሳሌትነት የአገራችንን ገመና እንፈትሽ፤-**

ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ በልዩ በረከትነት ከፈጣሪ የተቸረች በወርቅ የምትመሰል ድንቅ አገር ነች። ይህንን እውነታ ለመሞገት መሞከር ከቶውንም ቢሆን ያዳግት ይመስለናል። እንሟገት እንኳን ቢባል ግጭቱ የሚፋፋመው ከታሪክ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎችና ከተፈጥሯዊ የማሕበረሰባችን የአገነባብ ሥሪት ጋር መሆኑ አይቀሬ ነው።

ጉዳዩ “ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ” ከሚለው አገራዊ ብሂል በእጅጉ የራቀ መሆኑን ማስታወሱ አግባብ ይሆናል። ትምክህት ተደርጎም ሊቆጠር አይገባም። ይህቺ ምድር በተፈጥሮ ሀብት፣ በብሔረሰቦቿ ጥበብና እውቀት፣ በአሥራ ሦስት ወራት ተስማሚ የአየር ንብረቷ፣ በታሪክና በባህሏ እንደምን የበረከት ፀጋ እንደተጎናጸፈች በንጹሕ አእምሮ ለሚያስብ ዜጋ ይጠፋዋል ተብሎ አይገመትም። በብብቷ ውስጥ አቅፋ የያዘቻቸው ብሔረሰቦቿም ልክ እንደ ወርቅ የከበረ ማንነት ያላቸውና የስብጥራቸው መገለጫ “ቀለማትም” እጅግ የተዋቡና የደመቁ ናቸው።

እውነታውን ቀድመንና ተቻኩለን ከመጻረራችን አስቀድሞ ሁላችንም ልንጠይቅ የሚገባው መሠረታዊ ጥያቄ እነዚህን የመሰሉ በወርቅ ባህርያት የሚመሰሉ አገራዊ እሴቶቻችንና ፀጋዎቻችን ስለምን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደበሱ፣ እየወየቡ፣ እየጠቆሩና እየከፉ ሊሄዱ ቻሉ? ቆም ብለንና ሰክነን ልንነጋገርባቸው ጊዜው አጀንዳ አድርጎ ያቀበለን ዋና ጉዳይ ይመስለናል።

ዛሬ እያስተዋልናቸው ያሉት በርካታና ቅጥ አምባሩ የጠፋባቸው አገራዊ ችግሮቻችን ስለምን እንደ ከፋ ባዕዳን ወራሪዎች አስገብረው ሊገዙን እንደቻሉ ደፈርና ጫን ብለን ልንመክርባቸው ይገባል እንጂ “ጉዳዩ አይደሉም” ብለን ገሸሽ በማድረግ ብንርቃቸው የሚያዋጣ አይሆንም።

ለምሳሌ፡- “በዚህች መሰሏ የገነት ተምሳሌት ምድር” ላይ እየኖርን ስለምን በርሃብ ለመቀጣት በራሳችን ላይ ፈረድን? ስለምን ወደ ለምለሙ ምድራችን የስንዴ ርዳታ እንዲጎርፍ በራችንን ወለል አድርገን ከፈትን? እኮ ስለምን ያለ ግል ምርጫችንና ፍላጎታችን ለተገኘንበት ብሔር፣ ቋንቋና ባህል እያዳላን መገዳደልን ምርጫችን አደረግን? ልብ ተቀልብ፣ ሩሕ ለሩሕ እየተናበብን ወደ ጋራ መፍትሔ መቃረብ እስካልቻልን ድረስ እኛ ብናልፍም ታሪክ መትረፉ ስለማይቀር ውጤቱ ትዝብትና ማንነታችንን ጥቀርሻ አልብሶ ከማለፍ ውጭ አንዳች ፋይዳ አይኖረውም።

በታሪካችን ውስጥ ዘመን አምካኝ ሆነው ሲያሸማቅቁንና አንገት ሲያስደፉን የኖሩትን የደበሱና የበለዙ አገራዊ ታሪኮቻችንን በሙሉ ከመዘርዘር ታቅበንና ለጊዜ ጊዜ በመስጠት አቆይተናቸው ወደ ሰሞንኛው መሪር ሀዘናችንና ቀልባችንን ወዳስቆጣው ጉዳይ ውሱን ጥቁምታ እናድርግ።

በአዲስ አበባ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የአንድን ክልል ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ምክንያት አድርገው የተነሱት ሰሞንኞቹ ሁከቶችና ረብሻዎች ሥር መሠረታቸው ቢጠና በርግጡ ምክንያቱ ከላይኞቹ ባለሥልጣናትና ከታችኞቹ እንደሚነገረን ነው ወይንስ ሌላ ድብቅ አጀንዳ ይኖረዋል?

ይህ በአዲስ አበባ የተጫረው የእሳት ወላፈንስ በዚሁ በመዲናችን ብቻ ተወስኖ ስለመቅረቱ ምን ዋስትና ይኖራል? የችግሮቻችንን ሰበቦች ደፍረን ማፍረጥ እስካልቻልን ድረስ እየተደፋፈርን እርስ በእርስ ለመጠፋፋት ስለምንበረታታ ልባችንን ሰፋ አድርገንና የስሜታችንን ግለት አቀዝቅዘን መመካከሩ ውዴታ ብቻም ሳይሆን ግዴታም ጭምር ይመስለናል።

አገሪቱ እንደ ወርቀ ዘቦ ተጎናጽፋ ለዘመናት ያኖረችን የእርስ በእርስ የመከባበር እሴት ዛሬ ዛሬ እየተሸረሸረ ለመተማመን እስከማንችል ድረስ “ብሔራዊ የጥርጣሬ ባህል” ወደ መሆን ደረጃ ሊፋፋ የቻለው ምን ይሉት ማዳበሪያ ቢቀላቀልበት ነው? ይህን መሰሉ “ወርቃማ” እሴት እንዲደብስ ምክንያቱስ ምንና ማን ነው? ማንስ ነበር?።

በአንድ የእውቀት ማዕድ ላይ የተቀመጡ ልጆቻችን እርስ በእርስ የጎሪጥ እየተያዩ ውለው እንዲገቡስ ምክንያት የሆነው ክፉ ነቀርሳ በርግጡ ተለይቶ ይታወቃል ወይንስ እንደ ገበያ ውስጥ ሌባ ሰራቂውና ተሰራቂው “ሌባ ሌባ!” እየተባባሉ እንደሚሯሯጡት ዓይነት ይሆንን? በሰላም የወጡት ልጆቻችን በማያውቁት ጉዳይ በደም አበላ ተጠምቀው ሲመጡ ማየት ለወላጆች ምን ያህል ቅስም ሰባሪ እንደሆነ አጥፊዎቹም ሆኑ ተሚጋቾቹ አልተረዱትም ይሆን?።

ቋንቋና ባህላችንን ከልብ የምንወዳቸውና የምናከብራቸው ሁለቱንም ስለተወለድንባቸው እንጂ በደም ውርስ የተገኙ ፀጋዎች ስለሆኑ አይደለም። ቋንቋን ማወቅ ያስከብራል እንጂ የመለያያ ምክንያት ሆኖ ከቶውንም “ሰይፍ አያማዝዝም”። የክልል ሰንደቅ ዓላማም ቢሆን የአንድ ውሱን ክልል የፖለቲካ ምልክት እንዲሆን በአንድ ወቅት የፖለቲካ ተዋናዮች ፍላጎት የተፈጠረ አርማ እንጂ ከዘመናት አስቀድሞ “እንዳይለወጥና እንዳይሻሻል በውግዘት ማህተም ፀድቅ” የተላለፈ ውርስ አይደለም። መዝሙሩም ቢሆን ለተወሰነ የሥልጣን ዘመን የተገደበ እንጂ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚኖር “የሃይማኖት ቀኖና” አይደለም። እናስ በእነዚህ እውነታዎች ስንመዝነው የሰሞኑ ረብሻ መንስዔ በርግጡ ውሃ መቋጠር የሚችል ጉልበት ነበረውን? ደግሞስ ይኖረዋልን? የደረሰውን የንብረትና የሥነ ልቦና ጉዳትና ስብራትስ የመጠገን ብርታት አለው። አገራችንንስ ባልተፈለገ ሌላ መከራ ውስጥ ብትወድቅ የሚጠቀመው ማነው?።

ዛሬ ፖለቲካውን በመዘወር የአገር ናላ የሚያዞሩት አብዛኞቹ ፖለቲከኞችና “እሳት አራጋቢ አክቲቪስቶች” ያለምንም ይሉኝታ የተማሩት በውጭ አገራት ቋንቋ ጭምር እንጂ (ብዙውን ጊዜያቸውን ያጠፉት በባዕድ ቋንቋ በመማር መሆኑ ሳይዘነጋ) “የእናት አባቴ ውርስ” በሚሏቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዳልሆነ ጫን ብለን ማስረገጥ ያለብን ይመስለናል። የትኛውንም ቋንቋ መማር ክብርም ጌጥም ቢሆንም።

ይህ ጸሐፊ አፍ የፈታበትን ቋንቋ እና በአንድ የተለየ ቋንቋ ተናጋሪ ማሕበረሰብ መካከል በመኖር የለመደውን ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ በማወቁ አትርፎበታል እንጂ አንድም ጉዳት አላጋጠመውም፤ አልከሰረምም። እየተደነቃቀፈም ቢሆን በውጭ አገራት ቋንቋ መማሩም በእጅጉ ጠቅሞት አንቱ አሰኘው እንጂ ሰብእናውን አላንኳሰሰም። እናስ ልጆቻችንን ባልገባቸውና ባልተረዱት ጉዳይ “የፖለቲካ ማስተሰረያ ጦስ” እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ስለምንድን ነው? የታወኩትና የሥነ ልቦና ቀውስ እየደረሰባቸው ያሉት ልጆቻችን ብቻ ሳይሆኑ እኛ ወላጆች ጭምር ስለመሆናችን ያልገባቸው አካላት ይኖሩ ይሆን?።

አንዱን ስንቋጥር ሌላው አገራዊ ጉዳያችን እየተተረተረ፣ አንዱን ቀዳዳ ስንደፍን ሌላኛው እያንጠባጠበ፣ ያኛውን ችግር ስናጠራ ሌላኛው ጉዳይ እየተበጠበጠ መኖሩ ለድህነታችን ጉልበት ይሆን ካልሆነ በስተቀር አንዳች እርባና ስለማይኖረው ቆም ብለን በስክነት ብናስብበት አይከፋም።

በወርቅ መስለን የኖርንባቸውና ያኗኗሩን እሴቶቻችንንና ዛሬ ከእጃችን ወድቀው ለመከራ የዳረጉንን ፀጋዎቻችንን ቆም ብለን መፈተሽ ጊዜው የሚጠይቀው የመፍትሔ መንገድ ስለሆነ ሰከን እና ትንፋሻችንን ሰብስበን አድርገን በመወቃቀስ ሳይሆን በመከባበር፣ በመፈራራት ሳይሆን በመቀራረብ፣ በመተቻቸት ሳይሆን በመደማመጥ ልንመካከር ግድ ይሏል።

“አሌፍ፡- ወርቁ እንዴት ደበሰ? ጥሩው ወርቅስ እንዴት ተለወጠ? ጥሩ ወርቅ የሚመስሉ የከበሩ [ልጆቻችን] የሸክላ ሠሪ እጅ እንደ ሠራው እንደ ሸክላ ዕቃ እንዴት ተቆጠሩ?” (ሰቆቃወ ኤርሚያስ ምዕ. 4፡1-2)። በማለት እንዳነባው የቅዱስ መጽሐፉ ነብየ እግዚሃር ኢትዮጵያም ዛሬ “ወርቃማ የሆኑት እሴቶቿ ደብሰው ስለተበላሹባት” መንታ መንታ የምታነባ ይመስለናል።

ከግማሽ ክፍለ ዘመን በፊት በተጻፉ ጥቂት የግጥም ስንኞች ሃሳባችንን እንጠቅልል።

**“ትናንት መሠረት ነው ዛሬ የቆመበት፤-**
**ዛሬም መሠረት ነው ነገ የሚያርፍበት።**
**የዛሬው ውሳኔ ሚዛን ነው ለነገው፣**
**ዛሬ ያልከበደ ነገ መቅለሉ ነው።**
**ዛሬ እንደሠፈሩት ቢተርፈም ቢጎድልም፣**
**ነገ ይሠፈራል ታሪክ ፍርዱ አይቀርም።**
**ከባዱ ውሳኔ ትልቅ ኃላፊነት፣**
**የነገው ቅርጸ-መልክ የሚታነጽበት።**
**ነገ ዛሬ ሲሆን ዛሬም ትናንትና፣**
**የዛሬ ቁራኛ ግልጽ ድንቁርና።”**

(ምንጭ፡- “ሕያው ድምፆች” ከቀድሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የግጥም ስብስብ ተመጥኖ የተወሰደ።) ሰላም ይሁን።

# ተናጋሪው ዶሴ

# ክፉ ንግግር - እንጨት ላይ እንደተመታ ምስማር

አስመረት ብስራት

**≪ክፉ ንግግር እንጨት ላይ እንደተመታ ምስማር ነው፤ በይቅርታ ብንጠግነውም ጠባሳው አይተውም≫** የሚል አባባል ጊዜውን በውል ባላስታውሰውም አንድ ወቅት ላይ ማንበቤ ትውስ ይለኛል። እውነት ነው፤ በአንደበታችን የምንናገረው ነገር መልካም ሲሆን፣ ጽድቅ ሆኖ እንደሚቆጠርልን ሁሉ መጥፎ ከሆነ ደግሞ እርኩሰት ይሆንና በፈጣሪ ፊት ጭምር ተጠያቂ ያደርገናል። ኃጢአት በአብዛኛው ካልተገባ ንግግር የሚመነጭ ነው። ስለዚህም እንደስድብ እና የሐሰት ንግግር እንዲሁም አሳሳች ከሆኑና መሰል አባባሎች ከአንደበታችን እንዳይወጡ ልጠንቀቅ ይገባል። አስከፊ በሆነ ንግግር ሰዎችን መናገር እንዲሁም ቁጣና ጭካኔ የተሞላባቸው ቃላት እና ግብታዊ ንግግሮች፣ የማስፈራሪያ ቃላት፣ የሐሰት ምስክርነት እና በሐሰት መማል ሁሉም በአንደበት የምንሠራቸው እርኩሰት ናቸውና ከአንደበታችን ሊወጡ አይገባም የሚል እምነት አለኝ።እንዳውም በተቃራኒው ≪መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች≫ የሚለውን መከተል ያስፈልጋል። መጥፎ ንግግር ምላሹም መጥፎ ነውና ሰዎችንም ወደ ስሜታዊነት ይከታል።

ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ ‹‹መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም ከልቡ ክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል፤ ከልብ የተረፈውን አፍ ይናገራልና።›› የምንናገረው ቃል በሌሎች ላይ ተጽእኖ አለው፤ ስለዚህም ከአንደበታችን የምናወጣው ቃል በማስተዋል መሆን አለበት።

ይህን ሀሳብ እንዳነሳ ያስገደደኝ ከፍትህ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ያገኘሁት ታሪክ ነው። ዘወትር ‹‹አንቺ የማትረቢ በሽተኛ›› እየተባልኩ ስሰደብና ስዘለፍ ኖሪያለሁ ያለች የ39 አመት ወይዘሮ፣ ውስጧ የተፈጠረው መርዘኛ ቁሰል አልሽር ቢላት የልጆቿ አባት በሆነው በትዳር አጋሯ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ እጇን አንስታበታለች። ይህንን አስመልክቶ የሚከተለውን አሰናድተናል።

**ታታሪዋ ወይዘሮ**

ወይዘሮ ከበቡሽ አለሙ አበበ፣ ኑሮዋን ለማቃናት ዘወትር የምትለፋ ወይዘሮ ናት። አነሰ አደገ ሳትል ኑሮዋን ለመደገፍ ትታትራለች። ምንም እንኳን ፊደል ያልቆጠረች ቢሆንም ተፈጥሮ በለገሰቻት እውቀት ነግዳም በጉልበቷ አድራም ልጆቿ ምንም ሳይጎድልባቸው እንዲያድጉ ጥረት ታደርጋለች። በተቃራኒው ደግሞ የተማረውና የተሻለ ገቢ የሚያገኘው የትዳር አጋሯ በምትሰራው ነገር ምንም ደስታ ያልነበረው እንዲሁም በትዳሩ የሚናደድ ዘወትር ጭቅጭቅን አማራጭ ያደረገ ሰው ነበር።

በወጣ በገባ ቁጥር በውሃ ቀጠነ ሚስቱን መነዝነዙን ሳያንስ ያለመማሯን ነገር እያነሳ ያንቋሽሻትና ያዋርዳት ጀመር። ነጋ ጠባ ጭቅጭቅ የሆነበት ሴት እንደ ምንም ለልጆቼ ስል ልታገስ ብላ አንገቷን ደፍታ የሆዷን በሆዷ ይዛ ለመኖር ብትጥርም ‹‹አንቺ የማትረቢ! በሽተኛ!›› የሚለው ስደብ ግን ከውስጧ አልወጣ እያለ የልጆቿን አባት በጥላቻ እንድትመለከት አልፎ ተርፎም እሱን ለማጥፋት እቅድ ለማውጣት የምታስብ ሴት እንድትሆን አደረጋት።

እለት እለት ውስጥን አቁሳይ በሆነ ቃላት ወትሮም መርቅዞ አልድን ያላትን የውስጥ ቁስሏን እየነካካ ወደማትወጣው ጥላቻ ውስጥ ይከታታል። ከጥላቻም በላይ ፍፁም ጭካኔን እለት ከእለት እንድትለማመድ ትሆናለች። በከባድ የበታችነትና ራስን የመጥላት ስሜት ውስጥ ሆና ልጆቿን በማሰብ ነገሮችን ልታልፋቸው ብትሞክረም የውስጧን ጩኸት ግን ማስቆም አልቻለችም ነበር።

‹‹ግደይው!...ግደይው!...›› የሚለውን ስሜቷን ሊያሸር የሚችል ምንም ሀይል ጠፋ። ስለ ልጆቿ ብታስብ ስለነገዋ ብታልም ምንም ከልክ በላይ የሞላውን የጥላቻ ስሜት ከውስጧ ፍቆ ሰላምን እንድታስብ ብሎም ነገን በተስፋ እንድታይ ሊያደርጋት የሚችል አማራጭ አጣች። ከዛ ያንን የጥላቻና የበቀል ስሜቷን የምታበረድበት እቅድ ማውጣት ቀጠለች ።

**የበቀል ዛቢያ**

አቶ ፀጋዬ ሞላ ይባላል። ብዙም ደስተኛ የሚባል አይነት ሰው አይደለም። ማማረርና አቃቂር ማውጣት የዘወትር ተግባሩ የሆነ ሰው ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ



‹‹አይጠዳሽ›› የሚባል አይነት ሰው ነበር። አድጎ ተምሮ ስራም ይዞ እንኳን ያንን ባህሪውን አልተወም። በዚህ ባህሪው ብዙም ከሰው ጋር የማይግባባ ጓደኛ ያልነበረው ሰውም ነበር።

ልክ ስራ ይዞ የመጀመሪያ ደመወዙን እንደተቀበለ ነበር የወላጆቹን ቤት ትቶ በመውጣት ብቻውን መኖር የጀመረው። ወትሮም በሰላም ከቤተሰቡ ጋር ኖሮ የማያውቀው ይህ ሰው፣ ዞር ብሎ አንድም ቀን ወላጆቹን ለመጠየቅ ተመልሶ አያውቅም ነበር። አንዳንዴ በተከራያት አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ምግቡን እያበሰለ ይመገባል። ቤቱ ካላበሰለ ግን ለመኖር የተከራየባት አንድ ክፍል ቤት አካባቢ ከበቡሽ አለሙ የተባለች ወጣት በከፈተችው አነስተኛ ምግብ ቤት ሄዶ ይመገብ ነበር።

ቤት ከሚያበስለው ይልቅ የከበቡሽን ምግብ ምርጫው ያደረገው ፀጋዬ ወደ ምግብ ቤቷ መመላለስ አበዛ። ብዙም ፊቱ የማይፈታው ሰው በመመላለሱ ከከበቡሽ ጋር ተላመደ፤ መላመዳቸው ወደ ፍቅር አድጎ አብረው መኖር ጀመሩ። የተጋቡ ሰሞን በደስታና በመከባበር የተወሰኑ ወራትን ቢገፉም ውሎ ሲያድር ግን የፀጋዬ አመል ከተሸሸገበት ብቅ ማለት ጀመረ።

በዚህ መካከል የመጀመሪያ ልጃቸውን ሰላገኙ ከበቡሽ ስራዋን እርግፍ አድርጋ ትታ ቤት መዋል ጀመረች። የገቢው መቀነስ ከአባወራው አመል ጋር ተደማምሮ ንትርክ የማያጣው ኑሮ ለመግፋት ተገደዱ። በዚህ መካከል ሁለተኛ ልጃቸውን ደገሙ። አሁን ሁሉም ነገር አይን አውጥቶ ዘለፋና ማንጓጠጡ በርክቶ ዱላም ተከተለ።

ያን ጊዜ ከበቡሽ እንደምንም ራሷን አጠናክራ ወደ ቀድሞ ስራዋ ተመለሰች፤ ያ ደግሞ አባወራውን ጭራሽ አስቆጣው፤ ነጋ ጠባ ጭቅጭቅ ንዝንዝ ሆነ። ዝልፊያውና ማንጓጠጡን ግን እማወሪት መቋቋም ተስኗት ነበር።

**የቂም ጅራፍ**

ዘወትር ዝልፊያና ማንጓጠጡ የሰለቻት ወይዘሮ፣ ቂም ቋጥራ መጥረቢያዋን ስላ ሰው ሁሉ እንቅልፍ እስኪወስደው መጠበቅ ጀመረች። በተቀመጠችበት እንቅልፍ የጣላት ወይዘሮ፣ መጥረቢያዋን እንደታቀፈች ከእንቅልፏ ስትባንን የቀን እቅዷን አስታወሰች። ያለምንም ማወላወል ባሏ ወደተኛበት ተመለከተች። ለጥ ብሏል። ልጆቿም ጭልጥ ያለ የእንቅልፍ ዓለም ውስጥ መሆናቸውን አረጋገጠች።

ዕለቱ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ነው። ከሌሊቱ በግምት 9፡00 ሰዓት አካባቢ። በነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ልዩ ቦታው 58 ቆጣሪ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ነው። በወቅቱ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ አገር ሰላም ብሎ የተኛውን የሁለት ልጆቿ አባት የሆነውን ሟች ፀጋዬ ሞላ፣ ‹‹አንቺ የማትረቢ! በሽተኛ!›› እያለ ይሰድበኛል ከሚል ቂም በመነሳት በጭካኔ መጥረቢያውን ሰነዘረች። በአንድ ምት ጭንቅላቱን በመጥረቢያ የተመታው አቶ ፀጋዬ፣ እስከወዲያኛው ላይነሳ አሸለበ። ይሁንና ውስጧ ይንተከተክ የነበረው የበቀልና የጥላቻ ስሜት ጠፍቶ ውስጧ በሽብር ተሞላ። የሟችን ፊት ሸፍና ወደደጅ በመውጣት በውደቅት እጇን ለህግ አካላት ሰጠች።

**የፖሊስ ምርመራ**

‹‹ባለቤቴን ገድያለሁ›› ስትል እጇን ለፖሊስ ያስረከበችውን ሴት በመያዝ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የተገኘው ፖሊስ፣ ያየውን ማመን አቅቶታል። የተሸፈነው ሰው እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ጭንቅላቱን ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። በዛ ያለ ሰው ድምፅ ሰምተው ከእንቅልፋቸው የነቁት ህፃናት ግራ ተጋብተው የእናታቸውን አይን አይን ይመለከታሉ።

ፖሊስ ይጠቅመኛል ያለውን መረጃና ማስረጃ በመውሰድ ተከሳሿን ይዞ ወደ ማረፊያ ይወስዳል። በእጁ የገባውን መጥረቢያ፣ የተከሳሽን የእምነት ቃል፣ የፎረንስኪ ምርመራን በማድረግ ያጠናቀረውን ሕግ የሰው፣ የሰነድ እና የኢግዚቢት ማስረጃዎችን በመያዝ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት ያደርጋል።

ተከሳሽም ለፖሊስ በፍርድ ቤት እና በፖሊስ ጣቢያ ድርጊቱን ስለመፈጸሟ አምና የሰጠችውን ቃል ዐቃቤ ህግ ክስ ከተመሰረተባት በኋላ በችሎት ቀርባ ክዳ የተከራከረች በመሆኑ ዐቃቤ ህግ የሰው፣ የሰነድ እና የኤግዚቢት ማስረጃዎችን በማቅረብ ክሱን በበቂ ሁኔታ አስረድቷል።

**የፍርድ ቤት ክርክር**

ክርክሩን የመራው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ግድያ ችሎት ነው፤ በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ ጎአ እንደገለጹት የ39 ዓመቷ ወይዘሮ ከበቡሽ አለሙ አበበ፣ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 9፡00 ሰዓት በነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ልዩ ቦታው 58 ቆጣሪ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ካለ የመኖሪያ ቤቷ ውስጥ የሁለት ልጆቿ አባት የሆነውን ሟች ፀጋዬ ሞላ ‹‹አንቺ የማትረቢ! በሽተኛ!›› እያለ ይሰድበኛል ከሚል ቂም በመነሳት በጭካኔ ጭንቅላቱን በመጥረቢያ በመምታት ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረገች በመሆኑ የወንጀል ምርመራ ሲደረግ ቆይቶ ሚያዚያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ዐቃቤ ህግ በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ክስ መስርቶባት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።

ተከሳሽም ለፖሊስ በፍርድ ቤት እና በፖሊስ ጣቢያ ድርጊቱን ስለመፈጸሟ አምና የሰጠችውን ቃል ዐቃቤ ህግ ክስ ከመሰረተባት በኋላ በችሎት ቀርባ ክዳ የተከራከረች በመሆኑ ዐቃቤ ህግ የሰው፣ የሰነድ እና የኤግዚቢት ማስረጃዎችን በማቅረብ ክሱን በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንድትከላከል ብይን ቢሰጣትም የመከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ያላቀረበች በመሆኑ የመከላከል መብቷን አሳልፋ ሰጥታለች።

## ውሳኔ

ሚያዚያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ዐቃቤ ህግ በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል የመሰረተውን ክስ ሲመለከት የቆየው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት ሶስት የቅጣት ማቅለያዎችን በመያዝ በእርከን 36 ስር በ21 ዓመት ጽኑ እስራት እና ለ5 ዓመት ከማህበራዊ መብቷ እንድትታገድ ወስኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በሀሳብ እንጂ በሐረግ የሚሰባሰብ ዕውቀት እንዴት ይኖራል?

ደበል ካሳ

ወደአዋቂነት የዕድሜ ክልል ከተሸጋገርኩበት ጊዜ ጀምሮ ሁሌም የሚያስጨንቀኝ አንድ ጥያቄ አለ። ይኸውም “ለሰው ልጅ ሕይወት መሻሻል አንዳች ነገር የማያበረክት ይባሱኑ ሰውን የሚጎዳና ችግር ውስጥ የሚከት ሃሳብ ዕውቀት ሊባል ይችላል ወይ?” የሚል ነው። የዓለምን ሁኔታ በተረዳሁበት መጠን ይህንን ጥያቄ ደግሜ ደጋግሜ ራሴን ጠይቄያለሁ። በእርግጥ ሁሉም ሰው የራሱ የሆነ አረዳድ ይኖረዋል፤ እኔ የደረስኩበትን ድምዳሜ ግን በትዝብት መልክ ላካፍላችሁ። በግሌ “ለሰው ልጅ ሕይወት መሻሻል አንዳች ነገር የማያበረክት ይባሱኑ ሰውን የሚጎዳና ችግር ውስጥ የሚከት ዕውቀት ዕውቀት ሊባል ይችላል ወይ?” ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በርካታ ጊዜያትን ካሰብኩና ካሰላሰልኩ በኋላ “አይችልም” የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ። ምክንያቴን እንደሚከተለው ላቅርብ።

በእኔ ዕይታ ዕውቀት ዕውቀት ሊባል የሚችለው አገርም አልነው ዓለም ዞሮ ዞሮ የሚኖርበት ሰው ነውና ሰውን መጥቀም የሚችል ሲሆን ነው። ሰውን የማይጠቅም ይባስ ብሎ ሰውን የሚጎዳ ዕውቀት ግን ዕውቀትም አይደለም፤ ዕውቀት ተብሎ መጠራትም የለበትም።

ይሁን እንጂ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በየዘመኑ የማይጠቅምና በተቃራኒው ሰውን የሚጎዳ “ዕውቀት” ስያሜው ሳይገባው ዕውቀት የሚል መጠሪያን አላግባብ ሲጠቀም ተስተውሏል። አሁን በእኔ ዘመን እዚህ በእኛዋ ኢትዮጵያ ደግሞ ሰውን የሚጎዳ ዕውቀት ያልሆነ ዕውቀት ከመቼውም ጊዜ በላይ የተስፋፋ ይመስላል። እንዲህ ዓይነቱ ዕውቀት ያልሆነ “ዕውቀት” በተለያዩ መቸቶች ራሱን በተለያየ መልክ የሚገልጽ ቢሆንም አሁን ላይ በእኛ አገር በስፋት እየተስተዋለ የሚገኘው ግን ብሔርንና ብሔርተኝነትን ሽፋን አድርጎ ለጥፋት የቆመው ዋነኛው ዓይነት ያላዋቂዎች ዕውቀት ነው።

እውነት ነው በሐረግ እንጂ በሃሳብ የማይሰባሰቡ አላዋቂ አዋቂዎችና ዘረኛ ብሔርተኞች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተከታይ አላቸው። በተከታዮቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው ተደርገው ይወሰዳሉ። ይሁን እንጂ ይህ ዕውቀታቸው ዕውቀት ለመባል ጠበቃ ቆምንልህ ለሚሉት “ሕዝብ” አንዳች ፋይዳ ሊኖረው ይገባ ነበር። የሆነውና እየሆነ ያለው ግን በተቃራኒው ነው። እንዲያውም በመጥቀም ፋንታ ሕዝባቸውን በከፍተኛ ደረጃ እየጎዱት መሆኑ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ሆኗል። ምክንያቱም ለዘመናት አብሮ በሰላምና በፍቅር በኖረ ሕዝብ መካከል የጥላቻን መርዝ እየረጩ “ለጥቅምህ ታገልንልህ” የሚሉትን ሕዝብ ለችግር እየዳረጉት ነው።

በዚህም ከእነርሱ ውጭ ያለን ሕዝብ በጠላትነት እየፈረጁ ራስ ወዳድነትንና ግለኝነትን ይሰብኩታል፤ ያስተምሩታል፣ ያወርሱታል። ሃቁ ግን ለአንድ ብሔር ከራሱ ከብሔሩ ዘረኛ አቀንቃኞች በቀር ሌላ ጠላት አለመኖሩ ነው። ምክንያቱም “እከሌ በመሆንህ ሆን ተብሎ በማንነትህ ጥቃት እየደረሰብህ ነው” የሚል አንድ የብሔር “ተቆርቋሪ” እዳ ካልሆነ በቀር ለዚያ ሕዝብ የሚያበረክትለት አንዳች ፋይዳ የለውምና። እነዚህ ሰዎች የሚሰብኩት ቂምን፣ ጥላቻን፣ መለያየትን ሲሆን ለሕዝባቸው የሚያተርፉት ጥቅም ደግሞ ግጭትን፣ መፈናቀልንና ስደትና ሞትን ነው።

ታዲያ ፅንፈኛ ብሔርተኞች “ሕዝባቸውን” እየጠቀሙት ወይስ እየተጠቀሙበት ነው? የዚህን ጥያቄ ምላሽ ምን እንደሆነ ለእያንዳንዳችን ልተወው። ስለሆነም ከሰሞኑ እንደምንታዘበው ሰላምን መጥላት፣ ጥላቻን መስበክና ጦርነትን መቀስቀስ በምንም መመዘኛ የዕውቀት መለኪያ ሊሆን አይችልም። እስኪ የትኛው ነው ዕውቀት? ለዘመናት በፍቅር አብሮ በኖረ ሕዝብ መካከል የጥላቻ መርዝን እየረጩ እርስ በእርስ ማባላት? በአጥንትና በደም በተከፈለ መስዋዕትነት በነጭ እብሪት ያልተንበረከከ አሸናፊ ሥነ ልቦናን ያወረሰች ታላቅ አገር አፍርሶ ታናሽ አገር ለመፍጠር መነሳት? “የኔ” እንጂ “የኛ” ማለትን የማያውቅ የጥፋት ትውልድን የሚኮተኩት የውድቀት ርዕዮተ ዓለምን ያለ እረፍት መስበክ? ይኸ ነው ዕውቀት?

እንዲህ ዓይነት ዕውቀት መቼውንም ዕውቀት ሊባል፣ እንዲህ ዓይነት “ዕውቀት” ያላቸው ሰዎችም የቱንም ያህል ቢራቀቁ አዋቂዎች ናቸው ሊባሉ አይችሉም። በዚህ ዕውቀታቸው የመጨረሻው ማማ ላይ ቢደርሱም ታላቅ አይባሉም። ዓለም ላይ ታላቅ የሚባለውን ጀብዱ ቢፈጽሙም ጀግና ሊባሉ አይችሉም። እንደዚያ ከሆነማ ሂትለርን የሚያክል ጀግና ማን ነበር። ቅሉ ሂትለር አስተሳሰቡ የክፋት ዕውቀቱ የጥፋት ነበረና ያ ሁሉ የጥፋት ጀብዱው ጀግና አላስባለውም። የናዚዝም ዕውቀቱ ከፍተኛ ነበር፣ ሆኖም ዕውቀቱ አጥፊ ነበርና ሂትለር ታዋቂ እንጂ አዋቂ መሆን አልቻለም።

ነገር ግን እላለሁ፤ ጥላቻንና መለያየትን የምትሰብኩ ፅንፈኛ ብሔርተኞች እናንተ አዋቂ ከሆናችሁ የክፋት ሁሉ ምንጭ የሆነው ሴጣንም አዋቂ ነው። እንዲህ አይነት ሰዎች ጀግና ከሆኑ በሰው ልጆች ላይ የመጨረሻውን ዘግናኝ ግፍ የፈጸመው አረመኔው ሂትለርም ጀግና ነው ማለት ነው። ዕውነታው ግን እንዲህ አይነት ሰዎችም፣ ሴጣንም፣ ሂትለርም ታዋቂ ሆነው ሊሆን ይችላል እንጂ አዋቂ አይደሉም። ጀግናም አይደሉም፤ አይሆኑምም። ዕውቀት የሚባለው በክፋትና በጥፋት ልቆ መገኘት ከሆነም ሺ ጊዜ ድንቁርና ይመረጣል።

ለዚህም ነው በአውሮፓውያኑ የካቲት 2 ቀን 2015 በቅዱስ ፒተርሰበርግ ራሽያ ተወልዳ መጋቢት 6፣ 1982 ማንሃታን ኒውዮርክ አሜሪካ ውስጥ ያረፈችው “ኦብጀክቲቪዝም” በሚባል የራሷ የፍልስፍና እሳቤ የምትታወቀው ዝነኛዋ ራሽያ-አሜሪካዊት ደራሲና ፈላስፋ አያን ራንድ “ብሔርተኝነት ተፈጥሯዊ ሳይሆን የጭፍንነትና የመንጋነት አስተሳሰብ ውጤት ነው” በማለት ዘረኝነት አላዋቂነት መሆኑን አስረግጣ የተናገረችው። የዚች ታላቅ እንስት ፍልስፍና በተለይም የዘመናችን ምሁር ነን ባዮችና ፅንፈኛ ብሔርተኞች በደንብ የሚገልጽ ሃሳብ የያዘ በመሆኑ ሰፋ አድርገን እንመልከተው።

“በፍልስፍና መነጽር ስንመለከተው ፅንፈኛ ብሔርተኝነት ክፉና በጎውን ማመዛዘን የማይችል ምክንያታዊነት የጎደለው የጭፍን አስተሳሰብና በመንጋ ማመን የፈጠረው ነው። ለዚህም ዋነኛው ምክንያቱ በቡድን ካልሆነ በቀር ግለሰቦች በራሳቸው ምንም ማድረግ አይችሉም የሚለው የዘመናዊ ፍልስፍና አስተሳሰብ ነው። ይህ አስተሳሰብ በሂደት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርፆ በመግባት ተቀባይነትን ማግኘት ሲጀምር ግለሰቦች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት በከፍተኛ ደረጃ እየወረደ ይመጣል፤ የሚጠቅማቸውን ነገር ለመምረጥና ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን የራስ መተማመን ያጣሉ” ይላል የእንስቷ እሳቤ።

“ይህም ሰዎች ምክንያታዊ ዕምነት እንዳይኖራቸው ስለሚያደርጋቸው ሰዎች በአስተሳሰብ ሳይሆን በሥጋ የሚቀርባቸውን ቡድን እንዲቀላቀሉ ያስገድዳቸዋል። ይህ በአስተሳሰብ ሳይሆን በሥጋ ዝምድና የሚመሰረት “በምክንያት ያልተመረጠ ቡድን” ነው እንግዲህ “ብሔር” የሚል ታርጋ የሚለጠፍለት። በዚህ የተነሳም ብሔርተኞች በዕውቀትና በምክንያት ላይ ተመስርተው የሃሳቡን ጥቅምና ጉዳት መዝነው ሳይሆን አጥንታቸውን ቆጥረው ለተሰባሰቡበት ግዑዛዊ ቡድን “በማንኛውም ጊዜ ያለ ቅድመ ሁኔታ ለቡድንህ ታመን” ከሚለው ከሁሉም አስበልጠው ከሚያዩት የመንጋ መርሃቸው በቀር ሌላ ህግና መርህ አያውቁም።

እናም ብሔርተኝነት ፀረ ዕውቀት፣ ፀረ ምክንያታዊነትና ፀረ ሞራል የሆነ፣ ልፋት የማይጠይቅ የደካሞችና የሰነፎች ሥራ ነው። እናም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ጽንፈኞች ከራሳቸው ጠባብ የአጥር ክልል ውጭ ስላለው ዓለም ዴንታ የሌላቸው እንዲያውም ከእነርሱ ውጭ ያለውን ሁሉ የሚጠራጠሩና በስጋትነት የሚመለከቱ፣ በራስ ወዳድነት ታስረው የተቀመጡ ድኩማን ፍጥረቶች ናቸው። ጽንፈኞች ክፉውን ከበጎው የሚለዩበት ማመዛዘኛ ህሊና እና እውነቱን እውነት፣ ሃሰቱን ሃሰት፣ ትክክሉን ትክክል፣ ስህተቱን ስህተት የሚሉበት ሞራል የላቸውም።

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ ዩክሬን ዳግም ለማጥቃት ከ200 ሺህ በላይ ወታደሮችን እያዘጋጀች ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ ዩክሬን ዳግም ለማጥቃት ከ200 ሺህ በላይ አዳዲስ ወታደሮችን እያዘጋጀች መሆኑ ቢቢሲ ዘገበ።

የዩክሬን ፕሬዝዳንት እና ከፍተኛ የመከላከያ አዛዦች ሩሲያ በሚቀጥለው የፈረንጆቹ ዓመት መጀመሪያ ላይ አዲስ ጥቃት እንደምትጀምር ገልጸዋል። ይህም የዩክሬንን ዋና ከተማ ኪየቭን ለመያዝ ሁለተኛ ሙከራን ያካትታልም ተብሏል።

የዩክሬን ባለሥልጣናት የሞስኮን ጥቃት ለመከላከል የምዕራባውያን አጋሮቻቸው ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ እና ወታደራዊ ስልጠና አጥብቀው ይሻሉ።

የሞስኮ አዲስ ጥቃት በጥር ወር ሊከሰት ይችላል የተባለ ሲሆን፤ ፕሬዝዳንት ቮሎዲሚር ዘለንስኪ፣ ጀነራል ቫለሪ ዛሉዥኒ እና ጀነራል አሌክሳንደር ሲርስኪ ሐሙስ እለት ከዘ ኢኮኖሚስት መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስለ ጥቃቱ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ባለስልጣናቱ ጥቃቱ ከምስራቃዊ ዶንባስ አካባቢ፣ ከደቡብ ወይም ከአጎራባች ቤላሩስ ሊጀመር እንደሚችል እና በኪዬቭ ላይ ሌላ የመሬት ጥቃትን ሊጨምር ይችላል ብለዋል።

“ሩሲያውያን ወደ 200 ሺህ የሚጠጉ አዳዲስ ወታደሮችን እያዘጋጁ ነው። ወደ ኪየቭ ሌላ ጥቃት እንደሚያደርጉ አልጠራጠርም” ሲሉ ጀነራል ዛሉዝኒ ተናግሯል።

የዩክሬን መከላከያ ሚንስትር አሌክሲይ ሬዝኒኮቭ ዘ ጋርዲያን ላይ ባሳተሙት ጽሁፍ ሩሲያ ሰፊ አዲስ ጥቃት ለማድረስ ማቀዷን የሚያሳዩ መረጃዎች እየጨመሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በጥቅምት ወር ሩሲያ ጦርነቱን ለመደገፍ ከመለመለቻቸው 300 ሺህ ወታደሮች መካከል ግማሹ ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ አዲሱ እርምጃ በየካቲት ወር ሊከሰት እንደሚችል ሚንስትሩ ገምተዋል።

ዩሮ ኒውስ እንደዘገበው ሁለቱም ወገኖች በፈረንጆች ገና እርቅ እንደማይፈልጉ ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በአውሮፓ ትልቁ የሆነውን ግጭት ለማስቆም ያለመ ድርድር የለም ተብሏል።



## የጆን ኤፍ ኬኔዲ ግድያ የምርመራ ዶሴ ከ60 ዓመት በኋላ ይፋ ሆነ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዝዳንት የጆን ኤፍ ኬኔዲ ግድያ የምርመራ ዶሴ ከ60 ዓመት በኋላ ይፋ መደረጉ ተገለጸ።

ኬኔዲ የተገደሉት በዳላስ ከተማ ክፍት መኪና ውስጥ በጉብኝት ላይ ሳሉ ሲሆን ዋይት ሐውስ ጆን ኤፍ ኬኔዲን የተመለከተው ዶሴ ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ወስኗል። ይህ ዶሴ ለሕዝብ ይፋ እየሆነ ያለው ከ60 ዓመታት ጥብቅ ምሥጢርነት በኋላ መሆኑ አነጋጋሪ ሆኗል።

ብዛቱ ከ10ሺህ በላይ ይሆናል የተባለው ይህ ሰነድ ይፋ እንዲሆን የወሰኑት ፕሬዝደንት ጆ ባይደን ናቸው። ይሁንና አንዳንድ ሰነዶች አሁንም በምሥጢር እንደ ተወሰኑ የተነገረ ሲሆን ይህም ለአንዳንድ ሰዎች ደኅንነት ሲባል ነው ተብሏል።

ምንም እንኳ የጆን ኤፍ ኬኔዲ ግድያ ለረጅም ጊዜ እያወዛገበ ቢቆይም በዚህ ሰነድ የሚገለጥ አንዳች ታላቅ ምሥጢር ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። ዶሴው በፕሬዝዳንቱ ግድያ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ግን ልዩ ዕድል ይፈጥራል ተብሏል።

የቀድሞው ዝነኛና ተወዳጁ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ በቴክሳስ ግዛት፣ ዳላስ ከተማ፣ በክፍት መኪና ከባለቤታቸው ጋር በጉብኝት ሳሉ ነበር እ.ኤ አ በኅዳር 22፣1963 በተተኮሰባቸው ጥይት መገደላቸው ይታወሳል። ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ሰውየውን ማን ገደላቸው? ለምን ተገደሉ? በሚለው ዙሪያ ሺህ ምርመራዎች ተደርገዋል።

እነዚህ የምርመራ ሂደቱን የያዙ ዶሴዎችም በምሥጢር ሲከማቹ የቆዩ ሲሆን የ1992 የአሜሪካ ሕግ ዶሴዎቹ በጥቅምት 2017 ለሕዝብ ይፋ እንዲደረጉ አስገዳጅ አድርጎ ነበር። ዶናልድ ትራምፕ ለይስሙላ ያህል የተወሰኑ ሰነዶችን ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን አዘውም ነበር።

ትናንት ሐሙስ ግን ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ልዩ ትዕዛዝ በመስጠት 97 ከመቶ የሚሆኑትን ሰነዶች ይፋ እንዲሆን አዘዋል። ጨምረውም አንዳንድ ጉዳዮችን ለመቀነስ ስንል አንዳንድ የሰነዱ ክፍሎች በሰኔ 2023 ይፋ እንዲሆኑ ብለናል ብለዋል።



ጆን ኤፍ ኬኔዲ

# መጋቢ አዕምሮ

# ዓሳማ፤ መሰሳል አከራዩ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

---

በመንደሩ አንቱታን ያተረፉ የመሰላል አከራይ አሉ። በሰፈሩ ውስጥ ያለው መሰላል አንድ ነው፤ እኚህ ሰው ጋር የሚገኝ መሰላል ብቻ። ሰፈሬው መሰላል በፈለገ ጊዜ ወዲህ አባት ይመጣና ይከራያል፤ እርሳቸውም ከመሰላል ኪራይ ገቢ ያገኛሉ። ግለሰቡ በዚህ ስራቸው አንቱታን ያተረፉ በመሆናቸው የሰፈሩ ልጆች ምን መሆን ትፈልጋላችሁ ሲባሉ የሚመልሱት "መሰላል ማከራየት" የሚል ሆኗል። በሰፈሩ የሚገኘው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንም ሲያስተምሩ ምሳሌ የሚያደርጉት መሰላልን ነው። ሂሳብ ለማስተማር መሰላል ምሳሌ ይሆናል፤ አካባቢ ሳይንስ ለማስተማር መሰላሉ ይነሳል፤ በሌሎች ትምህርቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ በመሰላል ብዙ ይመሰላል። ለሽምግልና የተቀመጡ የአካባቢው ሽማግሌዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ መሰላል ለሽምግል ናቸው ምክር ማሳመሪያ የሚጠቀሙበት ምሳሌ ከሆነ አመታት አልፏዋል። በመሰላሉ ጉዳይ ግን ማንም የተለየ ጥያቄ አንስቶ የማያውቅባቸው አመታት። አንድ ቀን የተለየ ነገር ሆነ።

አንድ ቀን ከተማሪዎች መካከል አንድ ተማሪ "መሰላሉ ለምን አንድ ሆነ ለምንስ ብዙ ማድረግ አንችልም" ሲል ሀሳብ አቀረበ። ያገኘው ምላሽ አስደንጋጭና ምክንያታዊ ያልሆነ ምላሽ ነበር። አንዳንዱ "ይህን ጥያቄ ያነሳኸው በአካባቢያችን የተከበሩትን የእከሌን ገበያ ልትዘጋ አስበህ ነው" ሲል ምላሽ ሲሰጥ፤ ሌላው "ራሱን ከአባቶች በላይ ስለሚቆጥር ነው፤ በአባቶች ስራ ላይ አዲስ ሃሳብ ይዞ የሚመጣው" ሲል አስተያየት ሰጠ። ሌላው አስተያየት ሰጪ ደግሞ "በዓለም ላይ ያለው መሰላል አንድ መሆኑን ሳያውቅ ቀርቶ ነው ሌላ መሰላል ስለመስራት ያሰበው። ብቸኛውም መሰላል እዚህ መንደር ብቻ ያለ ነው። እንዴት የማይታሰብ ነገር ያስባል።" ሲል ከሰሰ።

በዚህ መሃል የመሰላል አከራዩ በራሳቸው ዓለም ሄዱ። እንዴት መሰላሉን እንደሰሩ፤ እንዴት መሰላሉ የእርሳቸው ብቸኛ መብት ተደርጎ እንዲታይ እንዳደረጉ፤ እንዴት ለአመታት የእርሳቸው መሰላል ሊተካ የሚችል እንዳይደለ አድርገው ማስረጽ እንደቻሉ፤ ይህን ሁሉ ያደረጉት ራሳቸውን በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ቦታ ለማሰጠት እንደሆነ አሰቡ። ቢሳካላቸውም ከሞቱም በኋላ በመሰላሉ ምክንያት የሚታወሱና ተቀናቃኝ የማይነሳባቸው ሆነው እንዲያልፉ ነው። አሁን የተፈጠረው ጠያቂ ልጅ ግን ከወዲሁ አሰጋቸው። ልጁ መጠየቅ ከጀመረ በቀላሉ መሰላሉ በሌላም ሰው ሊሰራ የሚችል መሆኑን በማሳየት ጉድ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንደ እዚህ ዘመን በማህበራዊ ሚዲያ ጉትጓቶ የዘመኑ ተጽእኖ ፈጣሪ ሆኖ ለመታየት እንደሚደረገው ጥረት፤ እኚህም አባታቸው በዘመናቸው እውቅና ሲሉ የቋጠሩት ቋጠሮ።

እንደተለመደው ጉድ ለአንድ ሰሞን ነውና ልጁን ሲቃወሙ የነበሩት አንድ ሰሞን ከግራ ከቀኝ ሲቃወሙት ቆዩና ሁሉም ጸጥ አሉ። ልጁ የተፈጠረው አዲስን ነገር የመቃወም፤ ቢገባንም ባይገባንም ከጥንት የመጣውን በሙሉ ትክክል አድርጎ የመቀበል አዝማሚያ ፋታ ሲል ሁለት ነገር አሰበ። አንድ የሰውዬውን መሰላል አወላልቆ መልሶ መስራት ወይንም አዲስ መሰላል ሰርቶ ማሳየት። ሁለተኛውን መንገድ መሄድን ዓላማ አደረገና አዲስ መሰላል ሰርቶ ወደ ገበያ ሊገባ አሰበ።

ቀናት ተቆጠሩና አንድ ቀን በአካባቢው ባለው ትልቅ ገበያ በተለያየ መጠን የተዘጋጀ መሰላል ለገበያ ቀረበ። ሰው ሁሉ እየፈራና እየተባ አዲሱን መሰላል መንካት ጀመረ። እየወሰደም መሞከር ጀመረ። በቅድሚያ ለአመታት ከአንድ መሰላል በስተቀር መሰላል የለም ብሎ ሲያስብ የነበረውን አስተሳሰቡ ጋር ተጋጨ። በመቀጠል ይህን አስተሳሰብ እንዲይዝ ካደረጉት ጋር ተጋጨ። ልጁ ዓላማ ብሎ የተነሰውን በተግባር አሳክቶም አሳየ። በሰፈሩ አዳዲስ ነገሮችን የማሰብ፤ ዓላማን የማሳካት፤ ዓላማን ለማሳካት ለሚገጥም መውጣት መውረድ ምሳሌም ሆነ፤ በዓላማ በስተቀር በምንም ሊሰራ የማይችለው ሁለተኛው መሰላል በሰፈሩ ተሰርቶ ወደ ስራ ገባ። የአገሬው ሰው አዲሱን መሰላል ከእጁ አድርጎ መጠቀም ሲጀምር ለአመታት አንድን ብቸኛ ተደርጎ የቀረበ መሰላል በኪራይ ለማግኘት ወረፋ ይጠብቅ የነበረበትን ዘመን አስታውሶ አዘነ።

ቀስ በቀስ የመሰላል ኪራይ እየቀረ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱን መሰላል መስራት የሚቻልበት ደረጃም ላይ ተደረሰ። መሰላል፤ መሰላል ይሆን ዘንድ የሚያስፈልገው እንጨትና ሚስማር ነውና።

ከዚህ ቀደም ከዓላማ አንጻር በዚሁ አምድ ላይ ያቀረብነውን ጽሁፍ ማስተካከያ በማድረግ እንደሚከተለው አቅርበናል።

**ዒላማ ይኑርህ!**

ወደ መሰላል የወጣ ሰውና ለአደን የወጣ ሰው ይመሳሰላሉ። ለአደን የተሰማራ ሰው ዒላማውን አስተካክሎ አንዳች ድል ይዞ መመለስ ፈልጎ ወደ ጫካው ውስጥ ይገባል። ዒላማው በራሱ ዓላማ አይደለም፤ ዓላማው ዒላማው ሲሳካ የሚሳካው ነው። ዒላማውን በትክክል አድርጎ የሰነዘረ ዒላማውን መትቶ አውሬውን ቢጥለው ነገር ግን ባዶ እጁን ተመልሶ ወደ መጣበት ቢመለስ አንዳች ችግር እንዳለበት ይቆጠራል። ምክንያቱም ሕይወቱን አስይዞ የተሰለፈበት የዒላማ ፍልሚያው ዓላማ ገድሎ መመለስ አይደለምና። ወደ መሰላል የወጣም እንዲሁ ነው፤ በመሰላል ላይ ወጥቶ ሊደርስበት የሚገባው ጫፍ አለ፤ አንዳች ነገር ደርሶ የሚሰራበት ስፍራ።

በሕይወት ጉዞ ውስጥ ሰዎች ዒላማ የሚያደርጉት ብዙ ነገር አለ። ጎበዝ ተማሪዎች ዒላማ አድርገው የደረጃ ተማሪ ለመሆን ያጠናሉ። ካሱበት ደረጃ ተንሸራተው ሲገኙ አንዳች የጎደላቸው ነገር እንዳለ እስኪሰማቸው ድረስም ይደርሳሉ። አንድ ቀን በተማሪዎች የውጤት መቀበያ ቀን አንዱ ታዳጊ ተማሪ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል። አንዳች ነገር እንደተፈጠረ እምባው በሁለቱም አቅጣጫ ይፈሳል፤ ምክንያቱ ደግሞ በአንድ ማርክ ተበልጦ ደረጃውን ማጣቱ ነበር። ዒላማ ያደረገው ነገር ነበርና ዒላማውን መምታት ባለመቻሉ የተፈጠረበት ሃዘን።

ከግለሰብ አልፎ የዒላማ ነገር በተቋማት ውስጥም ይሰራል። ተቋማት ግብ/ታርጌት አስቀምጠው እያንዳንዱ ሰራተኛ እንደ ግለሰብ፤ ከእያንዳንዱ የስራ ክፍል እንደ ክፍል፤ ከአጠቃላይ ድርጅቱ እንደ ድርጅት ዒላማ ይደረጋል። ዒላማውም ይሳካ ዘንድ የተለያዩ ተግባራትም ይከናወናሉ። ዒላማ በአግባቡ ታልሞ ውጤት ሲመጣ ደስታ ይሆናል። ዒላማ የተደረገው ነገር ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ ምክንያቱ ይገመገምና የማስተካከያ መንገድ ይቀየስለታል፤ በዚሁ መንገድ የዒላማ ጉዞ ይቀጥላል።

ዒላማ ማድረግን እንደ ባህል በአደጉት አገራት ዘንድ የተለመደ ነው። ጃፓኖች የማኔጅመንት ሳይንስ እንዲዳበር የአሰራር ማሻሻልን በየጊዜው በማድረግ ዒላማን መምታት የሚቻልበት ደረጃ ላይ መድረስ እንዲቻል ምሳሌ የሚሆኑ አሰራሮችን ለዓለም አስተዋውቀዋል። ዒላማን ትኩረት ያደረጉ በጥራት፣ በሰው ኃይል አስተዳደር፣ በንግድ አስተዳደር፣ በንብረት አያያዝ ወዘተ ውስጥ አሰራሮችን አስተዋውቀው ውጤታማም ሆነዋል።

አንባቢው አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ዒላማን በማለም ልምድ ያለው ሊሆን ይችላል። አንዳንዱ ሰው የአዲስ አመት እቅድን በልኩ አቅዶ ተግብሮ ራሱን ገምግሞ የመሸለም ልማድም አለው። በሂደት ውስጥ ከዛሬ ነገን በስራ መቀየር። ዒላማ እዚህ ውስጥ ያለው ድርሻ ትልቅ ነው። ዒላማ የምናደርገው ነገር ግልጽ ነው። በቁጥርም፤ በስፋትም፤ በርዝመትም ወይንም በሆነ አንዳች መለኪያ አማካኝነት የሚለካ ስለሆነ። በመሰላል ላይ የወጣ ለምን በመሰላል ላይ እንደወጣ ካላወቀ ችግር ነው።

ዒላማ አድርጎ ቀኑን በሰዓት ከፋፍሎ የሚንቀሳቀስና እንዲሁ ቅርጽ በሌለው አካሄድ ቀኖቹን ተቀብሎ የሚሸኝ ተመሳሳይ ውጤት ሊኖራቸው አይችልም። ተማሪው፣ አርሶ አደሩ፣ ነጋዴው፣ ሰራተኛው ወዘተ በዒላማ ውስጥ ስራቸውን ያከናውኑ ዘንድ ይመከራል፤ በዚህ መንገድ የሚያከናውኑት ለውጤት ደርሰው ይታያል። ከፍ ያለው ጥያቄ ግን ዓላማ ነው፤ ከዒላማ የሚገዝፈው፤ የዒላማ ድምር ውጤት የሚገልጸው። በትውልዱ ውስጥ ቦታ የተነፈገ የሚመስለው በዒላማ ተሸፍኖ የሚኖረው፤ ዓላማ!

**ዓላማ ይኑርህ!**

ማርክ ትዌይን የተባለ አሜሪካዊ ፀሀፊ "በሕይወት ውስጥ ወሳኝ የሆኑት ሁለት ቀናት አንደኛው የተወለድክበት ሲሆን ሁለተኛው የሕይወትህን ዓላማ ያገኘህበት ነው" ይላል። ዓላማ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ቦታ በሚገባ የሚያሳይ አባባል ነው።

የስድብ ጥሩ ባይኖረውም "ዓላማ ቢስ" የሚል ስድብ የሰዎችን ስሜት የመንካት አቅሙ ከፍተኛ ነው። ማንም ሰው ዓላማ ቢስ እንደሆነ ተደርጎ እንዲቆጠር አይፈልግም። በዘመናት መካከል አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ የደረሰችበት ምእራፍ ላይ ለመድረስ ያለፉ በርካታ ስልጣኔዎችን አልፋለች። እያንዳንዱ ዘመን ይዞት የነበረው ስልጣኔ በታሪክ መዝገብ ውስጥ ተጽፎ ከሚገኘው ባሻገር በእያንዳንዱ አካባቢ አሻራው ዛሬም ድረስ ይታያል። ኢትዮጵያውያን አንድ ሰው ዓላማ ብሎ የያዘውን ነገር ዳር በማድረስ ውስጥ የሚሰጡት ሙገሳ ወይንም አድናቆት የታሪካችን አካል ነው። ከዚህ አንጻር "ዓላማ ቢስ" የሚለው ቃል ለአንድ ኢትዮጵያዊ ስሜትን የሚጎዳ ቢሆን ሊገርመን አይችልም።

ቤተሰቦች ልጆቻቸው ትምህርትን በአግባቡ እንዲያጠኑ፤ በአግባቡ እንዲከታተሉ ሲመክሩ ትምህርትን እንደ ዓላማ አድርገው በማቅረብ ነው። ሴት ልጅ ከሆነች ደግሞ ከዓላማዋ ሳትዘናጋ ትምህርቷን ዓላማ አድርጋ እንድትማር ትመከራለች። ለሃላፊነት ብቁ ሳይሆን ወደ ጾታዊ ግንኙነት መሄድም እንዲሁ ከዓላማ መስመር መሳት ተደርጎም ይቀርባል። አባቶቻችን በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ገብተው ሳይማሩ ከግል ሕይወት ተነስቶ እስከ አገር ድረስ በዓላማ ውስጥ የመኖርን አስፈላጊነትን ይገልጻሉ።

ባለንበት ዘመን ደግሞ ዓላማ የሚባለው ነገር ፈጽሞውኑ የጠፋ ነው ባንል እንኳን እየደበዘዘ የሄደበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ዓላማ እጅግ ጠቦ በየትም በኩል ተደርጐ ገንዘብ ላይ መድረስ የሚለው የሕይወት ዘይቤ የሰፋ ይመስላል። በስራ መንገድ ገንዘብ ላይ መድረስ የሚጠበቅ ቢሆንም ባልተገባ ስራ መድረስ እንዲሁም መነሻ ዓላማቸው ገንዘብ ባልሆኑ ዘርፎች እንደ ሃይማኖት፤ ፖለቲካ፤ ሕዝብ አስተዳደር ወዘተ ከብዙሃን ጋር በሚሰጥ አገልግሎት ውስጥም ታልፎ ገንዘብ ጋር መድረስን ግብ የሆነበት ዘመን ላይ መገኘት አሳዛኝ ነው። ዓላማ በገንዘብና በእውቅና ለመለካት የተሄደበት እርቀት ብዙ እንደሆነ በግልጽ የሚታይበት ወቅት።

መነሻችንን ዒላማ ያደረግነው በዒላማ ስሌት ዓላማ እየወደቀ ስላለ ነው። ገንዘብ የማግኘት ዒላማ ወይም ግብ ያለው ሰው በማንኛውም መንገድ አድርጎ ገንዘብ ጋር መድረስን ከሆነ የሚያስበው በመደበኛ ንግድ ገንዘብ ጋር ከመድረስ በኮንትሮባንድ መንገድ ላይ መሄድን ሊመርጥ ይችላል። በሙስና ገንዘብ ላይ መድረስን ዒላማ ያደረገ ሰው ካለበት አንድ ኃላፊነት ወደሚከተለው ሲያድግ ዒላማው በተጨማሪ ሃላፊነት ህዝብን ማገልገል መሆኑ ይቀርና ለበለጠ ሌብነት ልምምድ እያደረገ ይሰነብታል።

የዒላማ ሕይወት በዓላማ ውስጥ ሲሆን እጅግ ጠቃሚ መሆኑን የሚያስረዱ አያሌ የማኔጅመንት ሳይንስ ጽንሰ ሃሳቦች አሉ። እውነታው ግን ዓላማ የለሽ በመሆን ውስጥ የበቀሉት ዒላማዎች ትርጉማቸው ማትረፍ እየመሰሉ መክሰር፤ ማግኘት እየመሰለ ማጣት፤ መገኘት እየመሰለ መጥፋት ነው። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ሊባል የሚችልባቸው ክስተቶች በየፌርማታው ከዓላማ አንጻር በዝቷል። ያል እጅ መንሻ ውጤት ማግኘት በማይታስብበት ዘመን ውስጥ ስንኖር በተለመደው መንገድ ወጥቶ



የሚገባው ዓላማውን ለማሳካት በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆን አዋጭ እንዳልሆነ በማሰብ ተስፋው እየተሸረሸረ ሊሄድ ይችላል።

**የዓላማ ሕይወት**

ዓላማን ውስብስብ አድርጎ ከማቅረብ በቀላሉ "ሰዎችን ማእከል አድርገን ልንኖረው የተገባው ሕይወት" ብለን ልናየው እንችላለን። በምድር ላይ የምንኖረው ኑሮ በጊዜ ገደብ የተገደበ መሆኑ እሙን ነው። ሰው በመሆናችን በውስንነት ውስጥም እንኖራለን። በዚህ ሁኔታ ምድር ላይ ስንኖር ዓላማ ትልቁ ስንቃችን ነው፤ ልንኖር የተገባውን ሕይወት ላይ ያደረስነው ውሳኔም ነው።

እንደ ግለሰብ በውስጣችን ያለውን ተሰጥኦ ተጠቅመን ልንኖር የምንፈልገውን ሕይወት ለመኖር እውቀትን ማእከል አድርገን ስንመላለስ እርሱ ዓላማ ነው። የዓላማ ሕይወት ራስን ፈልጎ በማግኘት ለሌሎች የሚመነዘር ማድረግ ነው። አንድ ሰው በቁጥር አንድ ቢሆንም ለራሱ በቂውን ጊዜ ሰጥቶ ራሱን ፈልጎ ባገኘበት እርቀት ለብዙዎች የሚመነዘር ሊሆን ይችላል። የዓላማ ሕይወት ሰዎች ግራ ተጋብተው በሚኖሩበት ሁኔታ ውስጥ የተረጋጋን ሕይወት እንድንኖር የሚረዳ ነው። ራስን ፈልጎ ማግኘት በውጤቱም ለሌሎች መድረስ። ሮበርት ኤፍ. ኬኔዲ "የሕይወት ዓላማ ነገሮችን መልካም ለማድረግ በሆነ መንገድ የምናደርገው አስተዋጽኦ ነው" በማለት ዓላማን ከራስ አጥር ባሻገር መመልከት እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ሲሆን የውስጥ ጩኸት ምላሽ መስጠት፤ ከፈጣሪም ከተፈጥሮም ጋር ታርቆ የመኖር ሕይወት ይከተላል። ተልእኮ አድርጎ የሚወሰድን ነገር ዳር ማድረስ የሚያስችል ሕይወትም ይሆናል።

በመቃብራችን ላይ የሚገኙ ሰዎች ምን አድርገን እንዳለፍን ቢያውቁ ደስ ይለናል። የተጣላን አስታራቂ፣ ተስፋ ላጡ ተስፋን መመለስ፣ የተራቡትን የሚያበላ፣ በስራው ታታሪ ሆኖ ብዙ የስራ እድል የፈጠረ፣ ወይንስ ምን? ፒካሶ እንዲህ ይላሉ "የሕይወት ትርጉም ስጦታህን ማወቅ ነው።" የሕይወት ዓላማ ደግሞ ስጦታህን ለሌሎች መስጠት።

ዓላማ በተቻለው መጠን ራስን ማእከል ከማድረግ ወጥቶ ሌሎችን የሚያስብ ቢሆን እያንዳንዱ ርምጃ አስደሳች ይሆናል። አንድ ሰው ነግዶ ገንዘብ ማግኘት ቢፈልግ እንደ ዓላማ መያዝ ያለበት በሚሰራው የንግድ ስራ ሰዎችን የሚጠቅምበትን ነው። ለአርሶ አደሩ የሆነ እቃ አቅርቦ የአርሶ አደሩን የሆነን ችግር ፈቶ ገንዘብ ማግኘት ሲሆን ትርጉሙ እንዲሁ ነግዶ ገንዘብ ማግኘት ከሚል ዓላማ ይሻላል። ገንዘብ ማግኘት ዒላማ ሲሆን የሚሰራው ስራ የሚጨምረው እሴት ግን ዓላማ ነው።

የማይጠየቁ ብዙ ነገሮች በዙሪያችን አሉ። መጠየቅ ሲጀምሩ ወደ መልስ መድረስ ይቻላል። የዓላማ ሕይወትም ውጪውን ሳይፈሩ ወደ ውስጥ በመጠየቅ የሚኖር ሕይወት ነው። ይህን ሕይወት ብዙዎች አይኖሩትም፤ ጥቂቶች እንጂ!

## ስኬት

# ከራስ አልፎ ለሌሎች የመትረፍ ፀጋ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ብዙዎች የስኬትን ትርጉም በራሳቸው መስፈርት ለክተው ያስቀምጡታል። አንዳንዶች ደግሞ የወል ትርጉም ሰጥተውት በዚያ መለኪያ ስኬታማ ሰዎችን ይበይኑበታል፤ አድናቆትና ከመስጠት ባሻገር ስኬታማውን ሰው አሊያም ተቋም እንደ በጎ ምሳሌና አርአያ ይመለከቱታል። ሁለቱም አካሄዶች መስፈርቱን ባወጡት አካላት እይታ ትክክል ቢሆኑም፣ አብዛኛውን ጊዜ ስኬት የሚመዘነው ብዙሃኑ በሚስማማበት መለኪያ እንደሆነ ይታመናል።

ስኬት እንዲያው በቀላሉ የሚደረስበት ሳይሆን ከራስ አልፎ ለብዙሃን ብርሃን መሆን፤ ለመድረስ ዋጋና ጥረትን የሚያስከፍል መንገድን በትጋትና በትእግስት የመጓዝ ወኔን፤ እየወደቁ መነሳትን፣ ከስህተት መማርን፣ ታናናሾችን ማድመጥና ሁሌም ለመማር ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል፤ ዳገት ቁልቁለት የበዛበት ጭምርም ነው። መጨረሻው ግን ሃሴትን የሚያላብስ፣ በብዙዎች ምሳሌ የመሆን ሞገስን የሚያጎናፅፍ ሙሉ የመሆን ፀጋ ነው።

የዝግጅት ክፍላችን ሁሌም በዛሬው እለት በስኬት አምዱ ላይ ግለሰቦች፣ ተቋማትና ሌሎችም አገርንና ማህበረሰብን በሚጠቅም መስክ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን እየጋበዘ ስኬት የተጎናጸፉበትን መንገድ ቀጣይ ጉዟቸውን ያመላክታል። ከልምዳቸው እየጨለፈ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ለሌሎች ትምህርት እንደሚሆን ይጋብዛል።

በዛሬው እለትም አንድ እንግዳ ይዞላችሁ ቀርቧል። እንደ ከዚህ ቀደሙ በስኬት መለኪያ መነፅራችን ውስጥ ከገቡት መካከልም ኤልሳቤጥና ታደለ የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ህብረት የሽርክና ማህበር አንዱ ነው። ማህበሩ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ እንዲሁም በፕላስቲክ ምርት ተሰማርቶ በጊዜ ሂደት ውጤታማ እየሆነ መጥቷል።

ማህበሩ ከቆዳ የተሠሩ የህጻናትና የአዋቂ ጫማዎችን እንዲሁም ቦርሳዎችን እያመረተ ለገበያ ያቀርባል። ከቆዳ በተጨማሪም ፕላስቲክ ጫማዎችን በማምረት ለገበያ እያቀረበ የሚገኘው ይህ ማህበር ከተቋቋመ ከአስር ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በአሁኑ ወቅት እያመረታቸው ያሉ የቆዳ ጫማዎችና ቦርሳዎች በተለይም በእጅ የሚሠሩ ክፍት የቆዳ ጫማዎች ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያም ተፈላጊም ናቸው።

የማህበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ታደለ ሽፈራሁ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ነው። ጫማ ወደ ማምረት ሥራ የገቡበትን አጋጣሚ፣ ዛሬ ላይ ለመድረስ ያሳለፉትን ውጣ ውረድ እንዲሁም ያለፉባቸውን መንገዶች አጫውተውናል። ገና በልጅነት ዕድሜያቸው ከቤተሰብ ተለይተው ለመኖር አስገዳጅ ሁኔታ የገጠማቸው አቶ ታደለ፣ ሕይወትን ለማሸነፍ ሲሉ ሥራ ሳይመርጡ በትጋት ሰርተዋል።

የልጅነት ዕድሜያቸውን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች አሳልፈዋል፤ ካለፉባቸው የሙያ ዘርፎች መካከል ለጫማ ሥራ አድልተዋል። አብዛኞቹ አጋጣሚዎቻቸውም ወደ ጫማ ሥራ ይገፉቸው እንደነበርም ያስታውሳሉ። ያገኙትን ሁሉ ሠርተው ማለፍ ቢችሉም የጫማ ሥራ ሙያን ግን እስካሁን ሳይተው ዛሬም ድረስ ይዘውት ቆይተዋል። ይህን ስራ መተዳደሪያቸው ከማድረግ ባለፈም ሙያውን ለሌሎች በማስተማር ከ20 ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል።

‹‹በወቅቱ ወደ ዘርፉ እንድገባ ያደረገኝ ለሙያው የነበረኝ ፍላጎትና ድፍረት ነው›› የሚሉት አቶ ታደለ፤ አንበሳ ጫማ ፋብሪካ ተቀጥረው ይሠሩ ነበር። በፋብሪካው በቆዩበት ጊዜም ለሙያው የነበራቸው ቅርበት የተሻለ በመሆኑ ብዙ እውቀት ቀስመዋል። በቆይታቸው የጫማ ሥራ ሙያን ጥንቅቅ አድርገው ባያውቁም በለቀቁ ጊዜ ግን የጫማ ሥራን በግላቸው ለመሥራት እንዲዘጋጁ ረድቷቸዋል። በወቅቱም የጫማ ጥገና እና የልክ ጫማ ሥራን ነበር የጀመሩት።

ለሙያው ያላቸውን ፍላጎትና በጥቂቱም ቢሆን በአንበሳ ጫማ ፋብሪካ የቀሰሙትን ልምድ ተጠቅመው ወደ ሥራው ለመግባት ጊዜ ያልፈጁት አቶ ታደለ፤ ሥራውን ወደ ክልል ቢወስዱት አዋጭ እንደሆነ አመኑ። ጉዟቸውን ሀዋሳና ሻሸመኔ በማድረግ በሁለቱም ከተሞች የጫማ ጥገናና የልክ ሥራ (የሰዎችን እግር ለክተው) ሠርተዋል። በየዕለቱ በሚያደርጉት ጥረትም ከጫማ ሥራ ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ረዳቸው። የራሳቸውን ሙያ ከማሻሻል አልፈው ለሌሎች ማስተማር ጀመሩ።

ሙያቸውን ለሌሎች በማስተማርም ከነበራቸው ልምድ ጋር ቴክኖሎጂው በእጅጉ ያገዛቸው እንደሆነ የሚያነሱት አቶ ታደለ፤ የእውቀት ሽግግሩን የጀመሩትም በሀዋሳና በሻሸመኔ ከተማ ነበር። ወደ አዲስ አበባ በተመለሱ ጊዜም ብሩህ ተስፋ ከተባለ የውጭ ድርጅት ጋር በጋራ የሠሩ ሲሆን፤ ድርጅቱ የጎዳና ልጆችን ከየጥጋ ጥጉ ሰብስቦ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ያሰለጥንም ነበር። በወቅቱ በጋራ ለመሥራት ሲወስኑ ከሚከፈላቸው ደመወዝ ይልቅ ድርጅቱ ይዞት የመጣው ሃሳብ እጅጉን አስደስቷቸዋል።

‹‹ብሩህ ተስፋ የተባለው የውጭ ድርጅት ጎዳና ላይ የወደቁ በርካታ ወጣቶችን አንስቶ የተሻሉና ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ አድርጓል። እኔም የዚህ በጎ ተግባር አካል ብሆን በብዙ አተርፋለሁ በማለት ነው የተቀላቀልኩት›› የሚሉት አቶ ታደለ፤ በወቅቱም ከጎዳና የተሰባሰቡት ወጣቶች እንደየፍላጎታቸው የተለያየ ሙያ ይማሩ እንደነበር ይናገራሉ። የጫማ ሥራ ሙያን ለመማር የፈቀዱትንም በነበራቸው ፈቃደኝነትና ተነሳሽነት አስተምረው በርካቶችን ባለሙያ ማድረግ ችለዋል።

በጊዜው 1800 የሚደርሱ ወጣቶች የጫማ ሥራ ሙያን ከአቶ ታደለ እጅ ተምረዋል። አብዛኞዎቹም ወደ ስራ የገቡ ሲሆን አንበሳና ጥቁር አባይ ጫማ ፋብሪካን ጨምሮ በተለያዩ ፋብሪካዎች ተቀጥረው እየሠሩ የሚገኙ አሉ። ተቀጥረው ከሚሰሩት ባለፈም በግላቸው አምራች የሆኑ ስለመኖራቸው ምስክር እንደሆኑ ገልጸው በዚህም እጅጉን ደስተኛ እንደነበሩ ያስታውሳሉ።

በጫማ ፋብሪካ ተቀጥሮ ከመሥራት ጀምሮ የተቀደዱ ጫማዎችን መጠገን፣ ጫማ ለክቶ በመሥራትና ሙያውን ለበርካቶች ሲያስተምሩ የቆዩት አቶ ታደለ፤ በአሁኑ ወቅት ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ኤልሳቤጥ ፍቅሬ ጋር በመሆን የተለያዩ የቆዳና የፕላስቲክ ውጤቶችን እያመረቱ ይገኛሉ። ‹‹ከትናንት ተነስተን ዛሬ ላይ ለመድረሳችን ምክንያቱ የባለቤቴ ጥንካሬ ነው›› የሚሉት አቶ ታደለ፤ ወደ ማምረት ከመግባታቸው አስቀድሞ ባለቤታቸው በምርት ሂደት እንከን የገጠማቸውን ጫማዎች ከተለያዩ ጫማ አምራቾች በመረከብ ያለመሰልቸት ተዘዋውረው ይሸጡ እንደነበር ያስታውሳሉ።

በአንድ አጋጣሚ መንግሥት ባመቻቸው ዕድል ተደራጅተው ሁለት በሁለት የሆነ ቦታ ያገኙት ወይዘሮ ኤልሳቤጥ፤ ትጉህና ታታሪ በመሆናቸው በዛችው ቦታ ጫማ ይሰፉ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ቦታውን በቆርቆሮ በመከለል አንድ ሲንጀር የስፌት መኪና ገዝተው ወደ ሥራው የገቡት አቶ ታደለ፤ የጫማ ሥራ ሙያን ለባለቤታቸው ቀደም ብለው ያስተማሯቸው በመሆኑ ወደ ሥራው ለመግባት ብዙም አልተቸገሩም። ወይዘሮ ኤልሳቤጥ፤ የተማሩትን የጫማ ሥራ በተግባር በማሳየት እርሳቸው ሲሰፉ አቶ ታደለ ደግሞ የውጭውን ሥራ (ዕቃ የማቅረብ) ይሠሩ ነበር።

ቀስ በቀስ የጀመሩት ጫማ የማምረት ሥራ አሁን ከመንግሥት ባገኙት የማምረቻ ቦታ ላይ በስፋትና በአይነት እያመረቱ ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያም ማቅረባቸውን ቀጥለዋል። ሲጀምሩ አንድ ሲንጀር መኪና የነበራቸው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት 12 መስፊያ ማሽኖች፣ የተለያዩ መላጫ ማሽኖች፣ ሶል ማጣበቂያ ማሽኖች፣ ቤዛ ማሽንና ሌሎችንም በማፍራት አንድ ጫማ ፋብሪካ ሊኖረው የሚገባውን ማሽኖች በማሟላት ምርቶቻቸውን በጥራት እያመረቱ ይገኛሉ።



አቶ ታደለ ሽፈራሁ

ከምርቶቻቸው መካከልም የህጻናትና የአዋቂ የቆዳ ጫማዎችና ፕላስቲክ ጫማዎች ይገኙበታል። ፕላስቲክ ጫማዎቻቸውን የሚያመርቱት መልሰው ጥቅም ላይ በሚውሉ የተጣሉ ፕላስቲካ ጫማዎች በመሆኑ ለየት ያደርጋቸዋል። አገልግሎታቸውን ያጠናቀቁና በየአካባቢው ተጥለው የሚገኙ ፕላስቲክ ጫማዎችን በኪሎ ገዝተው መልሶ ጥቅም ላይ መዋል እንዲችል ሲያደርጉም ጫማዎቹ ጸድተውና ተፈጭተው አዳዲስ ፕላስቲክ ጫማዎች የመሆን ዕድል አላቸው። ይህም ጫማዎቹ አካባቢን እንዳይበክሉ ከማድረግ ባለፈ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ አስችሏል፤ ያገለገሉ የፕላስቲክ ጫማዎች ሰብስበው ለሚያመጡ ሰዎችም የገቢ ምንጭ እንዲፈጠርላቸው አግዟል።

የሚያመርቷቸው ጫማዎችና ቦርሳዎችም ቆዳ በቆዳ የሆኑና በተሻለ ጥራት የሚመረቱ ስለመሆናቸው ያነሱት አቶ ታደለ፤ በተለይም ክፍት የቆዳ ጫማዎቹን ከአገር ውስጥ ባለፈ ወደ ቻይና፣ ሱዳን፣ ኬንያና ታንዛንያ እንደሚልኩ ተናግረዋል። ድርጅቱ ጫማዎቹን ወደ እነዚህ አገሮች የሚልከው በቀጥታ ሳይሆን በወኪሎች አማካኝነት ነው። በአገር ውስጥ ደግሞ በተለያዩ ክልሎች በተለይም በምስራቁ የአገሪቱ ክፍል በስፋት ይፈለጋሉ።

በአሁኑ ወቅትም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ሱቅ ይዘው የሚሸጡ ደንበኞች አሏቸው። የቆዳ ጫማዎቹ በእጅ የመሥራት ሂደትን የሚከተሉ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ታደለ፤ ምርቶቻቸው የሚፈለጉትም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ያስረዳሉ። የሚጠቀሙት ሶልም ምቾት ያላቸውና ቡሽ በመሆናቸው ተመራጭነታቸውን ከፍ አድርጎታል።

“በአሁኑ ወቅት ቡሽ ሶል ለማምረት አስፈላጊ የሆነውን ጥሬ ዕቃ ማግኘት አልተቻለም” የሚሉት አቶ ታደለ፣ ያም ሆኖ በአገር ውስጥ የሚገኝ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ የመተካት ሥራ እየሠሩ መሆኑን ይናገራሉ። በዚህም እንደ ከተማ ሞዴል በመሆን ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የዕውቅና ሰርተፍኬት አግኝተው ተሸላሚ ሆነዋል።

ሶልን በአገር ውስጥ ምርት ተክተው ከመሥራታቸው በተጨማሪ አገልግሎታቸው ያበቃላቸውን ፕላስቲክ ጫማዎችን በኪሎ ገዝተው አጽድተውና የተለያዩ ኬሚካሎችን ተጠቅመው በከፍተኛ ሙቀት በማቅለጥ በተለያዩ ሞልዶች ውስጥ እያስገበ በሁለት የተለያዩ ቀለማት ጫማዎችን እያመረቱ ናቸው። እነዚህ ጫማዎችም በአብዛኛው ወደ ክልል የሚላኩ ሲሆን በተለይም በሰሜኑ የአገሪቷ አካባቢዎች የሚዘወተሩ ጫማዎች እንደሆኑም ነግረውናል።

የሶልና የፒፒሲ ወይም የፕላስቲክ ጫማ ፋብሪካው በቀን 3600 ጫማ ወይም ሶሎችን የማምረት አቅም እንዳለው አቶ ታደለ ይናገራሉ። 28 ሠራተኞችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ ይችላል። ሁለት ቀለም ያላቸው ፕላስቲክ ጫማዎችን ያመርታል።

የቆዳ ምርት የሆኑት ጫማዎች አብዛኛው ሥራ በእጅ የሚከናወን በመሆኑም በቀን ከ70 እስከ 90 የሚደርስ የሰው ኃይል ይፈልጋል። በአሁኑ ወቅት ገበያው የተቀዛቀዘ በመሆኑ እስከ 20 ሠራተኞች ይሳተፋሉ። በተለያዩ የገጠር አካባቢዎች የሚዘወተረው ፕላስቲክ ጫማ እንደመሆኑ ይመረታል። በተለይም በሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል በስፋት የሚፈለጉ ቢሆንም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲዚህ ግን በአካባቢው በነበረው ጦርነት ምክንያት ገበያው መቀዛቀዙን ገልጸዋል። አስቀድመው ከላኳቸው ጫማዎች ገንዘብ መቀበል እንዳልቻሉና በርካታ ቁጥር ያላቸው ጫማዎችም ወደ አካባቢው ገበያ መላክ እንዳልቻሉ ነው ያስታወሱት።

በአገሪቱ ለሁለት ዓመታት የቆየው ጦርነት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳት ማድረሱን አንስተው በድርጅታቸውም ተመሳሳይ ኪሳራ አስከትሎባቸው ማለፉን ይናገራሉ። ይሁን እንጂ አሁን በመጣው ሰላም ትልቅ ተስፋ መሰነቃቸውን አልሸሸጉም። ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን ጠቅሰው፤ ዘላቂ ከሆነ ምርቶቻቸውን እንደቀደመው ለማምረትና ወደ ገበያው ለመግባት በዝግጅት ላይ እንደሆኑ ገልጸዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ሴሳው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ፈተና

# የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች እጥረትና የዋጋ ንረት

መሳኩ ሌሮሴ



ግንባታን ውብ እና ማራኪ ከሚያደርጉት መካከል የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች ይጠቀሳሉ። ህንጻ የታለመለትን አገልግሎት በአግባቡ መስጠት እንዲችል፣ ህንጻውን የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ከመከላከል ባሻገር ከመበስበስ እና ከዝገትም በመከላከል በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉም ይገለጻል።

ከሴራሚክ፣ ከእንጨት፣ ከወረቀት፣ ከፕላስቲክ እቃዎች እና ከብረት፣ ወዘተ. የሚመረቱት እነዚህ የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች፣ ለግንባታው ዘርፍ እጅግ ወሳኝ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች አቅርቦት ላይ የተከናወነው ተግባር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ ላለፉት 30 ዓመታት የነበራት አንድ የሴራሚክ ፋብሪካ ብቻ ነው።

በቅርቡ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ባካሄደው አውደ ጥናት ላይ ንግግር ያደረጉት የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ወንድሙ ሴታ እንደተናገሩት፤ በአገሪቱ ውስጥ የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች ከፍተኛ ፍጆታ አለ። ሁሉም የግንባታ ፕሮጀክቶች የማጠናቀቂያ እቃ ይፈልጋሉ። የግንባታ ማጠናቀቂያ እቃዎች እጥረት እና የዋጋ መናር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን እየተፈታተኑ ካሉ ችግሮች አንዱ ነው።

የህንጻ ማጠናቀቂያ ምርቶች ከፍተኛ ፍጆታ እና ፍላጎት ቢኖርም፣ በአገሪቱ የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች ማምረቻ ፋብሪካዎችን በማቋቋም እና በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ ክፍተት ይስተዋላል። ሴራሚክን በአብነት በመጥቀስ ሲያብራሩ አገሪቱ የነበራት አንድ የታቦር ሴራሚክ ፋብሪካ ብቻ ነው። እሱም ያረጀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቂ አቅም የለውም።

ለሴራሚክ የሚሆን ግብዓት በአገር ውስጥ እንዳለም ተናግረው፣ በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ እየዋለ ግን አለመሆኑን ነው ያመለከቱት። ተመርቶ እየቀረበ ያለው ሴራሚክም የጥራት ጉድለት የሚስተዋልበት፣ ዋጋውም ከፍ ያለና የቅሬታ ምንጭ ሲሆን የሚስተዋል እንደሆነ ያብራራሉ። በሌሎች የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች ላይ የተከናወነው ተግባርም እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው የጠቀሱት።

በመሆኑም ለማጠናቀቂያ ለወለል ንጣፍ የሚውል ሴራሚክ በአብዛኛው ከውጭ አገራት ይገባል፤ ይህም በገበያ ተለዋዋጭነት ወጪው በየጊዜው ከፍ እያለ ዘርፉን እየፈተነ ይገኛል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገሪቱ ባጋጠማት የውጭ ምንዛሪ እጥረት የሴራሚክ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየናረ መምጣቱ ይነገራል።

በግንባታ ማጠናቀቂያ ላይ የተፈጠረው ችግር በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ አሉታዊ ጫና ከማሳደሩ ባሻገር በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ላይም አሉታዊ ጫና እያሳደረ ይገኛል ያሉት አቶ ወንድሙ፤ በግንባታ ማጠናቀቂያ እጥረት ምክንያት በርካታ ፕሮጀክቶች እስከመቋረጥ መድረሳቸውን ነው የጠቆሙት።

እንደ አቶ ወንድሙ ማብራሪያ፤ የኮንስትራክሽን ማጠናቀቂያ እቃዎችን ለማምረት የሚያስችል አቅም አገር ውስጥ አለ። በተለይም ማርብል እና ግራናይት ለማምረት የሚያስችል በቂ ክምችትም አለ። ከጎጃም እስከ ሐረር፤ ከጋምቤላ እስከ ቤኒሻንጉል በቂ ክምችት አለ። ግን ያንን ክምችት አውጥቶ በአግባቡ ፕሮሰስ አድርጎ ለግንባታ በሚያስፈልገው የጥራት ደረጃ ልክ ማምረት ላይ ግን ችግር ይስተዋላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ ዘርፍ ተስፋ ሰጪ ስራዎችን መስራት እንደሚቻል ፍንጭ እየታየ ነው የሚሉት አቶ ወንድሙ፣ በተለይም በቅርቡ በተካሄደው የማዕድን ኤክስፖ ላይ በጣም ብዙ ኩባንያዎች የግንባታ ማጠናቀቂያዎችን ወደ ማምረት እየገቡ መሆናቸውን መመልከታቸውን ጠቅሰዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚገባውን ምርት በአገር ውስጥ መሸፈን የሚቻልበት እድል መኖሩንም ጠቁመዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተጨማሪ የግንባታ ማጠናቀቂያ ፋብሪካዎች ወደ ስራ እየገቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በኦሮሚያ ክልል ዱከም ከተማ ላይ አንድ ሴራሚክ ማምረቻ ፋብሪካ ወደ ስራ እየገባ መሆኑን ጠቅሰዋል። በአማራ ክልል በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ በአረርቲ ከተማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኘው የአረርቲ ሴራሚክ ፋብሪካም እንዲሁ ወደ ስራ ገብቷል ሲሉ ያብራራሉ። አረርቲ ሴራሚክ ፋብሪካ በቀን እስከ 20 ሺህ ሜትር ስኩየር ሴራሚክ የማምረት አቅም እንዳለውም ጠቁመዋል።

እነዚህ ሁለቱ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ማምረት ከገቡ የሴራሚክ ችግሩን በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአገሪቱ ያለውን የሴራሚክ ምርት እጥረት ለመፍታት ሁለቱ ፋብሪካዎች መጨመራቸው ግን በቂ አይደለም ይላሉ። ተጨማሪ ፋብሪካዎችን ማቋቋምና ወደ ስራ ማስገባት እንደሚያስፈልግም ገልጸው፣ ለፋብሪካዎቹ የሚያስፈልገው ሙሉ ጥሬ እቃ አገር ውስጥ እንዳለም አመልክተዋል።

በአውደ ጥናቱ ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት አቶ ዘሪሁን ዘገየ እንደሚሉት፤ ከ2006 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ሶስት ነጥብ 34 ቢሊየን ብር የሚገመቱ የተለያዩ አይነቶች የሴራሚክስ ምርቶች በአገር ውስጥ ተመርተው ግብይት ተፈጽሞባቸዋል። ከ2006 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ አምስት ነጥብ 79 ቢሊየን ብር የሚጠጋ የሴራሚክስ ምርት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ገብቷል። ይህም የሚያመላክተው አገሪቱ ሴራሚክ ለማስገባት ብቻ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንደምታወጣ ነው።

ሴራሚክን ጨምሮ ሌሎች የህንጻ ማጠናቀቂያ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች አብዛኛውን ግብዓት ከውጭ አገራት የሚያስገቡ መሆናቸውም የምርት እጥረቱ እና የዋጋ መናር እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል ሲሉ ይጠቁማሉ። በአንዳንድ ወቅቶች የማጠናቀቂያ ምርቶች እጅግ ከመወደዳቸው የተነሳ በአገር ውስጥ ጭምር በዶላር ይሸጡ እንደነበር ጥናት አቅራቢው በመጥቀስ፣ አቅራቢዎቹ ለምን በዶላር ሆነ ተብለው ሲጠየቁ ማጠናቀቂያ ምርቶችን በዶላር ስለምናስገባ ነው በማለት በዶላር ግብይት እንዲፈጸም ሲያደርጉ እንደነበር ተናግረዋል። ይህም የቅሬታ ምንጭ ሆኖ እንደነበር ነው ያስታወሱት።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ይህ ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ከማሳደሩም ባሻገር የሰውን የመግዛት አቅም የሚያዳክም በመሆኑ ልዩ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል። ይህንን ችግር ለመፍታት ለፋብሪካዎቹ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ከአገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

የሴራሚክስ የአገር ውስጥ ምርትን ለማበረታታት በአሁኑ ወቅት ጥረቶች ቢደረጉም፣ የህንጻ ባለቤቶች ለአገር ውስጥ ምርት የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑ የአገር ውስጥ ምርት በሚፈለገው ልክ እንዳያድግ ምክንያት ሆኗል ሲሉም ያብራራሉ። ከአመለካከት ጀምሮ ለአገር ውስጥ ምርት ያለው ግንዛቤ የተዛባ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በአገር ውስጥ የሴራሚክ ምርት ላይ የተዛባ ግንዛቤ እንዳለም ነው ያመለከቱት፤ ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ የአገር ውስጥ ምርቶች በጥራት፣ በጥንካሬ፣ በውበት፣ በበቂ መጠን አለመመረታቸው ተመራጭ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ዘርይሁን መረጃ፤ ከግንባታ ማጠናቀቂያዎች መካከል ለአብነት ለግንባታዎች የሚውሉ አንዳንድ የአገር ውስጥ ውብ ንጣፎች (ታይሎች) ከውጪው ጋር ሲነጻጸሩ በእርግጥም ጥራታቸው የወረደ ነው። እነዚህ አንደኛ ውሃ ወደ ውስጥ ያሰርጋሉ፣ ሁለተኛ ቆሻሻ ለማስለቀቅ ሲፋቁ የመፈረካከስ ባህሪ አላቸው፤ ስለዚህ ጥራታቸው ላይ ችግር አለ። ከዚህ የጥራት ችግር የተነሳ ሰው የአገር ውስጡን እየተጠቀመ አይደለም። በመሆኑም መሰል ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ጥራታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

ሌሎቹ ከፍተኛ ችግር የሚስተዋልባቸው የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች ቀለም እና መስተዋት ናቸው። በሁለቱም በኩል ሰፊ ችግር ይስተዋላል። ይህን ችግር ለመፍታት በርካታ ተግባሮች መከናወን አለባቸው።

የህንጻ ማጠናቀቂያዎች እጥረት እና የዋጋ ንረት በግንባታው ዘርፍ ላይ እያስከተለ ካለው ተጽዕኖ ባሻገር ለአጠቃላይ ምርት የዋጋ ንረትም የበኩሉን ሚና ይጫወታል። የዋጋ ንረትን ለመቋቋምና ኢኮኖሚውን ለመደገፍ የአገር ውስጥ የህንጻ ማጠናቀቂያ ምርቶች ከውጭ የሚገባውን እንዲተኩ መደረግ አለበት። ለዚህም አስገዳጅ ህጎችን አውጥቶ ተግባር ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

ሴራሚክን ጨምሮ የሌሎች የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች ጥራትና ዋጋ ላይ የሚስተዋለውን ችግር መቅረፍ የሚቻለው በዘርፉ ብዙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ሲቻል ነው የሚሉት አቶ ዘሪሁን፤ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ሴራሚክ እና ሌሎች የግንባታ ማጠናቀቂያዎች ከውጭ ከሚገባው በቅናሽ እንዲቀርቡ ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ።

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ፤ ድርጅቶች ስፔስፊኬሽን ሲያስቀምጡ የሚስተዋለውን ችግር መቅረፍ ያስፈልጋል። አብዛኞቹ የህንጻ ማጠናቀቂያ ምርት ገዢዎች ግዥ ለመፈጸም የአገር ውስጥ ምርቶችን ስፔስፊኬሽን ውስጥ የማስገባት ችግር አለባቸው። ስፔስፊኬሽን ውስጥ እንዲገቡ እየተደረጉ ያሉት እቃዎች ግን የውጭ ናቸው። ይህም በአገር ውስጥ ያለው ምርት እንዳይበረታታ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። በመሆኑም የአገር ውስጥ ምርቶች ስፔስፊኬሽን ውስጥ እንዲገባ የሚያስገድድ አስገዳጅ ህግ መዘጋጀት አለበት።

የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ጥራትና አገልግሎት አሰጣጥ፣ ምርታማነትን ማሳደግ፣ ከውጭ አገራት የሚገባውን በአገር ውስጥ መተካት፣ ወደ ውጭ መላክ፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣ በገበያ ትስስር የአገር ውስጥ የግንባታ የገበያ ትስስር ውስጥ እንዲካተት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም አንስተዋል።

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ፤ ባለፈው ዓመት የኮንሰልታትንስ ወርክ ማኑዋል/ የአሰራር መመሪያ/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አፅድቋል። በዚህ በስፔስፊኬሽን ውስጥ የአገር ውስጥ ምርቶች መጠቀስ አለባቸው የሚል ተካቶበታል። የአገር ውስጥ ምርቶች ካልተጠቀሱ ስፔስፊኬሽኑ ውድቅ መሆን አለበት። በተደጋጋሚ ስፔስፊኬሽን ውስጥ እነዚህ ነገሮች አስገዳጅ ሆነው መግባት አለባቸው የሚል ቅሬታ ይነሳ ስለነበር ነው ይህ እንዲገባ የተደረገው።

በአገር ውስጥ የማይመረቱ እና ሊገኙ የማይችሉ ምርቶቹ ከሆኑ ብቻ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እውቅና ሲሰጠው ከውጭ በመጣ ምርት መስራት ይቻላል የሚል መመሪያ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። እነዚህ ህጎች ለኮንትራክተር እና ኮንሰልታንት ሰፊ ግንዛቤ ተሰጥቶ ወደ ውጪ የሚሄደውን የውጭ ምንዛሪ ፍሰት መቀነስ ይቻላል፣ የአገር ውስጥ ምርትንም ማበረታታት ይቻላል ተብሎ ነበር።

የአገር ውስጥ ምርት ሲበረታታ ፋብሪካዎቹ ስለሚጠናከሩ የግንባታ ማጠናቀቂያ ችግሮችን ከመቅረፍ ባሻገር የስራ እድልም መፍጠር ይቻላል። አሁንም ለእዚህ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት አለበት። ሁሉም አካል ለተፈጻሚነቱ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

በዚህ ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት፣ ቴክኖሎጂ ለማሸጋገር በጆይንት ቬንቸር መስራት ያስፈልጋል። አብረው የሚሰሩ የውጭ ኩባንያዎች ቴክኖሎጂውን የማምጣት እድል አላቸው፣ አገር ውስጥ ያለው ደግሞ የራሱን ማምረቻ መሰረተ ልማቶችን ማቅረብ ይችላል። ሁለቱ በመተጋገዝ ምርትን ማሳደግ ይችላሉ። ይህን ማድረግ ከተቻለ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ስራ ያቆሙ የማጠናቀቂያ እቃዎች ማምረቻ ፋብሪካዎችን ወደ ማምረት ስራ ማስገባት ይቻላል። በዚህም ጥራት ያለው ምርት ማቅረብ ይቻላል።

አገሪቱ ባላት አቅም የማጠናቀቂያ ምርቶችን ማምረት ብትችል ብዙ ሚሊየን ዶላሮችን ማዳን እንዲሁም ብዙ የቆሙ ፕሮጀክቶችን ማስቀጠልም ይቻላል። በመሆኑም ለዚህ ሰፊ ስራ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

የግንባታ ማጠናቀቂያ ምርቶች አምራች ፋብሪካዎች ግብዓቱን ለማምረት የሚያስፈልጋቸው ዘመናዊ እና ውድ ማሽኖችን ለማሟላት በሚያደርጉት ጥረት መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፤ በዚህ ረገድ በትኩረት ካልተሰራ የግንባታ ዘርፉን አሁን ካለበት ችግር ማውጣት አይቻልም። በመንግስት እና በግለሰቦች የሚገነቡ ፕሮጀክቶችንም ለማጠናቀቅ አዳጋች ይሆናል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሲታገዝም፤ ሲደነቅም የሚገባው የመንግስት ለዘላቂ ሰላም ኃላፊነትን የመወጣት ጉዞ

ሰላም ለአንድ አገርና ሕዝብ ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና እውን መሆን ተኪ የሌለው የመጀመሪያም የመጨረሻም አውድ ነው። ያለ ሰላም ልማት፣ ያለ ሰላም መልካም አስተዳደር፣ ያለ ሰላም ወጥቶ መግባት፣ ያለ ሰላም ወልዶ መሳም፣ ያለ ሰላም ሁሉንም ሰብዓዊም ሆኑ ዴሞክራሲያዊ መብቶች አረጋግጦ መኖር እጅጉን ፈታኝ ነው።

ይህ የሁሉ ነገር መሰረት የሆነው ሰላም ደግሞ በተለያየ መልኩ ሊመጣ ይችላል። ምናልባትም የሰላም ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን ቀድሞ በመፍታት ሰላምን ማምጣት ይቻላል። ችግሮቹ ወደ ግጭት ካመሩ በኋላም ግጭቱ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ በመነጋገር ሰላምን ማምጣት ይቻላል።

አንዳንዴም ግጭቶቹ ከፍ ብለው ወደ ጦርነት ካመሩ በኋላ በጦር ኃይል በሚገኝ የአንድ ወገን የበላይነት ላይ ተመስርቶ ሰላምን ማምጣት የሚቻልባቸው አጋጣሚዎች አሉ። በተለይ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገራት ይሄኛው መንገድ ዘመናትን የኖሩበት ሰላም የማረጋገጫ መሳሪያ ተደርጎ ስለመኖሩ ከየሥርዓቶቹ የሚጠቀሱ በርካታ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል።

ይሁን እንጂ በአንድም ሆነ በሌላ የሚገኝን ሰላም እንደ ጊዜያዊ የሰላም አማራጭ ከመውሰድ በዘለለ፤ የተገኘውን ሰላም ዘላቂ በማድረግ ሂደት ላይ መንግስታት ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው የዘርፉ ምሑራን ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ በሰሜኑ ክፍል ተከስቶ የነበረው እና ላለፉት ሁለት ዓመታት የዘለቀውን ጦርነት ለዚህ አንድ ማሳያ አድርጎ ማየት ይቻላል። ግጭቱ ከመቀስቀሱ በመንግስት በኩል ተደጋጋሚ የሰላም ተደርገው ነበር፤ ሳይሳካ በመቅረቱ ወደ ጦርነት ተገባ።

ጦርነት ከተነሳም በኋላ መንግስት ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት ጭምር የተናጠል ተኩስ አቁም አድርጎ የሰላም ውይይት እንዲደረግ ያቀረበው ተደጋጋሚ ጥሪ ሳይሳካ በመቅረቱ በተራዘመው ጦርነት በርካታ ዜጎች ሕይወታቸውን፣ አካላቸውን፣ ሃብት ንብረታቸውን አጡ። አገርም ብዙ ተጎዳች።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ኃይል ወደ ሰላማዊ ድርድር መግፊያ አማራጭ ተደርጎ በመወሰዱ በመንግስት በኩል የተገኘው የኃይል የበላይነት የሰላም መንገዱ ተቀባይነት እንዲኖረው ብቻ ሳይሆን፤ ደቡብ አፍሪካ ላይ የተደረሰው የሰላም ስምምነት እውን እንዲሆን አስችሏል። ይሄም ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ወዳጆች ጭምር እፎይታን የፈጠረ ሆነ።

ከስምምነቱ ማግስትም በስምምነቱ ላይ የተቀመጡ ዘላቂ ሰላምን የማምጫ ነጥቦች በሁለቱም (በመንግስትም፣ በሕወሓትም) በኩል ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ ስምምነቶችም ተፈረሙ። ይሄን ተከትሎ መንግስት ኃላፊነት እንዳለበት አካል ቅድሚያ ወስዶ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፤ በሕወሓት በኩልም በውስጡም ሆነ ከውጪ ባሉ አካላት ጎታች አካሄዶች ቢኖሩበትም መልካም የሚባሉ ጅምሮች ታይተዋል።

መንግስት ቀደም ሲል ከጦርነት ይልቅ ሰላምን አስቀድሞ የሄደበት ርቀት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አሁን ላይ የተገኘው ሰላም ዘላቂ እንዲሆን በማድረግ በኩል የሚጠበቅበትን ሁሉ እያደረገ ይገኛል። ለምሳሌ፣ ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ወደ ትግራይ ክልል መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ ድጋፎች (ምግብ፣ መድሃኒት እና ሌሎች ድጋፎች) በአየር እንዲሁም በየብስ በሶስት ኮሪደሮች እንዲገቡ በማድረግ ለህዝቡ ማድረስ ተችሏል።

በተመሳሳይ በጦርነቱ ወቅት ጉዳት የደረሰባቸውን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች መልሶ በመገንባት ወደ አገልግሎት እንዲገቡ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። በዚህም በበርካታ የክልሉ አከባቢዎች የቴሌ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ የውሃ እና ሌሎችም መሰረተ ልማቶችን ጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል።

ህብረተሰቡም የሰላሙም ሆነ የልማቱ ተጠቃሚ፣ ተሳታፊም የሚሆንበትን ስርዓት ዘርግቶ ህዝቡ ይሄንኑ እንዲያጣጥም እድል ፈጥሮለታል። ያገኛቸው የሰላምም የልማትም እድሎች ዳግም ከእጁ እንዳይወጡም ሕዝቡ በባለቤትነት እንዲይዛቸውም እየተደረገ ነው።

መንግስት በዚህ መልኩ የተገኘውን ጊዜያዊ ሰላም ዘላቂ ለማድረግ የሰላም ስምምነቱ ያስቀመጣቸውን ነጥቦች በትኩረት እየፈጸመ ይገኛል። ይሄን የሚያደርገው ግን በስምምነቱ ላይ ስለተቀመጡ ብቻ ሳይሆን እንደ መንግስት ዜጎቹ የሰላምም የልማትም፣ የሰብዓዊ ድጋፍም እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት ስላለበት ነው።

ይሄ የመንግስት ዘላቂ ሰላምን የመሻት ቁርጠኛ አካሄድ የሚደነቅ ብቻ ሳይሆን፤ ከውስጥ በመላው ሕዝብ፣ በውጪ ደግሞ በአጋርና በደጋፊ አካላት ሁሉ እውቅና እና ድጋፍ ሊደረግለት የሚገባ ነው።


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## አገር በትናንት መልኳ ብቻ አትገለፅም፤ ነገዋን በሚሰሩ ጥበበኞችና ብርቱዎች ትጋት እንጂ፤

ዶክተር ጀኔኑስ

ኢትዮጵያ መልኳ ምንድን ነው? ብየ ልጠይቃችሁ ወደድኩኝ። በእርግጥ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ብዙም ውሃ ላይቋጥር ይችላል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቀለል ያሉ ነገሮችን መልሶ መላልሶ መጠየቅና ማጠያየቅ ክፋት የለውም። ምናልባትም ቀላል በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ የገዘፉ፤ የተስተካከሉ በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ የተዛነፉ፤ የጨዋ ልኬት በምንላቸው ውስጥ ቅጥ ያጣ ቅሌት፣ በማወቅ ውስጥም አለማወቅን ያሳያሉና። እኔም ኢትዮጵያ መልኳ ምንድን ነው? ብዬ ስጠይቃችሁ እነዚህን ታሳቢ ማድረጌ ጠቃሚ ይመስለኛል።

የአገር መልኳ ሰሪዎቿን ይመስላል። ወዳጄ ልቤ! ኢትዮጵያ መልክ አላት፤ ለዚያውም ፍንትው ብሎ የሚታይ። አንተ ደግሞ መልክህ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገለፃል። ኢትዮጵያ ስትደስት መልክህ ፈገግታ ነው፤ እርሷ ሲከፋት የአንተ መልክና ውበት የወረዛ ነው፤ የኢትዮጵያ መገለጫ መልክና ውበቷ እኛ ልጆቿ ነን። አንተ ማለት ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ ማለት አንተ ነህ። ይህን ነገር መልሰህ መላልሰህ ስትጠይቅ ነገሩ ይገባህና፤ እውነት ኢትዮጵያ መልኳ ምን ይሆን ብለህ ራስህን መጠየቅ አይቀሬ ነው።

ግሪካዊ ፈላስፋ ሶቅራጥስ «እራስዎን ይወቁ እና መላውን ዓለም ያውቃሉ» ሲል ሁሉን ነገር ለማወቅ መጀመሪያ ሰው ራሱን፤ አገሩን እና ወገኑን በሚገባ ማወቅ እንዳለበት በአንክሮ ይናገራል። ሰው አካባቢውን ለማወቅ መጀመሪያ ግራ ቀኝ ያሉትን ጎረቤቶቹን ማወቅ ይጠበቅታል። እኔም ስለነገሮች በዝርዝር ከመግባቴ በፊት ሌሎች እንዴት ይገልጹናል የሚለውን ለማወቅ እና ኢትዮጵያ የምትባለው አገር እንዴት እንደምትገለጽ በጥቂቱ ለማሳወቅ መሞኮር ተገቢ ይመስለኛል።

ዊኪፒዲያ ገና በመግቢያው ገጽ ኢትዮጵያ ማለት ይላል፤ «በአፍሪካ ቀንድ የምትገኝ የረጅም ዘመን ታሪክ ያላት አገር ናት። በአፍሪካ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ብቸኛም አገር ነች። አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ዕድሜያቸው ከአንድ ምዕተ-ዓመት የሚያንስ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ግን ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በንጉሠ-ነገሥታት እና ንግሥተ-ነግሥታት የተመራች አገርም ናት። የሠለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት የአመጣጡን ዘር እስከ አስረኛው ዓመተ-ዓለም ድረስ ይቆጥራል።

"ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የኖረባት ቦታ እንደሆነች ብዙ የሳይንሳዊ መረጃ ተግኝቷል። በበርሊን ጉባኤ በኩል የአውሮፓ ሃያላት አገሮች አፍሪካን ሲከፋፍሏት፣ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃለች። የሊግ ኦፍ ኔሽንስ (League of Nations) አባል ከነበሩት ሦስት የአፍሪካ አገሮች አንዷ ነበረች። ከኢጣልያን ወረራ ጊዜ በኋላም የተባበሩት መንግሥታት መሥራቾች አንዷ አገር ናት።

" ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ የአፍሪካ አገራት ነፃነታቸውን ሲያገኙ፣ ሰንደቅ-ዓላማቸውን በኢትዮጵያ ቀለሞች ማለትም በአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ላይ ነው የመሠረቱት። አዲስ አበባ ደግሞ ለየተለያዩ በአፍሪካ ላይ ያተኮሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ሆነች» ሲል ከዕድሜ ጠገቦቹ አገራት ቀዳሚ፤ ከታሪክ ድርሳናትም በዋና ምንጭነት የምትጠቀስ፤ በጀግንነት ምዕራፍ ደግሞ ነጮችን አንበርክካ የጥቁር ህዝቦችን ገድል ከፍ ያደረገች እጹብ አገር ስለመሆኗ ይመሰክራል።

የኢትዮጵያ ማለት መልክ ብዙ፤ የውሃ ልኳ የተመጠነ ግን ደግሞ ከፍ ያለ ማንነቷ ያልተበረዘች ማለት ነው። ታዲያ የዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ መልኳና ክብሯ ልጆቿ ናቸው። ኢትዮጵያ የምትገለጠው አሁን ባሉ ዜጎቿ እንጂ ባለፈ ታሪክ ላይ ብቻ ቆማ የምትቆዝም አገር መሆን የለባትም። የትናንት አባቶች በደም በአጥንታቸው ኢትዮጵያን መልከ ሸጋ አድርገው አቆይተዋል።

አሁን ያለው ትውልድ ደግሞ ቡሩሹን ከቀለሙ ነክሮ የሚያኖራት ኢትዮጵያ ጥንት ከነበረችው በብዙ እጥፍ ያማረች፣ ያሸበረቀች፣ በባህልና ትውፊቷ የተከበረች፤ ለልመና ሳይሆን ክብሯን ለማስጠበቅ የምታትር መሆን አለባት። የኢትዮጵያ መልክ መገለጫው ግጭት፣ አለመግባባት፣ ጦርነት፣ ርሃብና ድህነት ሆኖ መቀጠል የለበትም።

ይህ ትውልድ ዕዳ አለበት። የኢትዮጵያ ቀለም መቀየር፤ የኢትዮጵያን አንድነት ማጉላት፤ የኢትዮጵያ የጥቁር ህዝቦች መኩሪያና መታፈሪያ ሆና የኖረችና በዚሁ የምትቀጥል መሆኗ ማረጋገጥ የትውልዶች አደራ ጭምር የተጣለበት ትውልድ ነው።

ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፤ ኢትዮጵያዊ መልክ፤ ኢትዮጵያዊ ማንነት፤ ኢትዮጵያዊ ዘረመል፣ የኢትዮጵያዊነት እሳቤ በሁሉም አቅጣጫ ነው መታየት ያለበት። አመራሩ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ተላብሶ የህዝቡን መብት አክብሮ መሥራት አለመስራቱን ራሱን መፈተሽ አለበት።

ይህ ትውልድ ውብ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር፤ ለመጪው ትውልድ ማኖር ይጠበቅበታል። አገር በነበር ብቻ አትጠራም፤ ነገን ታሳቢ በማድረግ ጭምር እንጂ። አገር ባለፉት መሪዎችና ትውልዶች ታሪክ ብቻ ስትዘከር አትኖርም፤ አሁንም መራር ትግል በማድረግ ለመጪው ትውልድ ደማቅ አሻራ በማኖር እንጂ። አገር በትናንት መልኳ ብቻ አትገለፅም፤ ነገዋን በሚሰሩ ጥበበኞችና ብርቱዎች ትጋት እንጂ።

በአንድ ወቅት አዲስ አድማስ ጋዜጣ ዘለግ ባለው ፅሁፉ «ኢትዮጵያ አብዛኛው ህዝብ በድህነት እየማቀቀ ጥቂቶች የሚበለፅጉበት አገር ሆናለች። የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እየተጣሱ» ሲል በዘመነ ኢህአዴግ የነበረውን ግፍ ለመተንተን የጠቆመበት ቃል አንዳች ነገር ያስታውሰኛል።

ብዙ ጊዜ በተለያዩ ደረጃዎች ወደ መንበረ ስልጣን የሚመጡ አመራሮች የኢትዮጵያን መልክ ካለማወቃቸው የተነሳ፤ የጠላትን ጭቆና አሽቀንጥሮ የጣለን ህዝብ በመልካም አስተዳደር እጦት ያሳዝኑታል። ካለው የሚያካፍልን ማህበረሰብ አራቁተውት ተመፅዋች ሊያደርጉት ይዳዳቸዋል።

ኢትዮጵያ ከግለሰቦችና ከአንዳንድ ቡድኖች ግልፈተኝነት የተሞላበት እሳቤ በጣም የላቀች አገር መሆኗን ባለመረዳታችን ከወርቅ ማማ ላይ ጎትተን አረንቋ ውስጥ ልንከታት የሚዳዳን ብዙዎች ነን። አለቀላት፤ አከተመላት ስትባል እንደ ዓደይ አበባ ፈክታ፤ እንደ ጥዋት ጀንበር ደምቃ ብቅ የምትል ልዩ ሙሽራ ናት።

ኢትዮጵያ አሸናፊነት፣ ኢትዮጵያዊነት መመካከርና ታጋሽነት፣ ኢትዮጵያዊነት ሠላምና አንድነት፣ ኢትዮጵያዊነት ችግር ወደ ድል መቀየር ነው። ኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር ችላ ለሁሉም የምትሆን አገር ናት። እኛ የአገራችን መልክ የምንሠራ መሆናችን ከአሁኑ ተገንዝበን በህይወት ዘመናችን ሁሉ የሚጠበቅብን ማድረግ ይገባል።

የአገር መልኳ መገለጫዋ እኛ ዜጎቿ ነን። በመሆኑም አገራችን ተልቃ የምታተልቀን፤ ገዝፋ የምታገዝፈንና በዓለም ዓደባባይ በልጽጋ የምታኮራን ትሆን ዘንድም የሁላችንም ጥረት፣ ፅናትና ትጋት ይጠይቃል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^ስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# እጅ ያጠረው ዕድሜ

መልካምሥራ አፈወርቅ

ያለፉት ሰማንያ ዓመታት ለእማማ ሁሉአገርሽ ተሰማ በጎና ምቹ አልነበሩም። በእነዚህ ጊዜያት አብዛኛው የሕይወት መንገድ ጎርባጣና ሻካራማ ነበር። ወይዘሮዋ ያለፈውን በትዝታ መልሰው ሲያወጉት ከልብ ይከፋቸዋል፣ ያዝናሉ፣ ይተክዛሉ። እንደዋዛ ሰማንያ ዓመታት ነጉደዋል። እንደቀልድ ስምንት አስርት አመታት አልፈዋል። የእሳቸው የሳቅ ደስታ ዘመን ግን በጣም ጥቂቱ ነበር።

ዛሬ ሁሉአገርሽ ድፍን ሰማንያ ዓመት ሞልቷቸዋል። እሳቸው ይህን ይበሉ እንጂ ዕድሜያቸው ከአካላቸው ሲናበብ ስልሳዎቹን የተሻገሩ አይመስልም። ገጽታቸው የነቃ፣ አካላቸው የጠበቀ ነው። ቁመናቸው የዕድሜ ጥላ ያንዣበበት አይመስልም። ዛሬም ለመኖር ይታገላሉ፣ ለሕይወት ይሮጣሉ።

### ስምንት አስርት ዓመታት ወደኋላ

የልጅ ልጃቸውን አብዝተው የሚወዱት መነኩሴዋ አያት ህጻኗን ከእሳቸው መለየት አይሹም። በየሄዱበት አዝለዋት ይዞራሉ። እሳቸው ልጆቻቸውን በልፋት ድካም አሳድገዋል። ዛሬ ሁሉም ራሱን ችሎ የራሱን ሕይወት ይመራል፣ እማሆይ ጉልበታቸው እየደከመ ትከሻቸው እየተፈተነ ነው። እንዲያም ሆኖ ለልጅ ልጃቸው የሚሆን አቅም አላጡም። ህጻኗን በየሄዱበት ከትከሻቸው አዝለዋት ይጓዛሉ።

የእሳቸውን ልፋትና ድካም ከልጅ ልጃቸው ፍቅር አጣምረው የሚያዩ ዘመዶች ታዲያ ሁሌም ይገረማሉ። አንዳንዶች ደግሞ ለእሷ የሚመጥን ስም እንዲያወጡላት ይጠይቃሉ። አያት ሀሳባቸውን አልናቁም። ለልጅ ልጃቸው ስም መረጡ፣ አማረጡ። ዘወትር ከትከሻቸው አዝለው በየቦታው የሚያዞሯትን ህጻን ‹‹ሁሉአገርሽ›› ሲሉ ጠሯት።

ሁሉአገርሽ ከአያታቸው ትከሻ ታዝለው ብዙ ቦታን አይተዋል። ደጀሰላም ገዳሙን፣ አገር መንደሩን፣ ቀዬ ገበያውን ጎብኝተዋል። ይህ አጋጣሚ ለሁኔታው ፈቅደ፣ልና ሁሉ አገራቸው ቢባል አያስደንቅም። ስማቸው በሌሎች ተወደ፣ል። ትርጓሜው በሁሉም ጸድቋል።

በአያታቸው እጅ ያደጉት ሁሉአገርሽ ከትከሻቸው ወርደው መራመድ እንደያዙ የሕይወትን ግዴታ ‹ ሀ..› ብለው ጀመሩት። ልጅነታቸው እንደ እኩዮቻቸው ነበር። እናት አባታቸው ቤት ካፈራው፣ ሁሉ አይነፍጓቸውም። ከቀዬው እየቦረቁ፣ ከባልንጀሮቻቸው እየተጫወቱ አድገዋል።

ከአካባቢው ጥቂት የሚባሉት በያዙት ዕውቀት ስማቸው ይጠራል። እሳቸው ግን ትምህርትን የማግኘት ዕድል አልነበራቸውም። እንደሴት ልጅ ወግ ከእናታቸው ጉያ ሳይርቁ ቤተሰቡን በጉልበት አግዘዋል። የታዘዙትን ከውነዋል።

### ኮረዳነት

አሁን ሁሉአገርሽ ከልጅነት ዕድሜ አይደሉም። ህጻንነታቸው አልፎ፣ ሩጫ ዝላዩን ትተዋል። እንደበፊቱ ቀና ብለው አይሄዱም። ሲያናግሯቸው ያፍራሉ። ለእርምጃ ጉዟቸው ይጠነቀቃሉ። በእሳቸው ዕድሜ ያሉ እኩዮቻቸው ዕጣ ፈንታ ባል ማግባት ትዳር መያዝ ነው። ሁሉአገርሽም ቢሆኑ ለዓይን የሚሰቡ ልጃገረድ ሆነዋል። አስራ አምስተኛ ዓመታቸውን ከያዙ ጀምሮ ‹‹ልጃችሁን አጋቡን፣ ዳሩልን ›› የሚሉ በዝተዋል።

እናት አባት ለጋብቻ የሚመጡ ጥያቄዎቹን አልገፉም። ልጃቸው ባል አግብታ፣ ትዳር ይዛ ወግ ማዕረግ ብታይ ይወዳሉ። ቆይቶ ጋብቻውን ከጠየቁት መሀል ለአንደኛው ልባቸው አጋደለ። ቀልባቸው ለፈቀደው ሰው ሁሉአገርሽን ሊድሩ ተስማሙ።

ሁሉአገርሽ በአስራ አምስተኛ ዓመታቸው በወላጆቻቸው ይሁንታ በሰርግ ተዳሩ። የልጅነት፣ ዕቃ ዕቃ ጨዋታ ተረሳ። ዝላይ ፈንጠዝያው ቀረ። ሁሉም አለፈና ወይዘሮ ተባሉ። ‹‹ሙሽሪት ልመጂ›› የተባለላቸው ወጣት የእናት አባታቸውን ቤት ትተው



ወ/ሮ ሁሉአገርሽ ተሰማ

ባላቸውን ተከተሉ። አዲሱ ጎጆ በአዲስ ሙሽሮች ድምጽ ሞቀ፣ ደመቀ። አዲስ ሕይወት ቀጠለ።

ትዳር እንደጀመሩ የመንግስት ሰራተኛው ባለቤታቸው ለስራ ከአካባቢው ሊርቁ ሆነ። ትዳር ነውና ሁሉአገርሽ ከእሳቸው መነጠል አልቻሉም። ባለቤታቸውን ተከትለው ወደ አሰብ አቀኑ።

በወለጋ መስመር ጅባትና ሜጫ ‹‹ጨሊያ›› የተወለዱት ወይዘሮ ዕድገታቸው ከአካባቢው የራቀ አይደለም። ከስፍራው ወጥተው ባያውቁም ባላቸውን ለመከተል ዓይን አላሹም። ‹‹ጨርቄን ማቄን›› ሳይሉ አብረዋቸው ተጓዙ።

አገራቸው ላይ እናት አባታቸውን ትተዋል። ‹‹የራሴ›› የሚሉት ሀብት ንብረትም አላቸው። ይህ ሁሉ ግን ከባላቸው አልነጠላቸውም። አሰብ ገብተው ትዳራቸውን ቀጠሉ። አሰብ ላይ ሁሉም ሮጦ ተግባብቶ ያድራል። ማነህ ? ከየት ነህ ? ምንድነህ ? ይሉት ጉዳይ የለም። ሁሉም በግሉ ሰርቶ በጋራ ይበላል። ልዩነት አይታወቅም፡ እንደቤተሰብ ቋንቋው አንድ ነው። በፍቅር ተዋዶ፣ ተከባብሮ ይኖራል።

ባለቤታቸው በአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ ድርጅት ይሰራሉ። እሳቸውን ጨምሮ በርካቶች የድርጅቱ ነዳጅ ማጣሪያ ላይ ሕይወታቸው ተወስኗል። ሁሉአገርሽ ለቤት ለኑሯቸው የባላቸውን እጅ አልጠበቁም። ሌሊቱን እንጀራ እየጋገሩ ሲነጋ ለሽያጭ ያስረክባሉ።

ጊዜው በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን ነው። የዛኔ እንዳሁኑ ሕዝብ አልበዛም። ኑሮ አልተወደደም። እንዲያም ሆኖ ራስን ለማሸነፍ ሌት ተቀን መልፋት ግድ ነው። ሁሉአገርሽ ለእሳቸው፣ ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው መኖር እየታገሉ ነው። ሙቀት እያጋያቸው፣ በጉልበታቸው ድካም በላባቸው ወዝ ያድራሉ።

ጥቂት አይሏቸው ዓመታት በአሰብ ሕይወትና ኑሮ ተገፉ። በእነዚህ ግዜያት ልጆች ተወልደው አደጉ። ጊዜዎች ነጎዱ፣ ዕድሜ ጨመረ። ከጊዜያት በኋላ የንጉሱ ወንበር በስልጣን ነቅናቂዎች ተገርስሶ ወደቀ። በመላው አገሪቱ ለውጥ መጣ፣ ኑሮ ተለወጠ።

አብዮትና ፖለቲካ ይሉት ጦስ የብዙዎችን ቤት አንኳኳ። የነበረው ባልነበረው ጥግ ሲጓዝ እንደነ ሁሉአገርሽ ያሉ ሰርቶ አዳሪዎች ኑሯቸው ተንገጫገጨ። ሁኔታዎች ተረጋግተው ቦታቸውን እስኪይዙ ጥቂት ቸገራቸው። ቆይቶ ግን ሕይወት እንደቀድሞው ቀጠለ።

ዓመታትን በስፍራው የገፉት ቤተሰቦች የአቅማቸውን እየሰሩ እስከ 1983 ዓ.ም ዘለቁ። ከዚህ ዓመት በኋላ ግን ሁሉም ነገር ተቀየረ። አዲስ የመንግስት ለውጥ መጣ። ስልጣን በሌሎች ሀይሎች በተተካ ጊዜ ሰራዊቱ ተበተነ፣ ይሄኔ በየስፍራው ያለ ነዋሪ ስለደህንነቱ ዋስትና አጣ። ስደት፣ መፈናቀል፣ ስራአጥነት በረከተ።

የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያና በውስጡ ያሉ በርካታ ሰራተኞች ከዚህ ችግር አልዳኑም። በሌሎች የሆነው ሁሉ በእነሱም ደረሰ። አብዛኞቹ የነበሩበትን ለቀው ወደ መሀል አገር ተሰደዱ። ጥቂት የማይባሉት ቤት ንብረታቸውን ትተው ተፈናቀሉ። ህጻናት ሴቶችና አረጋውያን፣ ጉዳትና እንግልት አገኛቸው።

### ጥቁር እንግዳ

ወይዘሮ ሁሉአገርሽና ቤተሰቦቻቸው የአሰብን ምድር ለቀው ወጥተዋል። አሁን በአገሪቱ አዲስ ለውጥ ሆኗል። አብዛኞች በያዙት ለመቀጠል፣ በትናንቱ ለመኖር ተቸግረዋል። ሁሉም ሕይወቱን ለማትረፍ ይበጃል ያለውን እያደረገ ነው። አቅም ያለው አገሩን ትቶ ወጥቷል። ስደት ብርቅ አልሆነም። ችግር እግር በእግር ተከትሎ የብዙዎችን ማንነት መፈተን ይዟል።

ሁሉአገርሽ አዲስ አበባ ደርሰዋል። ብቻቸውን አይደሉም። ከእሳቸው ጋር ልጆችና ባለቤታቸው አሉ። አሁን ‹‹ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ›› ይሉት ስሜት በውስጣቸው ነግሷል። በእጃቸው እዚህ ግባ የሚባል ጥሪት የለም። ድንገቴው ለውጥ ብዙ ነገራቸውን ቀይሯል።

ከእጅ ባጡ፣ በነጡ ጊዜ ከዘመድ መጠጋት፣ እንግዳ መሆን ያሳቅቃል። ሌላውን ለመጠየቅ፣ ለመጠያየቁ ያወጡት፣ ይመነዝሩት ሲኖር፣ ደስ ይላል። ባዶ እጅ ደርሶ ያስጨንቃል፣ ያሳፍራል። ሁሉአገርሽና ቤተሰቦቻቸው ምርጫ አላገኙም። ተፈናቅለው አዲስ አበባ ከመጡ ጀምሮ ማረፊያቸው ከዘመድ ቤት ሆኗል።

ያረፉት ከባለቤታቸው እህቶች ዘንድ ነው። እነሱ የራሳችን ይሉት ቤትና መጠጊያ አላገኙም። ቀን አልፎ ችግር እስኪርቅ እንዲህ ሊሆኑ ግድ ብሏል። ሁሉአገርሽ ግን ተጨንቀዋል። ካደጉበት አገር የራሳቸው ቤትና ንብረት ነበራቸው። እሱን ትተውት ከራቁ ዓመታት አልፈዋል። ይህን ሲያስቡ ወላጆቻቸው ትውስ ይሏቸዋል። እስከዛሬ ተመላልሰው ጠይቀዋል። አሁን ግን ሁለቱም በሕይወት የሉም። ውስጣቸው ባዶነት እየተሰማው ነው። ትናንት ለሌሎች ይተርፍ የነበረው እጃቸው ዛሬ ለእርዳታ ተዘርግቷል። አሁን የሚያዙበት ዕልፍኝ እንዳሻቸው የሚቆርሱበት ማጀት የላቸውም። እንዲህ መሆኑ አስከፍቷቸዋል።

ጥቂት ጊዜያት ቆይቶ ወይዘሮዋ ራሳቸውን ለመቻል መሮጥ ያዙ። በወቅቱ ለሌሎች መሰሎቻቸው የሆነውን እርዳታ አላገኙም። በተፈናቃይ ስም የጠየቁት የቀበሌ ቤትም አልተሳካም። መቀመጥ አልፈለጉም። ጉልት ለመሸጥ ጥቂት ነገሮች ይዘው ከመንገድ ተቀመጡ። በውሏቸው ያገኙትን ቋጥረው ቤት መመለስ ልምዳቸው ሆነ።

ውሎ አድሮ መላው ቤተሰብ የአዲስ አበባን ሕይወት ለመደው። ባለቤታቸው እያረጁ ነው። ወይዘሮዋ ባላቸው የጡረታ አበል እንዳላቸው ሰምተዋል። ሽማግሌው ግን ለአንድም ቀን አሳይተው፣ ሰጥተዋቸው አያውቁም። ልጆቻቸው ቢደርሱም ሊያግዙ ሊደግፏቸው አይፈቅዱም። ዘወትር ለየራሳቸው ኑሮ ይሮጣሉ።

ከዓመታት በፊት በሴት ልጃቸው እጅ የነበረን የንግድ ሱቅ ተከራይተው ነበር። በእሱ ጥቂት እየሰሩም ቀን ገፍተዋል። ቆይቶ ግን ‹‹ቦታው ይፈለጋል›› በሚል ሰበብ መተዳደሪያቸው ተነጠቀ። ይህ ከሆነ ወዲህ ቤት ከመዋል ያለፈ መላ አላገኙም።

ሁሉአገርሽና አዛውንቱ ባለቤታቸው ዛሬም በአንድነት ይኖራሉ። አባወራው በህመም ምክንያት ከአልጋ ከዋሉ ቆይቷል። መነሳት፣ መንቀሳቀስ ተስኗቸዋል። እሳቸውን የማገዝ የማኖር ጫናው ከአዛውንቷ ሁሉአገርሽ እጅ አላለፈም። ህመምተኛውን በደከመ አቅማቸው እያነሱ ያገላብጧቸዋል፣ ያገኙትን እያቀመሱ መድኃኒታቸውን እየሰጡ ያስተኟቸዋል።

ዛሬ አብሮ አደጎቹ ባልና ሚስት ከአባወራው እናት አባት በተላለፈ የቀበሌ ቤት ይኖራሉ። ከአጠገባቸው የሰውዬው የቅርብ ዘመዶችና እህቶቻቸው አሉ። የእነሱ መኖር ግን ለሁሉአገርሽ ኑሮ የጠቀመ አይመሰልም። ሰላማቸውን ካጡ ቆይቷል።

የእሳቸው ውስጠት በገለልተኝነት ስሜት ተይዟል። ሁሌም ብቸኛ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። ሁሉም የሚናገሩትን የሚያምኗቸው፣ የሚሉትን የሚቀበሏቸው አልመስል ካላቸው ሰንብቷል። አንዳንዴ ባለቤታቸው ጭምር ከዘመዶቻቸው አብረው ይናገሯቸዋል። ያስከፏቸዋል። ይህ እውነት ‹‹ብቸኛ ነኝ›› ለሚሉት ሴት ልዩ ትርጉም አለው።

በዕድሜ ብዛት መፍረስ የጀመረው ቤታቸው ከረምቱን ዝናብና ጎርፍ ያስገባል። እንዲህ መሆኑ ወይዘሮዋን ጤና አሳጥቷል። በድካም እየተንገላቱ የሚያቀኑትን ጎጆ የሚጎበኘው የለም። ወዲህ ችግሩ፣ እልፍ ሲልም እጅ ማጠሩ ሲያሳስባቸው ይውላል።

### የሰባቶች እናት

ወይዘሮዋ ዕድሜያቸው እየገፋ አቅማቸው እየደከመ ነው። ማንም ግን ‹‹እናቴ፣ እረፊ፣ እንጡርሽ፣ እንደግፍሽ›› አይላቸውም። ባለቤታቸው ከሌላ እናት የወለዷቸው ልጆች አሉ። አንዳንዴ አባታቸውን ያስባሉ፣ ይጠይቃሉ። ሁሉአገርሽ ግን ከሰባቱ ልጆቻቸው አንዳች የሚያገኙት የለም።

ይህን ባሰቡ ጊዜ ከልብ ይከፋሉ። ዕንባቸው በአንገታቸው ይወርዳል። በዕድሜያቸው ማምሻ አብረዋቸው የኖሩ አጋራቸውን መተው፣ መራቅ አይሹም። ሁሌም ጉዳት ህመማቸው ይሰማቸዋል። መቼም ቢሆን ችግራቸው የእሳቸውም ችግር ሆኖ ይዘልቃል።

ዛሬ ለጎደለው ኑሯቸው ከጎናቸው የሚቆም ልጅ የለም። ሰባት ልጆችን ወልደው፣ አሳድገዋል። አንዳቸውም ግን ‹‹እናታችን የት ነሽ ?› ብለዋቸው አያውቁም። እሱንም ቢሆን ‹‹ተመስገን›› ብለው ትተውታል። አንዳንዴ ግን ከባለቤታቸው ዘመዶች የሚደርስባቸው በደል ከአቅም በላይ ሲሆን ውስጣቸው ይነካል። እነሱ ቤት ለዋሉት ሽማግሌ ባይሆኑም ለእሳቸው ሲሆን ይበረታሉ። እንዲህ መሆኑ ጠዋት ማታ እጅ ለሚያጥራቸው፣ ጓዳቸው በችግር ለሚፈተነው ሴት ኑሮን አክብዷል።

በግቢው ያሉ ነዋሪዎችም ውስጣቸውን አላዩላቸውም። ሁሌም እንደሚሉት በእነሱም ዘንድ ፊት ተነስተዋል። እንዲያም ሆኖ ቂም ለመያዝ፣ ክፋት ለማሰብ ተዘጋጅተው አያውቁም። ለማይረዷቸው ልጆችና ዘወትር ለሚያስቀይሟቸው ሁሉ ውስጣቸው ይቅር ባይነትን ለምዷል።

ዛሬ ሁሉአገርሽ በማምሻ ዕድሜያቸው ላጠረ እጃቸው የፈጠነ ዕድል አላገኙም። እስከዛሬ ጾም ውሎ ላለማደር የአቅማቸውን ሞክረዋል፤ ያገኙትን ሰርተዋል። ዛሬ ግን እንደትናትናው አይደሉም። ተስፋ መቁረጥ ከችግር ተዳምሮ ሲያስከፋ፣ አንገት ሲያስደፋቸው ይውላል።

### ችግርን በምስጋና

በቅርቡ ውስጣቸውን የተረዱ አንዳንድ የወረዳ አመራሮች ከግቢው ደርሰው ቤታቸውን አንኳኩ። በአካባቢው ከሚገኝ የምገባ ማዕከል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በጠየቋቸው ጊዜ አላንገራገሩም። ጠያቂዎቹ የርሀባቸው ማስታገሻ፣ የችግራቸው መላ መሆናቸውን አመኑ። ውለው አላደሩም። በየቀኑ አንድ እንጀራ በወጥ እየተቀበሉ ለራሳቸውና ለህመምተኛው አባወራ ሆድ ደረሱ። በሆነው፣ በተደረገው ሁሉ ደስ አላቸው። በዚህ ዕድሜ ተቸግረው እጅ ቢያጥራቸውም አብልቶ ላሳደራቸው ፈጣሪ የተለመደውን ቃል አይነፍጉም። ዘወትር ‹‹ተመስገን›› ይላሉ። ‹‹ተመስገን››

# ስፖርት





## ኤምባሲው ለሴት እግር ኳስ አሰልጣኞች የሚሰጠው ስልጠና ተጠናክሮ ይቀጥላል

ብርሃን ፈይሳ

የእንግሊዝ ኤምባሲ በኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በጋራ በመሆን ለታዳጊ ሴቶች እግር ኳስ አሰልጣኞች የክህሎት ማሻሻያ ስልጠና ሰጠ። መሰል ስልጠናዎችን በቀጣይ ለማጠናከር መታሰቡም ተገልጿል።

ይህ የሴቶች እግር ኳስን ማሳደግ ዓላማው ያደረገ የአሰልጣኞች ስልጠና ለሶስት ቀናት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፣ የታዳጊ ሴቶች የእግር ኳስ አሰልጣኞች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ክህሎት እንዳገኙበት ተጠቁሟል። ስልጠናው ለ25 ሴት አሰልጣኞች እንዲሁም ሴቶችን በማሰልጠን ላይ የሚገኙ ወንድ አሰልጣኞች እንደተሰጠም ታውቋል። በስልጠናው ተካፋይ የሆኑትም ከአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም ከአጎራባች ከተሞች የተውጣጡ አሰልጣኞች ሲሆኑ፤ በተግባር ታዳጊ እግር ኳስ ተጫዋቾች ላይ እየሰሩ የሚገኙ መሆናቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠቁሟል።

የእንግሊዝ ኤምባሲ በኢትዮጵያ «ግሬት ፉትቦል» በመባል ከሚታወቀው ፕሮጀክት እና ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ያካሄደው ይህ ስልጠና፤ ሴት ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች እግር ኳስ እንዲጫወቱና የሴት ቡድን አሰልጣኞችንም በክህሎት በማብቃት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው። ለሶስት ቀናት የተካሄደውን ስልጠናም በአውን ሳውዝጌት እና የእግር ኳስ ለሰው ልጆች መስራች ቤሊ ቲዮንግኮ አማካኝነት ተሰጥቷል። የሁለት ቀናት ስልጠናው በክፍል ውስጥ ከተሰጠ በኋላም የመጨረሻውና ሶስተኛው ዕለት የ ስልጠና መርሃ ግብር በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በተግባር ተደግፎ ተጠናቋል።



ለሶስት ቀናት ሲሰጥ በቆየ ስልጠና የታዳጊ ሴቶች የእግር ኳስ አሰልጣኞች የሙያ ማሻሻያ ክህሎት እንዳገኙበት ተጠቁሟል፣

ስልጠናውን ተከትሎ በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይም ኤምባሲው መሰል ስልጠናዎችን በቀጣይም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተጠቁሟል። የእንግሊዝ ኤምባሲ ተወካይ ሉሲ ጎርደን፤ ውድድሩ የሴቶችን አቅም ለማጎልበት የተዘጋጀ መሆኑን የገለጹ ሲሆን እንደ እግር ኳስ ያሉ ስፖርቶችን መጫወት ለታዳጊዎች ያለውን አስፈላጊነት አስረድተዋል። ለአካላዊ ጥንካሬ እና አዲስ ነገርን እንዲማሩም ይረዳቸዋል ሲሉም አክለዋል። ሴቶችም መሰል አጋጣሚዎችን ማግኘት እንዲሁም ተነሳሽነቱም ሊፈጠርባቸው እንደሚገባ ተናግረዋል። በመሆኑም ስልጠናው አሁን ላይ ከአዲስ አበባ የተጀመረ ሲሆን፤ የሴቶች ስፖርት በመላው አገሪቷ መስፋፋት ስላለበት በቀጣይ ስልጠናው ተደራሽነቱን የሚያጠናክር ይሆናል ተብሏል።

ስልጠናውን ከሰጡት ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆኑት አውን ሳውዝጌት በበኩላቸው፤ ስልጠናው ቀጣይነት ያለው እንደሚሆንና በቀጣይም በአጭርና በረጅም የጊዜ የመስጠት ዕቅድ እንዳላቸው ጠቁሟል።

በስልጠናው ማጠቃለያ ላይም የታዳጊዎች እግር ኳስ ውድድር በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ተከናውኗል። በውድድሩም ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 18 የሚሆናቸው ታዳጊ ሴቶች የተካፈሉ ሲሆን፤ ውድድሩም በአራት ቡድኖች መካከል ነው የተካሄደው። ቡድኖቹ የተመረጡትም በስልጠና ላይ የተካፈሉት ባለሙያዎች ከሚያሰለጥኗቸው መካከል ሲሆኑ ለውድድሩም በጎ ፈቃደኝነታቸውን ያሳዩ መሆናቸው ታውቋል። ይኸውም የውድድር ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ሴቶች እድሎች ቢመቻቹላቸው ከወንዶቹ በተሻለ ስፖርቱን ማሳደግ እንደሚችሉም ማሳያ እንደሚሆን ተገልጿል። ፌዴሬሽኑም ሴቶች ላይ አተኩሮ እየሰራ እንደመሆኑ በቀጣይም ከኤምባሲው ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ በሴቶች እግር ኳስ ላይ እየሰሩ ለሚገኙ ባለሙያዎች ስልጠናውን መስጠት እንደሚቀጥል ተነግሯል።

ስፖርት ለሰው ልጆች የሚል መጠሪያ ያለው ፕሮጀክት ማዕከል አድርጎ እየሰራ የሚገኘው እግር ኳስን ብቻ ሳይሆን እንደ አጠቃላይ ማህበረሰብን የመለወጥ አላማም በማንገብ መሆኑን የገለጸችው ደግሞ ከአሰልጣኞቹ መካከል አንዷ የሆነችው ቤሊ ቲዮንግኮ ናት። ስፖርት በሰዎች መካከል ጤናማ ግንኙነትን የሚፈጥር በመሆኑ የሴቶች እና የታዳጊዎች ተሳትፎ ከፍተኛ ሊሆን ይገባዋል ብላለች። ስፖርት ሴቶችን በማነቃቃት ከፍተኛ ሚና ያለው ከመሆኑም ባለፈ የወደፊት ሕይወታቸውንም የተቃና እንዲሆን እንደሚያግዝም ጠቁማለች።

ስልጠናውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ በመገኘት ያስጀመሩ ሲሆን፤ ከእንግሊዝ ኤምባሲ ጋር በመሰል ስልጠናዎች ላይ በጋራ በመሆን እንደሚሰሩ መግለጻቸውንም ፌዴሬሽኑ አሳውቋል።


### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ልዩ ዞን ክ/ከ ወረዳ ዱከም ከተማ አስተ የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(TIN) 0041246396 ሸንግያ ማሽነሪ ኢንጅነሪንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚኒስቴር መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ያልተሠራበት ከቁጥር 0051 እስከ 0100 የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሠራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሠርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩት በገቢዎች ሚኒስቴር መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**ግብር ከፋይ ስም ሸንግያ ማሽነሪ ኢንጅነሪንግ ኃላ/የተ/የግ ማ**

### የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬት መጥፋት ማስታወቂያ

ጋሻው በለጠ ግዛው የሙያ ደረጃ፡ በሲኒየር ፋርማሲስት የሙያ ምዝገባ ቁጥር SP=24883/2006 በአማራ ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የተመዘገበ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ጠፋብኝ ብለው በቀን 29/3/2015 ዓ.ም ከፖሊስ በተጻፈ ማስረጃ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሰውን የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ወድቆ ያገኘ ወይንም በእዳ ይዤዋለሁ የሚል በአንድ ወር ጊዜ ካላመለከተ ተለዋጭ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍባለሙብት እነ ሲሳይ ሀብታሙ እና በፍ/ባለዕዳ እነ ያምነዋል ታሪኩ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 46426 በ25/10/2007ዓ.ም እና በመ/ቁ 136155 በ14/4/2008፤5/8/2010 7/11/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/17 የቤ.ቁ 367 የሆነ ቤት መንገድ 89 ካ.ሜትር ካርታ ያለው የቤቱ ስፋት 499 ካ.ሜ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 1,109,120 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሃያ ብር ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ የካቲት 2 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

### የጨረታ ማስታወቂያ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የአርባምንጭ አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከል ቀጥሎ የቀረቡትን እቃዎችን በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

- የጽህፈት መሳሪያ ፣ኤሌክትሮኒክስ ፣ሌሎች አላቂ ዕቃዎች፣ የሞተር ሳይክል ጎማዎችና መለዋወጫ፣ የመኪና ዕቃዎች፣ የህንፃ መሳሪያ እቃዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ቆዳና ቆዳ ነክ እቃዎች፣ የህክምና ዕቃዎች እና የደንብ ልብስ ሲሆኑ፤
- መ/ቤታችን ጨረታውን የሚያከናውነው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና የግዥ አፈፃፀም መሠረት በግልጽ ጨረታ ስነ -ስርዓት ሲሆን፡
- ለውድድሩ የሚጋበዙት ተጫራቾች፤

1. በሙያው ወይም በዘርፉ ህጋዊና በዘመኑ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር /Tin Number/ ያላቸው እና ቫት ተመዝጋቢ መሆን ይጠበቅባቸዋል።
3. አቅራቢዎች ለሚጫረቱበት እቃ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና 5,000 /አምስት ሺህ ብር/በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተመሰከረ CPO ከኦርጅናል ሠነድ ጋር በማያያዝ በታሸገ ፖስታ ማቅረብ አለባቸው፤
4. የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
5. ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት የማይመለስ 50 (ሃምሳ ብር) በሎት በመክፈል የጨረታ ሰነድ በመግዛት መወዳደር ይችላሉ።
6. የመወዳደሪያ ሃሳባቸውን መ/ቤቱ በሸጠላቸው የጨረታ ሰነድ ላይ የአንዱ ዋጋ በሚለው ቦታ ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስን ያካተተ ዋጋ በመሙላት የድርጅታቸውን ማህተም በኦርጅናልና ኮፒ ፖስታ ላይ በማድረግ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
7. ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በዚህ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት በአየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ16ኛዉ ቀን የጨረታዉ ሳጥን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በማዕከሉ የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል። ሆኖም ግን 6ተኛዉ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን ይከፈታል ።
8. በጨረታዉ መክፈቻ ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች ያለመኖራቸው የጨረታዉን መክፈት አያስተጓጉልም።
9. በጨረታዉ አሸናፊ የሆነ ድርጅት ያሸነፈውን ዕቃ እስከ ማዕከሉ የማምጣትና የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡
10. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ፡-** ስልክ ቁጥር 0468811883/0468810564

**አርባ ምንጭ አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከል**